ንግሥተ ሳባም ከሰሎሞን ጋር ከተገናኘች በኋላ ጥበቡን አይታ እየተረዳች ከማድነቋ በላይ የእግዚአብሔርንም አምልኮት ከሰሎሞን ተረድታ ስታበቃ ከሰሎሞን ጸንሳ ወደ ሀገሯ ኢትዮጵያ ተመልሳ በሐማሴን አውራጃ ላይ በነበረው ቤተ መንግስቷ ስትደርስ ማይ በላ በተባለው ቦታ ከአስመራ ስድስት ኪሎ ሜትር ያኽል ርቆ በሚገኘው ወንዝ ዳር ላይ ቀዳማዊ ምኒልክን ወለደችው ማይ በላ ማለትም በትግረኛ ለሕጻኑ ውሃ አምጡለት ማለት ነው። እስከ ዛሬም ቦታው በዚሁ ስም ይጠራል።

መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ለነበሩት አንድ ባሕታዊ ከተጋድሎ ... ወደ በዓቱ ተመልሶ ሲሞት ኖምኩ ብሎ ተናገረና በመላው ኢትዮጵያ ተሰማርተው የነበሩት ከእርሱ ጋር መጥተው የነበሩ ቅዱሳን ሁሉ እንደ ብጽዓታቸው በአንዲት ሰዓት በያሉበት አረፉ። ... ይህም የሆነው ከሀገራቸው ወደ ቅድስት ሀገር ኢትዮጵያ ሲመጡ በአንድነት እንደመጣን በአንድነት እንሙት ብለው ብጽዓት ስለነበራቸው ነው። ኖምኩ (ተኛሁ) ሲላቸው ንኡም (እንተኛ) ብለው ሞቱ እስከ ዛሬም ስማቸው ጻድቃነ ንኡም ተብለው ይጠራሉ

ግብጾች ከአጼ ሰይፈ አርእድ ጋር ክርስቲያኖችን እንዳያጠቁ የገቡትን .... ቃል በማፍረሳቸው ምክንያት አጼ ዳዊት ዓባይን ከገደቡና በጳጳሱ ሽምግልና ክርስቲያኖቹን ነጻ ስላወጡ ... የዓባይን ውኃ እንደቀድሞው እንዲፈስ ለቀቁላቸውና ያንን ቦታ ውኃው ተቋርጦበት ስለነበርካርቱም ተባለ ካርቱም ማለት ተቋረጠ ማለት ነው። ከርቶ እንዲል ትግሬ ክሩት ማለት ነው በትግረኛ ቆረጠ ሲል ከረተ እንዲል።

ከመጽሐፉ ውስጥ ገጽ የተወሰደ

ZA -Printing Press
0913339421/ 0927948872

www.ethiopianorthodox.org

ዋጋ 61.00

COVER DESIGN BY 0913398716 BDM

ጥንተ አሚን ዘኢትዮጵያ

ርእሰ ደብር ዕቁበ እንድርያስ ዓስቡ

# ጥንተ አሚን ዘኢትዮጵያ

አሳሳቢውና አዘጋጅ
ርእሰ ደብር ዕቁበ እንድርያስ ዓስቡ
ዘአግአዝያን ትምህርት ቤቶች ኃላፊ

# ጥንተ አሚን ዘኢትዮጵያ

አሰባሳቢውና አዘጋጅ፡

ርእሰ ደብር ዕቁበ እንድርያስ ዓለሙ
ዘአግአዝያን ትምህርት ቤቶች ኃላፊ

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ
በ፴፱ኛው ዘመነ መንግሥት
በ፲፱፻፷፩ ዓመተ ምሕረት ታተመ

www.ethiopianorthodox.org



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ ፡ ርእሰ
ሊቃነ ጳጳሳት ፡ ወፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ



እምዕለት ዕለተ ይዌስክ ንጉሥ ዓመቲሁ ፡ መዝ. ፷ ፮
ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ
ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ።

www.ethiopianorthodox.org

እና እኔም ይህችን በገጽ ብዛትዋ ትልቅ የማትባል መጽሐፍ ሳነብ የገረመኝን በመጻሕፍት ዙሪያ ለማውቃቸው ወዳጆቼ ሳካፍላቸው ይህስ ቁም ነገር ታትሞ ለብዙ ሰው በደረሰ ስላሉኝ መሠረታዊ የኃሳብ ለውጥ ያመጣሉ ብዬ ካሰብኩዋቸው ጥቂት የፊደል እርማቶች በቀር ምንም ሳልነካ ለህትመት ልኬዋለሁ።

የመጽሐፉ መጠን አሁን በገበያ ላይ ከሚገኘው መጠን ጋር እንዲጣጣም ስል መጠኑን አሳድጌዋለሁ።

በመጽሐፉ ውስጥ ያለው ቁም ነገር ለብዙዎች እንዲዳረስ ካለኝ ጽኑ ፍላጎት ውጪ ሌላ መጽሐፉን የማሳተም ምክንያት የለኝምና በቅንነት አንብባችሁ እንድትጠቀሙ በትህትና አስታውሳለሁ።

አሐዱ ኮነ (የብዕር ስም)


የውስጥ መልክእ እና ቅንብር
ቤz ማስታወቂያ እና ኅትመት
BEz Advertizing & Printing
0919326708
0921879024


## የአርእስት ማውጫ


| | ርእስ | ገጽ |
|---|---|---|
| ፩ | ስነ ፍጥረት | 15 |
| ፪. | አግአዝያን | 18 |
| ፫ | ትውልደ አብርሃም | 19 |
| ፬ | ንግሥተ ሳባ | 21 |
| ፭ | ሰሎሞናዊ መንግሥት ዘኢትዮጵያ | 22 |
| ፮ | ቀዳማዊ ምንሊክ | 24 |
| ፯ | ፍሬ ምናጦስ | 27 |
| ፰ | አብርሃ | 30 |
| ፱ | አጽብሐ | 30 |
| ፲ | ጻድቃነ ንኑም | 34 |
| ፲፩ | አባ ሊባኖስና አባ ዮሐኒ ስለ … ቅዱሳን | 37 |
| ፲፪ | ዓፄ ካሌብ | 41 |
| ፲፫ | ሀገረ ናግራን | 44 |
| ፲፬ | ዘእስራኤልና ዓፄ ገብረ መስቀል | 46 |
| | የአፍ ታሪክ | |
| ፲፭ | ዓፄ ዓምደጽዮን | 49 |
| ፲፮ | ዓፄ ዳዊት ቀዳማዊ ዘኢትዮጵያ ንጉሥ | 50 |
| ፲፯ | ግራኝ ንጉሥና ዓፄ ልብነ ድንግል | 55 |
| ፲፰ | ፖርቶጌዝ አመጣጥ | 58 |
| ፲፱ | ፖርቶጊዞች ሥራ | 62 |
| ፳ | ከግራኝ ጋራ ጦርነት | 64 |
| ፳፩ | ግራኝ ሞት | 67 |
| ፳፪ | ዓፄ ሱንዮስ | 74 |



www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| ፳፫ | ዓፄ ፋሲል | 82 |
| ፳፬ | አባ ርዝላና አባ ጁስፐ | 89 |
| ፳፭ | አባ ያዕቆብ ፈረንሣዊ | 93 |
| ፳፮ | ዓፄ  ቴዎድሮስና ደጃች ንጉሤ | 96 |
| ፳፯ | አባ ማስያስና ደጅአዝማች ንጉሤ | 96 |
| ፳፰ | አባ ማስያስና ዓፄ ሚኒልክ | 100 |
| ፳፱ | ዓፄ ዮሐንስ | 102 |
| ፴ | ደጅአዝማች ባሕታ | 105 |
| ፴፩ | ልዑል ራስ መንገሻ ዮሐንስ | 107 |
| ፴፪ | ሐማሴን መባል ቀርቶ ኤርትራ የተባለችበት | 109 |
| ፴፫ | ኢጣልያ መንግሥት ትምህርት ቅነሳ | 111 |
| ፴፬ | ኢጣልያ መንግሥት የግፍ ሥራ | 112 |
| ፴፭ | እንግሊዝ መንግሥት | 129 |
| ፴፮ | ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ | 132 |


www.ethiopianorthodox.org

www.ethiopianorthodox.org

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፩ዱ አምላክ ንዌጥን በረድኤተ እግዚአብሔር ተዋሥኦተ አሚን ወዜና ዘኢትዮጵያ በእንተ ምክንያተ ስብከተ ሐሰት ዘባዕዳን ይጽሕፍዎ ወይዜንው እንዘ ይብሉ ቀዳሜ ስብከቱ ለአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ዘሃይማኖት ዘካቶሊካዊት ሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ይእቲ ወሚመቶሂ ዘአም አባ አትናቴዎስ ሊቀ ጳጳሳት ዘእምርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ሮማዊት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ውእቱ ወበዝ ሃይማኖት ነበረት ኢትዮጵያ እስከ ፳፻ ዓመተ ምሕረት እምልደተ እግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ እንዘ ይብሉ።

ወበእንተ ዝንቱ ነገረ ሐሰት እጽሕፍ ወእወሥእ ነገረ ጽዱቀ ወእሙነ ዘተረክበ እምዜና አበው ቅዱሳን ወእመጻሕፍት ቅዱሳት፤ ወእምክብረ ነገሥት አስተጋቢእየ በከመ ክሂሎትየ ከመ ያንብብዋ ወይትዋሥኡ ባቲ እንዘ እነግር ወእከሥት ዘኮነ በበጊዜሁ ወበበመዋዕሊሁ በእንተ ዜና ወአሚን ዘኢትዮጵያ ሀገሪትነ እምኦሪተ ሙሴ እስከ ይእዜ እግዚአብሔር ያብርህ አዕይንተ አልባቢነ ወይባርህ ተግባረነ ለዓለመ ዓለም አሜን።

www.ethiopianorthodox.org

## መቅድም

ይህ መጽሐፍ የኢትዮጵያን የሃይማኖት ጥንትነትና የነገሥታትዋን ጥንታዊ ኃይል የሚገልጽ ሲሆን የተጻፈበት ምክንያትም ብዙ ሰዎች የሀገራቸው ኢትዮጵያን ታሪክ ሳይማሩና ሳያውቁ የውጭ ሀገር ሰዎች ኢትዮጵያውያንን ለማታለልና ሀገሪቱን ለመውረር እንዲመቻቸው የኢትዮጵያ ታሪክ እያሉ የጻፉትን በማንበብና በመረዳት የኢትዮጵን ክብር የሚቀንስ የፈጠራ ታሪክን የኢትዮጵያ ታሪክ እያሉ በኢትዮጵያ ቋንቋ በጽሑፍና በጋዜጣ በየጊዜው እየጻፉ የዘረጉትን የጥፋት መረብ ለማስተካከል፤ በሕዝቡም ዘንድ ቅሬታና ንትርክ መፍጠሩን ለማስተካከል ነው ።

ይህም ‹‹ኢትዮጵያ ጥንታዊ ሃይማኖትዋ በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተሰበከላት የሮማዊት ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ነው። የአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የጵጵስናው ሹመትም በርእሰ ሊቀ ጳጳሳት ሮማዊት በስተታች ስለሆነ ኢትዮጵያ ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከ፫፻፴፫ ዓ.ም ጀምራ እስከ ፲፮ ዓ.ም በሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት አምና ስለ ነበረች ሮማዊት ግንድ ስትሆን ኢትዮጵያዊት ቤተ ክርስቲያን ግን የሮማዊት ቅርንጫፍ ናት›› ሲሉ ይጽፋሉ።

ስመ ጥሩው ዓፄ ካሌብ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያም ሃይማኖቻቸው የሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ሃይማኖት ፩ ባሕርይ የሚል ነው። ፱ቱ ቅዱሳንም ሃይማኖታቸው የሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ስለሆነ ‹‹በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ ያስተማሩት የሰበኩት የ፩ ባሕርይ





ሃይማኖት ነው›› ሲሉ በማየቴ እንባቢ ትክክል መስሎት እንዳይሳሳት ለማስረዳት ነው። ዳግመኛም የባዕድ ሃይማኖት ሰባክትም ከዚህ ቀደም በሰባክያኑ በየጊዜው መጥተው በኢትዮጵያ ላይ የውጭ ሰዎች ሐዲስ ሃይማኖት በመስበክና በማስተማር፡ የእስልምና ሃይማኖት ሰባክያንም የቱርክን መንግሥት በማስመጣት፡ የሮማዊት ቤተ ክርስቲያንና የእስጳንያ ኢየሱሳውያን ማኅበር በሚል ስም በየጊዜው ሃይማኖት ለመስበክ የመጡት ነጮች በሰበኩት የሃይማኖት ጠንቅ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለያይተው እርስ በእርስ ማጋጨትና ውጊያ በመፍጠር ኢትዮጵያን ለመከፋል የጣሩት እነእርሱ እንደሆኑ ለማጋለጥ፤ የነገሥታትዋ ኃይልና የሕዝብዋ አንድነት እየደከመ በመሄዱ የባዕድ መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር የተመቸ ጊዜ ማግኘታውን ትውልዱ እንዲያውቅ ለመናገርና በኃሳብ ለማገዝ፤ በባዕዳን መንግሥት ኢትዮጵያ የደረሰባትን ግፍና መከራ በየጊዜው ከተፈጸመው አንድ አንድ ከብዙ በጥቂቱ ለመግለጥ ይህን መጽሐፍ ጽፌለሁና አንብበው ለማለት ነው።

ስለዚህ እኔም ይህን መጽሐፍ የጻፍኩት እውነተኛውን የኢትዮጵያ ታሪክ በጎንደር ከሚገኘው ጥንታዊ ጽሑፍ ክብረ ነገሥት፤ ሁለተኛም አክሱም ላይ ከሚገኘው ጥንታዊ ጽሑፍ ክብረ ነገሥት፤ ሦስተኛ የውጭ ሀገር ሰው ቻርልስ ዊልያም ኢንዘንበርግ ማርቲን ፍላድ ከጻፈው የእግዚአብሔር መንግሥት ከተባለው መጽሐፍ አስተዋጽኦ በማድረግ ነው።

www.ethiopianorthodox.org

አሁንም ደግሜ እላችኋለሁ ይህን መጽሐፍ ያዘጋጀሁት ባጭሩ የኢትዮጵያ የጥንት እምነትዋን የነገሥታትዋንም ኀይልና ሥልጣኔ፡ ስለ ሀገራቸው ኢትዮጵያም በየጊዜው የጀግንነት ሥራቸውን የፈጸሙበትን ጊዜና ዓመተ ምሕረቱን ለይቼ ለማመልከት ነው። ኤርትራም ከጥንት ጀምራ የኢትዮጵያ መሠረት ስትሆን ከኢትዮጵያ ሀገርዋ በሃይማኖት ሰባክያን ሰበብ/ምክንያት ገብቶ ፶፱ ዓመት ለይቶ እጅ አድርጎ ኢጣሊያውያን ለይተዋት ከነበረበት ዘመን በቀር ከኢትዮጵያ ተለይታ እንደማታውቅ ለመጪው ትውልድ ለማስረዳት፤ ጽሑፉን አንብቦ ኢትዮጵያ ኤርትራ ኤርትራም ኢትዮጵያ መሆንዋን እንዲረዳውና ስለ ሀገሩ ያለውን ፍቅር በልቡናው ውስጥ እንዲያሳድር ስል ይህን መጽሐፍ ጥንተ አሚን ዘኢትዮጵያ የሚል ስም በመስጠት ጽፌ ለኢትዮጵያ ወጣቶች አበረክታለሁ አንብባችሁ በሥጋና በነፍስ እንድትጠቀሙበት አሳስባችኋለሁ።





# ምዕራፍ ፩

## ሥነ ፍጥረት

እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን በሰማይና በምድር ያሉትን ብርሃናንና ጨለማን፣ ተንቀሳቃሽና የማይንቀሳቀስን፣ መላእክትንና ሰውን፣ እንስሳትንና አራዊትን ሲፈጥር አዳምን ሕያው፣ ነባቢ እና ለባዊ አድርጎ በአምሳያው ፈጠረው። ከፈጠረውም በኋላ ከጎኑ አንዲት አጥንት ነሥቶ ሔዋንን አስገኘለት። አዳምና ሔዋንን ከገነት አግብቶ ባስቀመጣቸው ጊዜም በገነት ያሉ ዕፀዋትን ሁሉ ብሉ ሲላቸው በገነት መካከል ካለች ዕፀ በለስ ግን አትብሉ ከርሷ ስትበሉ ሞት ትሞታላችሁ ሲል ትእዛዝ ሰጣቸው።

ይህንንም ያደረገ የጾምን ሕግ ለማስተማር ነው እንጂ ነፍጓቸው አይደለም። አዳምና ሔዋን ግን ትእዛዙን ጥሰው፤ በምክረ ከይሲ ተታለው፤ አምላክነቱን ሽተው፤ አትብሉ ያላቸውን ዕፀ በለስ በልተው፤ ከኃጢአት ላይ ወድቀው እንዲቀመጡበት ከሰጣቸው ገነት ወጥተው፤ ከሥልጣናቸው ተሽረው በዚች ምድር ጥረው ግረው እንዲበሉ አዝዟቸው ሲያበቃ ብዙ ተባዙ ምድሪቱንም ምሉዋት ብሎ በፍጥረቱ ሁሉ አሠልጥኖ

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፪

## አግአዝያን

በዚህም ሁኔታ ሲኖሩ ሳለ በንጉሥ ጺኦሪ ዘመነ መንግሥት፤ በርማ የሚባል የሕንድ ንጉሥ እስያንና ግብፅን ጠቅልሎ ሲገዛ ነበርና ኢትዮጵያንም ለመግዛት ለወረራ መጣ፡፡ የኢትዮጵያ ንጉሥ የነበረው ጺኦሪም ፈርቶ እሺ ባንተ እገዛለሁ ሲል እኒህ ነገደ ዮቅጣን የሆኑ የሴም ዘሮች ግን ‹‹በሀገራችን ኢትዮጵያ የሌላ መንግሥት አናስገባም›› ብለው ከሕንድ ንጉሥ ከበርማ ጋር ተዋግተው፤ ድል አድርገው፤ ከኢትዮጵያ ካስወጡት በኋላ የነገደ ካም የጺኦሪ መንግሥትን ሽረው፤ ከርሳቸው ወገን አክናሁስ ፪ኛ ሳባ የተባለውን አንግሠው፤ ሴማውያን ይባሉ የነበሩትን አግአዝያን ተባሉ፡፡ አግአዝያን ማለትም ነፃ አውጭዎች ማለት ነው፡፡

፪ኛ ሳባ ኢትዮጵስን ይወልዳል፤ ኢትዮጲስ ባለው ከለውን፤ ሦስተኛው ሳባ ኖባ ላክንዱንና ፰ቱን ይወልዳል፡፡ ሴማዊ የነበረው ቋንቋቸው በአግዝያን ቋንቋ ግእዝ ተባለ፡፡ ዘመነ መንግሥታቸውም ከአክናሁስ ፪ኛ ሳባ አንሥቶ እስከ ቀዳማዊ ምኒልክ ከ፩ ሺ ፱፻፹፭ (1985) እስከ ፱፻፹፪ (982) ዓመት ነበረ፡፡ የነገሡትም ነገሥታት ፶፪ (52) ናቸው፡፡ ዘመኑም ፩ ሺህ ፫ (1003) ዓመት ነው፡፡



www.ethiopianorthodox.org



በዚህ ጊዜ የእግዚአብሔር አምልኮት ጠፍቶ ዓለም ሁሉ በፀሐይና በጨረቃ፣ በድንጋይ፣ በዛፍና በዕንጨት ሰው አስመስለው ሠርተው ሐንፀው እያመለኩ እስከ ሤሩህ ወልደ ራግው ቆይተዋል፡፡ ሤሩህ ናኮርን፣ ናኮር ታራን፣ ታራ አብርሃምን እስኪወልድ ድረስ ዕንጨት ጠርበው ወርቅ ቀብተው ይህ ነው ሰማይና ምድር የፈጠረ አምላክ እያሉ ይሰግዱለት ነበር (ዘፍ.፩: ፳፪-፳፯)፡፡

### ትወልደ አብርሃም

በዚህ ዘመን የተወለደ አብርሃም በሰው እጅ ለተሠራ አምላክ አልሰግድም ብሎ ፀሐይን የፈጠረ አምላክ እንዳለ ተመራምሮ ‹‹አምላከ ፀሐይ ተናበበኒ፤ ፀሐይን የፈጠርክ አምላክ ተናገረኝ›› ብሎ በጸለየ ጊዜ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝ ከአባትህ ቤት ውጣ፤ ከዘመዶችህም ተለይና ላንተም ለልጆችህም የምትሆን ወተትና ማር የምታፈስ ምድርን አወርስሃለሁ፤ ታላቅ ሕዝብም አደርግሃለሁ፤ እባርካሃለሁ ስምህንም በምድር ላይ ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ እባርክሃለሁ ፤ የባረኩህን እባርካለሁ የረገሙህንም እረግማለሁ በዘርህም የምድር አሕዛብ ይባረካሉ›› አለው (ዘፍ.፲፪: ፩-፫)፡፡

(ዘፍ.፲፪:፩) አብርሃም ከእግዚአብሔር ቡራኬ ተቀብሎ ይስሐቅን፣ ይስሐቅም ያዕቆብን ወለደ:: እግዚአብሔር ያዕቆብን ‹‹ኢይኩን እንከ ስምከ ያዕቆብ ዳዕሙ ይኩን ስምከ እስራኤል እንግዲህ ስምህ እስራኤል እንጂ ያዕቆብ አይባል›› ብሎ ስሙን እስራኤል ሲል ጠርቶ፤ ‹‹ብዛ ተባዛ የምድር አሕዛብ ባንተ ይሁን፤ነገሥታትና አሕዛብ ካንተ ይገኙ ዘንድ ይሁን›› አለው:: በዚህ መሠረት ያዕቆብ የነበረው ስም እስራኤል ልጆቹም ደቂቀ እስራኤል ተብለው ተጠሩ:: የእግዚአብሔር አምልኮት በደቂቀ እስራኤል ብቻ ሲገኝ ሌላው ዓለም ሁሉ ከእግዚአብሔር አምልኮት ርቆ፤ የድንቁርና ጨለማ ተውጦ በነበረ ጊዜ እግዚአብሔር ሕጉንና ትእዛዙን በጽላተ ኪዳን ጽፎ፤ ለሙሴ ሰጠው:: እስራኤልም በዚህ ሕግ ጸንተው፤ እግዚአብሔርን እያመለኩ፤ እስከ ዳዊት ንጉሥ እስከ ሰሎሞን ወልደ ዳዊት ሲኖሩ፤ ሰሎሞን ንጉሥ ቤተ መቅደስን ሠራ:: በዚያም ላይ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርቦ ቅን ፍርድን ይገለጽለት ዘንድ እግዚአብሔርን በለመነ ጊዜ እግዚአብሔር የለመነውን ማስተዋልንና ያልለመነውን ጥበብንና ሀብትን የመንግሥቱንም ስፋት ጨምሮ ሰጠው:: የሰሎሞን ጥበብና ገናናነትም በዓለም ሁሉ ታወቀ:: ጥበቡም በሙሉ ዓለም ተደነቀ::



www.ethiopianorthodox.org



በዚህም **ንግሥተ ሳባ** ወይም (ንግሥተ አዜብ) ወይም (ማክዳ) የኢትዮጵያ ንግሥት የሰሎሞን ጥበብንና ገናናነቱን ሰምታ፤ ጥበቡን አይታ ለመረዳት ከኢትዮጵያ ተነሥታ በታላቅ ጉዞ በብዙ ከብትና ግመሎች፣ ብዙ ወርቅ፣ ብዙ ሽቱና የከበረ ዕንቁ ጭና ለሰሎሞን እጅ መንሻ ይዛ ወደ ኢየሩሳሌም ሔደች:: ከሰሎሞንም ጋር ተገናኘች (ነገሥት ቀዳማዊ ፲፩-፲፫፤ ዜና መዋዕል ፩-፲፫፤ ማቴ.፲፪: ፵፪):: የሔደችበትም ዘመን የሰሎሞን ፳ኛ ዓመተ መንግሥት ነበር::

ንግሥተ ሳባም ከሰሎሞን ጋር ከተገናኘች በኋላ ንጉሥ ሰሎሞን በክብር ተቀብሎ እያነጋገራት ሲኖር ጥበቡን አምልኮቱን ከሰሎሞን ተረድታ ስታበቃ ከሰሎሞን ፀንሳ ወደ ሀገርዋ ኢትዮጵያ ተመለሰች:: ወደ ሀገርዋ በመጣች ጊዜም በሐማሴን አውራጃ ላይ በነበረው ቤተ መንግሥቷ ስትደርስ ከአሥመራ ፯ ኪሎ ሜትር ያህል ርቆ በሚገኘው ማይ በላ በተባለው ቦታ ወንዝ ዳር ላይ ቀዳማዊ ምኒልክን ወለደችው:: ማይ በላ ማለትም ለሕፃኑ ውሃ አምጡ በሉ ማለት ነው፤ እስከ ዛሬም ቦታው በዚህ ስም ይጠራል::

ቀዳማዊ ምኒልክ ከንግሥተ ሰባ ተወልዶ የ፳፪ ዓመት ወጣት፤ ከሆነ በኋላ ወደ አባቱ ሰሎሞን ኢየሩሳሌም ሄዶ፤ በዚያው ሕገ

ኦሪትና ሥርዓተ መንግሥትን እየተማረ ፫ ዓመት ቆየ። በ፱፻፺፩ (991) ዓመት ከክርስቶስ ልደት በፊት አባቱ ሰሎሞን ልጁ ምኒልክን ከ፲፪ ነገደ እስራኤል ትውልድ ፲፪ ሺሕ፤ ከብልሐተኞቹ ጥበብ ያላቸውን ፲፪ ሰዎች፤ እንዲሁም ለሌዋውያን ፣ ሕገ ኦሪትና አምልኮተ እግዚአብሔርን የሚያስተምሩ ካህናት፤ ከመኳንንትም ፳፪ አለቆች ከርሱ ጋራ የሚመጡ ሠራዊት አዘለት፤ ይዞ መጥቶ፤ የእናቱ ንግሥተ ሳባ መንግሥትን ወርሶ፤ የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት ይሆን ዘንድ ወደ ኢትዮጵያ ላከው።

ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ተያይዞ የመጣው **ሰሎሞናዊ መንግሥት** እስከ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ጸንቶ ይገኛል። ጽላተ ሙሴም በዚህ ጊዜ በእግዚአብሔር ፈቃድ አብረው በመጡት ካህናት አማካይነት ወደ ኢትዮጵያ ገብታለች። ሕገ ኦሪትም ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ከአብርሃም ተያይዞ የመጣውየእግዚአብሔር እምነት በኢትዮጵያ ጎልቶ ይታይ ነበር። የኢትዮጵያ ሕዝብም በዚህ ብርሃን እየተመላለሰ ሲኖር ኖሮ ዳዊት ንጉሥ ‹‹ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር›› (መዝ.፷፯:፴፩)፤ ይገንዩ ቅድሜሁ ኢትዮጵያ ወጸላእቱሂ ሐመደ ይቀምሑ (፷፩:፲፯) ሲል የተናገረው ትንቢት ተፈጽሞለት



www.ethiopianorthodox.org



በእግዚአብሔር እምነት ጸንቶ ሲኖር በሮማና ከእስራኤል በቀር በሁሉ ዓለም አምልኮተ እግዚአብሔር ጠፍቶ ከዕንጨትና ከድንጋይ ከዛፍና ከምስል የተሠራ ጣዖት ሲመለክ ነበር። የኢትዮጵያ እምነትና ሃይማኖት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ ስለሆነ ኢትዮጵያ በሃይማኖት ግንድ እንጂ የሮማ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያን ከግንድ ዛፍ የወደቀ ቅርንጫፍ ናት እንደሚሉት አይደለችም።እንዳይደለችም ለማስረዳት ይኸው ዳዊት በሁለተኛ ትንቢቱ ይገልጽልናል።ሥርወ መንግሥቷም ከዳዊት ከሰሎሞን ወገን ነው። እግዚአብሔር ዳዊትን "ወአሐንፅ ለትወልደ ትውልድ መንበረከ ባለው መሰረት ከዳዊት ከሰሎሞን ከቀዳማዊ ምኒልክ ተያይዞ የመጣው ሰሎሞናዊ መንግሥት በኢትዮጵያ ብቻ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጸንቶ ይገኛል።

## ምዕራፍ ፫

ኢትዮጵያ በእምነትዋ **ቀዳማዊ ምኒልክ** ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ፱፻፺፩ (991) ዓመት ከመጣላት ጊዜ ጀምሮ በነበራት እምነት ጸንታ ስትኖር ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልደ። በአካለ ሰብእ እየታዩ በዚህ ዓለም ሥራውን ፈጽሞ ሙቶ ተነሥቶ ወደ ሰማያት አረገ። በኋላም በኦሪት ሕግ በዓመት ሁለት ወይም አንድ ጊዜ ኢየሩሳሌም ሒዶ መስገድና መሳለም እንዲገባ ታዝዟልና ሕዝቡ ራሱ፣ ነገሥታቱም አንድ መልክተኛ እንደራሲያቸውን ወደ ኢየሩሳሌም ይልኩ ነበር።

በዚህ ልማድ ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ በ፪ኛው ዓመት በ፴፭ኛው (35) ዓ.ም የህንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ ጃንደረባ (እንደራሴ) እንደተለመደው ከንግሥቲቱ ተልኮ፣ ኢየሩሰሌም ሂዶ ሰግዶ ሲመለስ ሰሎሞን ለንግሥተ ሳባ ጉልት እንዲሆናት ከሰጣት ጋዛ ከተባለችው ሀገር በደረሰ ጊዜ ጃንደረባውም በሰረገላ ተሣፍሮ ሲያልፍ (ጌታ) መንፈስ ቅዱስ ከ፸፪ አርድእት የሆነውን ፊልጶስ ሐዋርያን ጠርቶ ‹‹ሑር ትልዎ ለዝ ሠረገላ ሠረገላውን ተከትለኸው ሂድ›› ብሎ ተናገረው። ፊልጶስም ወደ ሠረገላው ቀርቦ ጃንደረባው መጽሐፈ ኢሳይያስ ሲያነብ ሰማውና



www.ethiopianorthodox.org



‹‹ይህን የምታነበውን መጽሐፍ ምሥጢሩን ታውቀዋለህን›› ሲል ጠየቀው። ጃንደረባውም ‹‹ማን ባስተማረኝ ልወቀው? አንተ ና እና በሠረገላዬ ውጣ ወጥተህም ንገረኝ›› አለው። ፊልጶስም በሠረገላው ላይ ወጥቶ በተቀመጠ ጊዜ ጃንደረባው ይህ ነቢይ የሚለው ስለ ራሱ ነው ወይስ ስለ ሌላ ነው ሲል ፊልጶስን ጠየቀው። ፊልጶስም ነቢይ የተናገረው ስለ ክርስቶስ መሆኑንና ክርስቶስም ከሰማያት ወርዶ መወለዱን መሞቱንና ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ ዓለሙን አድኖ ወደ ሰማይ መውጣቱን ነገረውና በርሱ አምኖ የተጠመቀ ይድናል ሲል አስረዳው።

ጃንደረባውም ወዲያው አምኖ ‹‹እንኪያስ ይኸው ውኃ ለመጠመቅ የሚከለክለኝ ምን አለ?›› ብሎ ቢጠይቀው ፊልጶስም ‹‹ካመንክ የሚከለክልህ የለም›› አለውና አብረው ከወንዙ ወረዱ። ፊልጶስም ጃንደረባውን አጥምቆት ከወንዙ በወጡ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ በደመና ነጥቆ ፊልጶስን ወደ ሀገረ ስብከቱ ወሰደው። ከዚያም በኋላ ጃንደረባው ፈጽሞ አላየውም (ግብ ሐዋ. ፰፡ ፳፮-፴፱)።

ጃንደረባውም ደስ እያለው ወደ ኢትዮጵያ ሀገሩ ተመልሶ ገብቶ፤ ባገኘው ጸጋ እየተደነቀ፤ ከፊልጶስ የተረዳውን ትምህርትና የተደረገለትን ተአምራት እየሰበከ፤ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን መወለዱንና ዓለሙን በሞቱ ማዳኑን አምኖ እንደ ተጠመቀ እየገለጸ አስተማረ።

በዚህ ጊዜ ዘመነ ሐዲስ መጀመሪያ በኢትዮጵያ ተሰበከ። ሮማ ግን በዚህ ጊዜ ጣዖት እያመለከች፤ወንጌልን የሚያስተምሯት ሐዋርያትንም ስትሰቅልና ስትገድል እንደ ነበረች ታሪኳ ግልጽ ሆኖ ይነገራል።
እንባቢ ሆይ የኦሪት የነቢያት መጻሕፍትና የእግዚአብሔር አምልኮት ከሮማ ከሌላውም ዓለም በፊት በኢትዮጵያ ተስፋፍቶ መኖሩን ይህን ጃንደረባ የንግሥት ህንዳኬ እንዳራሴ በዚያን ጊዜ መጽሐፈ ኢሳይያስን ሲያነብ በመታየቱ ልትረዳው ትችላለህና የሀገርህ ክብርና ሃይማኖት ቀዳማዊ መሆኑን አስተውል።
እንግዲህ ኢትዮጵያ ሀገራችን በንግሥተ ህንደኬ (ገርሳሞት) ቢትወደድ እንደራሴ (ጃንደረባ) የተሰበከላት ሃይማኖት ክርስቶስ ከድንግል ማርያም መወለዱን ከማመንዋ በላይ በሕገ ኦሪት እየተመላለሰች እስከ ፍሬምናጦስ ዘመን ፫፻፴፫ 333 ዓመተ ምሕረት ቆይታለች።ኤዛና ንጉሥ ከሞተም በኋላ እስከ ባለቤቱ

www.ethiopianorthodox.org





ሶፍያ ንግሥት በዘመነ ሐዲስ ደግሞ እስከ አብርሃና አጽብሐ በክርስቶስ እምነት ጸንታ የኖረች መሆኑን አስተውል።

## ምዕራፍ ፬

**ቅዱስ ፍሬ ምናጦስ** (አባ ሰላማ) ትውልዱ ከፅርዕ (ግሪክ) ሲሆን አባቱም ነጋዴ መረጻም (ማርጽዮስ) ይባላል። ግሪካዊ ሳለ የሚመጣበት ከጢሮስ ነው። ይህ ግሪካዊ ነጋዴ ሲነግድ ፪ቱ ልጆቹን ይዞ ከጢሮስ ወደ ኢትዮጵያ በመርከብ በመጣ ጊዜ ወደ ምጥዋ ወደብ ድኅኖ በተባለው የምጥዋ ወደብ ሲደርስ ሞተ። የምጥዋ ሰዎችም እነዚህ ፪ቱ ልጆቹን ሲድራኮስ (ኤድዮስ) ና ፍሬምናጦስ በመርከቡ ላይ አግኝተው፤ ይዘዋቸው መጡና ለሐማሴኑ ገዥ ባሕረ ነጋሽ ሰጡት። ባሕረ ነጋሽም ተቀብሎ ወስዶ አክሱም ላይ ለንግሥት አሕየዋ ወይም (ሶፍያ) ሰጣት። እርሷም ባልዋ ኤዛና ንጉሥ ሙቶ ስለ ነበር ልጆቻቸው አብርሃና አጽብሐ ሕፃናት ስለነበሩ እስከ ፫፻፵፫ ድረስ የኢትዮጵያ መንግሥት በርሷ ግዛት ነበር። እርስዋም ፍሬምናጦስን ብልህ በመሆኑ ለልጆችዋ አብርሃና አጽብሐ ሞግዚትና ጸሐፊ ሲድራኮስንም ጠጅ አሳላፊ አድርጋ ታኖራቸው ነበር።

ፍሬምናጦ በሀገሩ ሳለ ከሕፃንነቱ ጀምሮ ወንጌል እየተማረ ያደገ ክርስቲያን ስለ ነበር በቤተ መንግሥትና በአራቱ ሊቀ ካህናት እንበረም ከተባለው ካህን ዘንድ መወደድና መታወቅ ነበረው፡፡ ፍሬ ምናጦስ ሊቀ ካህናቱን ‹‹ምንትኑ ግዕዛ ለኢትዮጵያ ናሁ እሬኢ እምነተ ወግዝረተ ወጥምቀተ ወቀሪበ ቁርባንሰ ወስብከተ ወንጌል አልብኩሙ - እንዴት ነው የኢትዮጵያ ልማድ ወይም ባህል እንሆ እምነትን ግዝረትንና ጥምቀትን አያለሁ ቁርባንና ስብከተ ወንጌል ግን የላችሁም›› አለው፡፡

ሊቀ ካህናቱም ‹‹ጥምቀተ ወግዝረተ አምጽኡ ለነ አበዊነ ሌዋውያን ወጥምቀትሰ አምጽአ ለነ ሕፅዋ ለህንደኬ ንግሥተ ኢትዮጵያ ወለቀሪበ ቁርባንሰ ወለስብከተ ወንጌል ኢተፈነወ ሐዋርያ ላዕሌነ፡፡

እምነትንና ግዝረትን ያመጡልን አባቶቻችን ሌዋውያን ናቸው፡፡ እምነትንና ጥምቀትን ያመጣልንም የህንደኬ የኢትዮጵያ ንግሥት ቢትወደድ (ጃንደረባ) ነው፡፡ ለቁርባንና ለወንገጌል ስብከት ግን አልተላከልንም›› አለው፡፡





ከዚህ በኋላ ሊቀ ካህናቱ ከቤተ መንግሥት ጋር ተማክሮ ለዚሁ ነገር አንድ ጳጳስ ማስመጣት አስፈላጊ መሆኑን ተረድተው ንግሥቲቱና ልጆችዋ አብርሃ ና አጽባሐ ከመኳንንቱ ጋር መክረው ጳጳስን ለማስመጣት አሰቡ፡፡ ፍሬ ምናጦስንም ‹‹አንተ በምታውቀው መንገድ ሂድልንና ጳጳስ አምጣልን›› ብለው ስንቁንና ለመንገድ የሚሆነው ብዙ ገንዘብ ሰጥተውት ላኩት፡፡ ፍሬ ምናጦስም ፫፻፲፰(ሦስት መቶ አሥራ ስምንቱ) ሊቃውንት በኒቅያ ጉባኤ ተገኝተው፤ ወልድ ፍጡር ያለውን አርዮስን ረትተው፤ አውግዘው ለይተውት፤ ሃይማኖትን አደላድለው፤ ወደየአገራቸው ለመሄድ በሚለያዩበት በ፫፻፳፰ ዓ.ም ደረሰ፡፡ አራቱ ሊቃነ ጳጳሳት በተቀመጡበትም ቀርቦ ‹‹ኢትዮጵያ የተባለችው ሀገር ከዚህ ቀደም የሕገ ኦሪት እምነት በኋላም የክርስቶስ ልደትና ጥምቀት ሲኖራት የቁርባን ሥርዓትና ወንጌል ግን ሳይሰበክላት አለችና ወንጌልን የሚያስተምራት አንድ ጳጳስ ሹማችሁ እንድትልኩላት ስል መልእክት ይዤ መጣሁ ብሎ ነገራቸው፡፡ እነሱም የአፍሪቃ ክፍል በመሆኗ በኒቅያ አፈ ጉባኤ ለነበረው የእስክድርያው ሊቀ ጳጳስት አባ እለ እስክንድሮስ ‹‹አንተ ሹምላት›› አሉት፡፡

www.ethiopianorthodox.org



www.ethiopianorthodox.org

አባ እለ እስክንድሮስም ፍሬምናጦስን አንተ ባወቅኸው ቋንቋና ባህል ልታስተምራት ትችላለህና ካንተ የተሻለ አናገኝም ብሎ ሊሾው ወደደ:: ፍሬምናጦስም ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያንና የወንጌል ትምህርትን እያደላደለ ፫ ዓመት በእስክንድርያ ቆይቶ አባ እለ እስክንድሮስ ሙቶ በሱ ምትክ አባ አትናቴዎስ ተሹሞ በነበረበት ጊዜ በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት በአባ አትናቴዎስ ተቀብቶ አባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን አሰኝቶ ለኢትዮጵያ ጳጳስ ተሹሞ ወደዚች ሀገራችን በ፫፻፴፫ (333) ዓ.ም ምሕረት መጣ::

የኢትዮጵያ ነገሥታት **አብርሃና አጽብሐም** ወንጌልን ሊያስተምሯቸው የመጡ ሐዋርያትን ይሰቅሏቸውና ይገድሏቸው ከነበሩት በዕዳን አገሮች በተቃራኒ ከአክሱም አሁን ኤርትራ በተባለችው ሐማሴን ጠቅላይ ግዛት ወደ ከረን አውራጃ አስገደ በቅላ በተባለው ወረዳ የሐባብ ክፍል በሆነችው ቦታ ደረስ ቀርበው ከኢትዮጵያውያን ሕዝባቸው ጋራ በክብር ተቀበሉት:: ነገሥታቱ አብርሃና አጽብሐም ዕለቱን በሰበከላቸው ወንጌልን አምነው ከዚያው አስገደ በቅላ ጽርስፎራ በተባለው ወንዝ ላይ በአባ ሰላማ እጅ ተጠመቁ:: የአሪት ሊቀ ካህናት እንበረምም ከሕዝቡ ጋር ተጠምቆ ኤጲስ ቆጶስነት በአባ ሰላማ እጅ ተቀብቶ ተሾመ::





በዚያ ጊዜም ከነዚህ የተማሩት ፯ ሰዎች ክህነት ተቀበሉ:: እነዚህም ስማቸው 1ኛ ዘአማኑኤል፣2ኛ ማቴዎስ፣ 3ኛ ዕቁብ፣ 4ኛ. ስብሐት ለአብ፣ 5ኛ አሐዱ አምላክ፣ 6ኛ.ተንሥአ ክርስቶስ እና 7ኛ ስምዖን የተባሉ ናቸው:: ‹‹ወተቀበልዎ አብርሃ ወአጽብሐ ነገሥተ አክሱም በውስተ ሀገረ ሲሐት ዘትሰመይ ጽርስፎራ አው ፎራ ለአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ወተጠምቁ በውስቴታ›› በዚያን ጊዜ የተቀበሉት ሰዎች ስም በአብርሃ አጽብሐ ገድል ተጽፎ ይገኛል::የኢትዮጵያ ሕዝብም በደስታ ዕልልታውን እያቀለጠ፣ ነጋሪቱን እየጎሰመ፣ ሠራዊቱ እየተመመ፣ ክርስትናውን ተቀብሎ፣ የወንጌል ብርሃን ተዘርግቶና አብርቶ፣ ወልድ ዋህድ አንድ አካል አንድ ባሕርይ በሚል ከሐዋርያት ተያይዞ የመጣለትን ሃይማኖት አጽንቶ እስከ ዛሬ በዚሁ ተዋህዶ ሃይማኖት ጸንቶ ይገኛል::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፭

ሀገራችን ኢትዮጵያ አስቀድማ በኦሪት እምነቷ በእግዚአብሔር አምላክነት ጸንታ ከመኖርዋም በላይ በአባ ሰላማ የተሰበከላትን ቃለ ወንጌል አምና፤ አባ ሰላማም እንበረም የተባለውን የኦሪት ሊቀ ካህናት ኤጲስ ቆጰስነት ሹሞ፤ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ወንጌልን ያስተምርበት ዘንድ አንድ ክፍለ ሀገር ሰጥቶት ወንጌልን ሲያስተምር ነበር። ከዚሁ ጀምሮ ኢትዮጵያ በክርስቶስ እምነት ጸንታ፤ በልጆቿ መምህራንና በየጊዜው በመጡ ቅዱሳን ዘንድ ወንጌል እየተሰበከላት ስትኖር ነበር። በዘመነ ሐዲስም ምንም እንኳን የራሷ ተወላጆች ኢትዮጵያውያን መምህራን ወንጌልን የሚስተምሯት ቢሆኑም አባ ሰላማ ከእስክንድርያ የጵጵስና ማዕረግ ተሹሞ በመጣላት ልማድ በየጊዜው ከእስክንድርያ ጳጳስ እያመጣች ተዋህዶ ሃይማኖቷን ጠብቃ እስከ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መንግሥት ነበረች።

ሌሎች ባዕዳን ‹‹ኢትዮጵያ ከ፫፻፴፫ (333) ዓ.ም ከአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን ጊዜ ጀምራ እስከ 600 ዓ.ም ድረስ ከሮማ ካቶሊካዊተ ቤተ ክርስቲያን ጳጳሳት በየጊዜው ስታመጣ ኑራ ከዚህ በኋላ ወደ ሮማ ለመሔድ መንገዱ በእስላሞች ስለተከበበ መንገድ አጥታ ጳጳስን ከእስክንድርያ ለማስመጣት ግድ



www.ethiopianorthodox.org



ሆነባትና ሳትወድ ጳጳሳት ከእስክንድርያ ማምጣት ጀመረች። ጳጳሳትን ከእስክንድርያ ማምጣት የተጀመረውም በዚህ ጊዜ ነው›› ብለው ለማታለል የጻፉት ታሪክ ፍጹም አቡሃ ለሐሰት ከተባለ ዲያቢሎስ የመነጨ እንደሆነ ከዚህ መረዳት ይቻላል።

ይህንን ያሉትስ ባዕዳን ኢትዮጵያ መቼ ነው ጳጳስን ከሮማ ያመጣችው? ጳጳሳት አስመጣችበት ካላችሁት ከ፫፻፴፫ (333) ዓ.ም እስከ ፮፻ (600) ዓ.ም ከሮማዊት ቤተ ክርስቲያን የመጡትን የጳጳሳቱን ስም እና የመጡበትን ጊዜ ለይታችሁ ንገሩን ብንላቸውስ ምን መልስ የኖራቸው ይሆን? የላውም እንጂ እውነትስ ቢኖራቸው ይህን ቢነግሩን እንወድ ነበር።

ነገር ግን ይህንን ዕውነታ ከዓለም ታሪክ እንደማያገኙ የተረጋገጠ ነውና ወደ ኢትዮጵያ ሀገራችን እውነተኛው ታሪክ እንመለስ። የኢትዮጵያ ‹‹ወልድ ዋህድ ቃለ እግዚአብሔር›› ብላ እያመነች ሳታቋርጥ እስከ ግራኝ ንጉሥ ዘመን ከሃይማኖቷ ሳትናወጥ ትኖር ነበር። ይህም ዘመን ከልደተ ክርስቶስ አንድ ሺ ፭፻፴፭ (1535) ዓ.ም በፈረንጅም 1543 ነው። እስከዚህ ድረስ የውጭ ሃይማኖት ሳይቀላቀልባት ኑራለች።

ለኢትዮጵያ በአባ ሰላማ የተሰበከላት ክርስቲያናዊ ባህልና ሃይማኖት፤ መለኮትና ሥጋ ተዋህደው ወልድ ዋህድ ፩ አካል ፩ ባሕርይ እንደሆነ አምና አሳምናለች። ኦርቶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን ይህን ጥንታዊ የሆነውን ሃይማኖትዋንም በልጆችዋ ኢትዮጵያውያን መምህራን በየአውራጃውና በየአብያተ ክርስቲያናቱ አስፋፍታለች። ከዚህም ባሻገር ወደ እስክንድርያ እየላከች ከምታስመጣቸው በተጨማሪ ጽንዓ ሃይማኖቷን ሰምተው ለስብከተ ወንጌል የሚረዱ ብዙ ሌሎች ቅዱሳን በየጊዜው መጥተው የአባ ሰላማ ስብከትን መሠረት በማድረግ በኢትዮጵያ ላይ በኦርቶዶክሳዊት ሃይማኖትን ሲሰብኩና ሲያስተምሩ እንደ ነበሩ የታወቀ ነው።

እነዚህም ቅዱሳን የመጡት ከ ፬፻፶ (450) ጀምሮ እስከ ፭፻፳፩ (521) ዓ.ም ባለው ጊዜ ናቸው። የመጡበትንም ጊዜ ከ፫ ክፍለ ዘመናት ለይተን ታሪካቸውን ስንጽፍ በየዘመኑ የነበሩ የነገሥታቱንም ታሪክ ባጭሩ እንገልጻለን።

## ጻድቃነ ንኑም

መጀመሪያ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ብዛታቸው የንጉሥ ሠራዊት የሚያህሉ ቅዱሳን በግብፅ (ምስር) ሀገር አድርገው፤ በሱዳን ሀገር አልፈው ወደ ኢትዮጵያ የደረሱት በኢትዮጵያ



www.ethiopianorthodox.org



በዓፄ ሰልአደባና በዓፄ አልአሜዳ ፫ኛ መንግሥት በ፬፻፶ (450) ዓ.ም የንግሥና ዘመን ሲሆን በምሥራቅ ሀገርም ቴዎዶስዮስ ፪ኛ ንጉሥ በሞተበት በኋላውም የቴዎዶስዮስ እኅቱ ብርክልያ መርቅያንን አግብታ ነግሣ በነበረችበት ጊዜ ነው።

እነዚህ ቅዱሳን ወደ ኢትዮጵያ የመጡበት ምክንያት ኢትዮጵያ ታበጽሐህ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ሲል ዳዊት የተናገረላትን አስበውና ተከትለው እግዚአብሔር የማይለያት ሀገር ይህች ናት ብለው ዓለምን ንቀው መመነናቸው ነው። እነዚህም ቅዱሳን በኢትዮጵያ ላይ ገብተው ወንጌልን በማስተማርና በብሕትውናም በረሃ ለበረሃ በዱርና በገደል ተገድኋቸውን ሲፈጽሙ ስለ ነበሩ ምግባቸውም ሣርና ቅጠል ነበር። በዚያም ዘመን አንድ ቀን ከመካከላቸው አንዱ ባሕታዊ ሌሊት ቆዳ (ዓጽፍ) ለብሶ ከሜዳው ባረክናሃ በሚባል መንደር በሽማዛና ወረዳ ከአከለ ጉዛይ አውራጃ ውስጥ ከሜዳው ሣር ሲበላ ሳለ ባለ ርስት ሰውዬው መጣበት። እርሱም ከብት መስሎት ሣሬን በላብኝ በማለት በጨቤ ወጋውና ይህ ከቅዱሳኑ ወገን የሆነ ባሕታዊ ከበዓቱ ተመልሶ ሞተ። ሲሞትም ኖምኩ (ተኛሁ)ብሎ ተናገረና በሞላው በኢትዮጵያ ላይ በዱርና በገደል በጫካና በጥሻ ተሠማርተው የነበሩት ቅዱሳን ሁሉ አንድነት

ተቀምጦ ነበር። ከዚህ በኋላ ያን ጊዜ በነበረው አባ ኤልያስ በሚባለው የኢትዮጵያ ጳጳስ ተጠርቶ ወደ አክሱም ሔደ።

ከጳጳሱ አባ ኤልያስ ተገናኝቶም፤ ከእሱ ጋር ጥቂት ዘመን ተቀምጦ ነበር። ከዚያም ተነሥቶ በአካለ ጉዛይ አውራጃ ላይ በጉርናጉር በዝባን ቡር በሌሎችም ቦታዎች እየተዛወረ ወንጌልን በመስበክና በጾም በጸሎት በብሕትውናም ሁኖ፤ እየተጋደለ ሲኖር ብዙ መነኮሳትን በየገዳማቱ፤ ብዙ ምእመናንን በየሀገሩ አሳምኖ፤ ገዳማትን አቅንቶ አብያተ ክርስቲያናትን አሠርቶ፤ በምንኩስናም ብዙ መነኮሳት አመንኩሷል። ከእርሱ በምንኩስና ልጅነትን የተቀበሉ ብዙ ቅዱሳንም እስከ ዛሬ ይገኛሉ። ይህ አባ ሊባኖስ በኢትዮጵያ ላይ ያስተማረው ሃይማኖት የአባ ሰላማን ስብከት መሠረት አድርጎ በእስክንድርያዊት ቤተ ክርስቲያን በኦርቶዶክስ ሃይማኖት ነበርና ሲ. ልጆቹ መነኮሳቱም በዚሁ ጸንተው ሲያስተምሩ ይገኛሉ። አባ ሊባኖስ የሞቱ ጊዜ ሲሆን እምባ (ደረቃ) ጠሪቃ ከሚባለው ቦታ በብህትውና ሥራው እየተጋደለ ሕይወቱን ፈጽሞ ጥር ፫ ቀን ዐረፈ።

፪ኛው አባ ዮሐኒ ያልነውም እላይ እንደ ተባለው ትውልዱ ሶርያ ሲሆን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ እስክንድርያ ገብቶ ከአባ ጳኩሚስ የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ተባርኮ ነበር። ኢትዮጵያ





የደረሰውም በ፬፻፶፭ (455) ዓ.ም ነበር። መጥቶም ወንጌልን በኦርቶዶክስ ሃይማኖት እያስተማረ በመላው ኢትዮጵያ ዞናው (ወሬው) ስለ ተሰማ መጀመሪያ ጊዜ ሲመጣ ፱ ሰናሒት በተባለው በሐባብ በከረን አውራጃ ተቀመጠ። እዚያም ሲኖር ደብረ ሲና የሚባለውን ገዳም ሕንፃ አሠርቶ አልፎአል። ያም ቤተ ክርስቲስያን ሕንፃ እስከ ዛሬ ቆሞ ይገኛል።

## ተስአቱ ቅዱሳን

እኒህ በ፫ኛ ጊዜ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት ተስአቱ (ዘጠኙ) ቅዱሳን የተባሉ ናቸው። እነሱም ስማቸው የሚከተለው ነው ፩ኛ ዘሚካኤል (አረጋዊ)፣ ፪ኛ ይስሐቅ (ገሪማ)፣ ፫ኛ ጰንጠሌዎን፣ ፬ኛ ሊቃኖስ፣ ፭ኛ ይምዓታ፣ ፮ኛ ጽሕማ፣ ፯ኛ ጉባ፣ ፰ኛ አፍጼ፣ ፱ኛ አሌፍ ይባላሉ። ትውልዳቸው ግን ከአንድ አገር አይደለም። የተወሰኑት ከሮማ የተወሰኑት ከሶርያ እና ከላእላይ ግብፅ እንደዚሁም ከሌሎች ሀገሮች ነበር።

እነዚህም በእስክንድርያው ሊቀ ጳጳሳት በአባ ቴዎፍሎስ ፈቃድ ከዚሁ ሊቀ ጳጳሳት ተባርከው ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በ ፬፻፸፩ (471) ዓ.ም በዓፄ አልአሜዳ መንግሥት ነው። በሮማም በአንስጣምስ (አንስታትዮስ)፱ኛ ቄሣር ጊዜ ይሆናል። ወደ

www.ethiopianorthodox.org

ኢትዮጵያም መጥተው የአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃንን ትምህርት መሠረት በማድረግ በተዋህዶ ሃይማኖት ሲሰብኩና ሲያስተምሩ ስለ ነበር የራሳቸው ገዳም አቁመው ብዙ ተአምራትና የተጋድሎ ሥራ በማሳየታቸው ከነሱ በምንኩስናም ብዙ መነኮሳት አመንኩሰው የነሱ ልጆች እስከ ዛሬ በየገዳማቸው ይገኛሉ። ከአባቶቻቸው ከ ፱ቱ ቅዱሳን የወረሱትን ተዋህዶ ሃይማኖትም ጸንተውበት ሲያስተምሩ ይኖራሉ።

አንድ አንዶቹ ሰዎች ግን በካቶሊካዊት ሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ተልከው በካቶሊክ ሃይማኖት አስተማሩ የሚሉ የሐሰት ወሬ የሚነዙ አሉ። ይህም በገዳማቸውና በልጆቻቸው መነኮሳት በገድላቸው መጽሐፍና በየምእመናኑ በዙሪያው ያሉትን እስከ ዛሬ የባዕዳን ባህልና ሃይማኖት ይዞ የሚገኝ ወይም የባዕዳን ባህልና ምልክት የያዘ ባለመገኘቱ የሐሰት ስብከት መሆኑን ልንረዳው እንችላለን።





## ምዕራፍ ፯

## ዓፄ ካሌብ

ንግባዕኬ ኀበ ጥንተ ነገር ወደ ጀመርነው ነገር እንመለስ። ከቀድሞ ጀምሮ የዓረብ ሀገር ገዥነት በኢትዮጵያ ነገሥታት ሥልጣን በታች ስለ ነበረ በዓፄ ካሌብ መንግሥት ጊዜ በ፬፻፺፭ (495) ዓ.ም (ዱ ኖባስ ዙዋስ) ወይም ፊንሐስ አይሁዳዊ የተባለ ሰው በዓረብ ሀገር በኀይል ገብቶ ሊገዛ ጀመረ። የአይሁድን ሃይማኖት ተቀብሎ ለማስፋፋትም ስለ አሰበ የየመን ሀገር ክርስያኖችን እያሳደደ አብያተ ክርስቲያናቱን አቃጠለ። (ገፍስቲን) ዩስጢኖስ የተባለ የቁስጥንጥንያ ንጉሥ በጊዜው የመን የኢትዮጵያ መንግሥት ግዛት በመሆንዋ ወደ እስክንድርያ ፓትርያርክ ሊቀ ጳጳሳት አባ ጢሞቴዎስ ልኮ በየመን ሀገር በሚኖሩ ክርስቲያኖች ላይ የተሠራውን ግፍ ሥራ እንዲበቀል ለመለመን የልመና ደብዳቤ ለኢትዮጵያ ንጉሥ እንዲጽፍለት አሳሰበው።

ፓትርያርኩም ደብዳቤ ጽፎ ለዓፄ ካሌብ ባደረሰላቸው ጊዜ ዓፄ ካሌብ ክርስቲያኖችን ለማጥፋት የተጀመረውን እልቂት ለማስወገድ ጦር አዘጋጁ። ጦሩም በዓረብ ሀገር ላይ ለመዝመት ባሕረ ኤርትራን የሚሻገሩበት መርከቦች አስፈለገው። በዚያን

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜም በዘይላ የኢትዮጵያ ወደብ ላይ ቆመው የነበሩት ፸ (70) ታላላቆች ፩፻ (100) ታናናሽ መርከቦችን የግሪክ መንግሥት የቁስጥንጥንያ ንጉሥ የነበረው ዩስጢኖስ የመንግሥቱ የዓፄ ካሌብን ሠራዊት እንዲያሻግሩ ትእዛዝ አስተላለፈላቸው ዐፄ ካሌብም ራሳቸው ከአሠሯቸውም ፻፺፩ (191) መርከቦች ጋር በ ፫፻፷፩ (361) በሆኑ መርከቦች ላይ ሠራዊታቸውን አሣፍረው ተሻገሩ:: ዓፄ ካሌብ ከአክሱም ቤተ መንግሥታቸው ሲነሱም አስቀድመው ከአባ ጰንጠሌዎን ዘንድ ሄደው የዓረብ ንጉሥ በየመን ሀገር ክርስቲያኖች ላይ የተደረገውን ግፍና እልቂት ነግረው የክርስቲያን ደም ለመበቀል እዘምታለሁ እና ጸሎት አድርግልኝ ሲሉ ለምነዋቸው ነበር:: አባ ጰንጠሌዎንም ቡራኬውን ሰጥቶ ‹‹ኢትፍራህ እግዚአብሔር ምስሌከ እስመ አንተ ትመውዕ ለንጉሠ ዛፋር እግዚአብሔር ካንተ ጋራ ነውና ፊንሐስ የዛፋርን ንጉሥ አንተ ድል ታደርገዋህ›› ብሎ ትንቢት ተናገረላቸው::

ዓፄ ካሌብም በጉልበታቸው ተደፍተው አቡነ ዘበሰማያት ተቀብለው በዚሁ ትንቢት በመተማመን ተጽናንተው ባሕረ ኤርትራን ተሻገሩ:: የየመን ሀገር ንጉሥም በብዙ ግርማና በብዙ ኃይል መምጣታቸውን በሰማ ጊዜ ያፄ ካሌብን ጦር ከፍ ባለ አመጣጥና ግርማዊነት መሆኑን አስተውሎ ከጀግንነት





ሞያው ይልቅ የተንኮል ሥራ ያውቃልና ምንም ሳይዋጋ ወደ ኋላ ሸሽቶ፤ ታዛዥነቱን አስታውቆ፤ በሰላማዊ መንገድ የዓፄ ካሌብን ቀጣ አቀዘቀዘው:: ዓፄ ካሌብም ግዛታቸውን በየመን ሀገር አደላድለው ሴም ያፋ የተባለውን የሀገሩን ባላባት ሹመው ባገሩ ላይ ተቀማጭ ጦር ትተው በ፭፻፲፯ (517) ዓ.ም ወደ ቤተ መንግሥታቸው አክሱም ተመለሱ::

ይህም ዘመቻ ኢትዮጵያ በዚያን ጊዜ ትልቅነቷ የነበረው በየብስ ጦር ብቻ ሳይሆን በባሕር ላይ የጦር ኃይል እንደነበራት ያስረዳል:: ዓፄ ካሌብ እንደተመለሱም እንደገና ፊንሐስን (ዱናባስን) ሹመው የተውት ሴም ያፋን ጦር ወግቶ በዛፋር የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናት አቃጠለ:: በናግራን ከተማ ያሉት ምሽጎች ጠንካራ ከመሆን በላይ ሕዝቡ ተከላክሎ እናስገባም ሲሉ ቢበረቱበት በጉልበት መግባት ቢያቅተው ባታላይነት ሊገባ አሰበ:: በከተማይቱ ያሉትን ሕዝብም መብታቸውን እንደማይነካ የመሐላ ቃል ሰጣቸው:: ሕዝቡም እንግዲያ መብታችንን አልነካም ሲል መሐላውን ከሰጠን ብሎ እንዲገባ ሊፈቅዱ ቢከጅሉ አባ ጊሩት የተባለው ኤጲስ ቆጶሳቸው አይሆንም አታስግቡት ቢላቸው ቃሉን እንስማም ብለው አስገቡት::

www.ethiopianorthodox.org

## የናግራን ክርስቲያኖች

ፊንሐስም በገባ ጊዜ በናግራን ከተማ ያሉትን ክርስቲያኖች በኅዳር ፳፮ ቀን ፭፻፳፪ (522) ዓ.ም በሰይፍና በእሳት አስፈጃቸው። በዚሁ ጊዜ የናግራን ከተማ ክርስቲያኖች እስከ ሕፃናቱ ሳይቀር በሰማዕትነት ‹‹ነአምን በእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ›› በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ እናምናለን እያሉ ተሰይፈው ሞቱ።

ስለ እነሱም ቅዱስ ያሬድ እንዲህ ይላል ‹‹ብሐኪ ኦ ዓባይ ሀገር ሀገረ ናግራን ሀገረ ነጎድጓድ ሀገረ እግዚአብሔር አንተ ተሰመይኪ ገነተ ደሞሙ ለሰማዕታትኪ ውኅዘ ከመ ማይ ድምፀ ነጎድጓዶሙ በጽሐ እስከ ሰማይ›› እያለ በድጓው መዝሙሩ በብዙ አጋኖ ያነሣቸዋል። በሐድረሞትም እንዲሁ ብዙ ክርስቲያኖች ፈጅቶ ብዙ አብያተ ክርስቲናትን አቃጠለ። ፊንሐስ (ዱኖባስ) ሁለተኛም በክርስቲያኖች ላይ የሠራውን ግፍ ዓፄ ካሌብ በሰሙ ጊዜ እንደገና አዲስ ጦር አዘጋጅተው ኤርትራ ባሕርን ተሻግረው ዓረብ ሀገር ድረስ ሄዱ። ጦራቸውንም ከሁለት ከፍለው አንዱ ክፍል ወደ ማኻል ሀገር ገፍቶ ሲገባ ሁለተኛው ክፍል ፊንሐስን እየተከታተለ ፋታ ሳይሰጥ ወጋው። ፊንሐስም የጦር ሠራዊቱ እየተጨፈጨፉ





ማለቃቸውን ዐዩና ተስፋ በቈረጠ ጊዜ ከፈረሱ ጋራ ከባሕር ተወርውሮ ሞተ።

ከዚህ በኋላ ዓፄ ካሌብ ሀገሩን ወደ ሰላማዊነት መልሰው፣ አብያተ ክርስቲያናትንም አሠርተው የሀገሩን ጸጥታ ለመጠበቅ በቂ የሆነ ጦር አስቀመጡበት። ሀገረ ገዢም ይሆን ዘንድ አብርሃም የተባለ ኢትዮጵያዊ በዚያው ሀገር እንደራሴያቸውን ሾመው ወደ አክሱም ከተማ ቤተ መንግሥታቸው ተመልሰው ገቡ።

ዓፄ ካሌብ በዚሁ ሁለት ጊዜ በፈጸሙት ዘመቻ ዝናቸውና ስማቸው በዓለም ሁሉ ናኘቷል። ይህም የሆነው በ፭፻፳፫ (523) ዓ.ም ነው። ዓፄ ካሌብ የሾሙት እንደራሴያቸው አብርሃምም ሰንዓ የምትባለውን መናገሻ ከተማው አድርጎ ተቀመጠ። ከዚያም ያሠራው የቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ በሚያስደንቅ ሁኔታ ስለ ተሠራ የዚያን ጊዜ የእስላም ሃይማኖት ሳይቀበሉ በጣኦት ያመልኩ የነበሩት ዓረቦች በመካ ከተማ ከነበረው በጣም ከታወቀው ካባ (ቀባ) ከተባለው የጣዖት መቅደሳቸው ይልቅ ይህ ቤተ ክርስቲያን በውበትና በግርማ በልጦ ስለ ሚታይ ወደሱ ለመሳለም የሚጎርፈው ሕዝበ ክርስቲያንም ቁጥሩ በጣም ከፍ ያለ በመሆኑ የሕዝቡ መንፈሳቸው ወደ ክርስትና መሳብ ጀምሮ ነበር ይባላል።

www.ethiopianorthodox.org

# የአፍ ታሪክ

## ምዕራፍ ፰

ከዚህም ስለ ዓፄ ካሌብ የአፍ ታሪክ እንጽፋለን:: ዓፄ ካሌብ **ዘእስራኤልና ገብረ መስቀል** የተባሉ ፪ ልጆች ነበሯቸው እነዚህንም ፪ቱ ልጆቻቸው ከዓረብ ሀገር ከተመለሱ በኋላ ታናሹ ገብረ መስቀል ከጋሸ ወንዝ ርባ ዓንሰባ ጀምሮ ኤርትራና ትግሬን ይዞ እስከ ማዳካስካር እስከ ህንድ ውቀያኖስ የኢትዮጵያ ደቡብ ላይ አክሱም ከተማው አድርገው አነገሡት:: ትልቁ በኩር ልጃቸው ዘእስራኤልም በኤርትራ ሰሜንና ምዕራብ በባሕር ማዶ እስከ ዓረብ ሀገር ያለውን ግዛታቸው ከተማውም ከሰላ አድርገው አነገሡትና ዓፄ ካሌብ ዓለምን መንነው ዘውዳቸውንና ልብሰ መንግሥታቸውን በኢየሩሳሌም በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መቃብር ለመታሰብያ እንዲሆናቸው ወደ ኢየሩሳሌም ልከው ሰጥተው ሲያበቁ ገዳም ገብተው በአባ ጰንጠሌዎን እጅ መነከሱ:: ምንተኑ አዓሥዮ ለእግዚአብሔር ይህን ሁሉ በእንተ ኩሉ ዘገብረ ሊተ፤ እግዚአብሔር





ስለአደረገልኝ ምን ውለታ እከፍለዋለሁ? እያሉ በዋሻ ውስጥ ዘግተው በጾም በጸሎት በስግደት ተወስነውም ተቀመጡ::

ከዚህ በኋላ የዘእስራኤል መኳንንት ‹‹አንተ በኩር ልጅ ትልቅ ሳለህ አባትህ አንተን ከበረኻ ላይ አንግሠውህ ታናሽ ወንድምህ ግን በለማ ሀገርና ጽላተ ሙሴ ባለችበት ላይ ያነገሡት ማድላታቸው አይደለም?›› ቢሉት ዘእስራኤልም እውነታቸው ነው ሲል ተነሥቶ ከወንድሙ ከገብረ መስቀል ጋር ለመዋጋት ጦርነት ተሰለፈ:: ዓፄ ካሌብም የሆነውን በመንፈስ ቅዱስ አውቀው ከበዓታቸው ወጥተው ሁለታቸውን ጠሯቸው::

ሁለቱም ወደ ዓፄ ካሌብ በመጡ ጊዜ ‹‹በከንቱ የክርስቲያን ደም አታፍሱ ብትፈቅዱ አንዳችሁ በሥውር አንዳችሁም በግልጥ እንዲትገዙ እግዚአብሔርን እለምነዋለሁ:: ዘእስራኤል ትልቅ ነህ ሠረገላ ጽዮንና በሥውር መግዛት ትወዳለህን ወይስ ታቦተ ጽዮንንና በግልጥ መግዛትን ትመርጣለህ?›› ብለው ቢጠይቁት ከመኳንንቱ ጋር መክሮ ‹‹ሠረገላ ጽዮንና በሥውር መግዛትን›› እመርጣለሁ ሲል መልስ ሰጠ::ወዲያው ከነሠራዊቱ ከነልጆቻቸውና ከነምሽቶቻቸው ከነሠረገላ ጽዮን ሁኖ ተሠወረ:: ሠረገላውም በምኒልክ ጊዜ ጽላተ ሙሴን ይዘውባት የመጡት ሠረገላ ነበረች::

www.ethiopianorthodox.org

ዓፄገብረመስቀልም ከጽላተ ሙሴ መኖሪያ አክሱም ከተማቸውን ይዘው በግልጽ ፭፻፴፰ (538) ነገሡ ሲሉ በአፍ ታሪክ ይተርካሉ::

ይህንንም ለመረዳት እስከ ዛሬ በድንገት የሥውርን ነገር ሲደቀንብህ ‹‹እስራኤል እንቶቻችን ናቸው›› እየተባለ የሚነገር ስለሆነ የሚመስል ነገርና የአፍ ታሪክ ሁኖ እናገኘዋለን:: በትግርኛም ደቂ እስራኤል የሚለው ይታወሳል::

ዓፄ ካሌብም ይህን ሁሉ የሠሩ ስለ ክርስቲያን ሃይማኖት ሲሆን ሃይማኖታቸውም ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እንደነበረ የሚያስረዳን ዩስጢኖስ የቁስጥንጥንያ ንጉሥ ስለ የመን ክርስቲያንን ለመርዳት ለዓፄ ካሌብ ሲልክላቸው በእስክድርያው ሊቀ ጳጳሳት በአባ ጢሞቴዎስ በኩል የልመና ደብዳቤ መላኩ በሃይማኖት ለሊቀ ጳጳሳቱ የሚመስሉት ስለሆነ ነው እንጂ የሌላ ሃይማኖት ቢኖሩስ? በሮማ ሊቀ ጳጳስ በኩል ወይም በርሱ በላከላቸው ነበር፤ ዓፄ ካሌብ ካቶሊክ አለመሆናቸውን ይህ ብቻ ሊያስረዳን ይችላል:: የሚበጀውም ስለሃይማኖታቸው ባዕዳን የሚሉትን አለ መስማት ነው::





## ምዕራፍ ፱

ከረጅም ዘመናት በኋላ ከ፲፫፻፬ (1304) እስከ ፲፫፻፴፩ (1331) ዓ.ም በ**ዓፄ ዓምደ ጽዮን** ጊዜ ልዩ ልዩ መጻሕፍት ከዓረብ ከዕርዕ ወደ ግዕዝ ማስተርጎምና አንድ አንድ የሥልጣኔ ሥራ ለመስራት ተጀምሮ ነበር:: እነዚሁም መጻሕፍት የሚበልጡት ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተተረጎሙ ናቸው:: ከነሱም አንድ አንድ ለመጥቀስ በዮሴፍ ወልደ ኮርዮን የተደረሰ ዜና አይሁድ የሰዓታት መጻሕፍት ሌሎችም በያይነቱ መጻሕፍት ማየት እንችላለን:: ገድለ ሰማእታትን ከዓረብኛ ወደ ግዕዝ የተረጎመው ሚካኤል ካህን ግብፃዊ ነው:: ፍትሐ ነገሥት የተጻፈው ወደ ግዕዝ የተተረጎመውም ክብረ ነገሥትና የኢትዮጵያ ታሪክ መጻፍ የተጀመረውም በዚህ ጊዜ ነው::

ከዓፄ ዓምደ ጽዮን በኋላ ልጃቸው ዓፄ ሰይፈ አርዕድ የተባሉ በነገሡ ጊዜ ስለ ሃይማኖት ብዙ ሠርተዋል:: ከሠራቸውም አንዱ ትልቅ ሥራ ወደ ግብፅ ያደረጉት ዘመቻ ነው:: በ፲፫፻፶ (1350) ዓ.ም በግብፅ ሐነፋይ የተባለ ንጉሥ በነበረበት ጊዜ አባ ማርቆስ የተባለውን የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት የቤተ ክርስቲያን ግብር አምጣ ብሎ አሠረው:: ይህንንም ዓፄ ሰይፈ አርዕድ ሰምተው እሱን ለመውጋት



www.ethiopianorthodox.org

ሠራዊታቸውን አስከትተው፤ ከመንዝ ተነሥተው ወደ ትግሬ ደረሱ። ያን ጊዜ ከነበሩት ባሕታዊ ከአቡነ መድኃኒነ እግዚእ ዘንድ ለመባረክ ወደ ደብረ በንኮል ወጡ። የእስክንድርያውን ሊቀ ጳጳሳት መታሠሩንና እሱን ለማስፈታት ወደ ግብፅ ዘመቻ መነሣታቸውንም ነግረው ተባረኩ። ጉዞዋቸውንም ቀጥለው ሄዱና ላዕላይ ግብፅ በደረሱ ጊዜ ከግብፅ ንጉሥ ሐነፋዊ ጋር ተዋግተው ድል አደረጉ። ሐነፋዊም ዕርቅ ለምኖ ሊቀጳጳሳቱን ፈትቶ ለወደፊቱም ክርስቲያኖችን እንዳይበድላቸውና እንድዳይገፉቸው መሐላ አድርጎ ተዋዋሉ። በዚሁ ውል ሊቀ ጳጳሳቱ አባ ማርቆስም ወደ ሹመቱ በተመለሰ ጊዜ ዓፄ ሰይፈ አርዓድ በደኅና በድል አድራጊነት ወደ ሀገራቸው ኢትዮጵያ እ ተመለሱ። ይህ ታሪካቸው በጥቅምት ፳፩ ስንክሳር መጽሐፍ ይገኛል።

ከዚህ በኋላም በ፲፫፻፺፭ (1395) ዓ.ም በ**ዓፄ ዳዊት** ፩ኛ (ቀዳማዊ) መንግሥት ጊዜ የነበረው የግብፅ ንጉሥም በክርስቲያኖች ላይ እንዳይበድሉ ከዓፄ ሰይፈ አርዓድ ጋር የተዋዋሉትን የዕርቅ መሐላን አፍርሶ አባ ዮሐንስ የተባለውን የእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳት ግብር አምጣ ሲል አስሮታል የሚል ወሬ ዓፄ ዳዊት በሰሙ ጊዜ ሠራዊታቸውን አስከትለው ግብፅን (ምስርን) ለመሔድ ተነሱ። ተነሥተውም አልቀሩ ሱዳን ሀገር



www.ethiopianorthodox.org



ሲደርሱ እስከ ግብፅ ስንሔድ ከመንገዱ ርቀትና በበረሃ ሠራዊቱ በድካምና በበሽታ ከሚያልቅ እዚሁ የኢትዮጵያን ውኃ የዓባይን ወንዝ ግብፅ የሚጓዘውን መገደብ ይሻላል። ብለው የሚጓዘውን የዓባይ ውኃ ሠራዊቱ እንዲገድቡት አድርገው ውኃው ወደ ኋለ ተመልሶ ወደ ሌላ በረሃ እንዲሄድ አደረጉ። በዚሁ ነገር ግብፅ የዓባይን ውኃ በማጣቱ ፫ ዓመት በረኀብና በጥማት ተጨንቃ ከመከራና ከችግር ላይ ወደቀች። በዚህ ጊዜ የግብፅ ንጉሥ ሊቀ ጳጳሳቱ አባ ዮሐንስን ከእሥራቱ ፈትቶ ከእንግዲህ ወዲህ ለወደፊቱ በግብፅ የነገሡ ነገሥታት ክርስቲያኖችን እንዳይገፉና እንዳያጠቁ በአብያተ ክርስቲያኖችም ግብር እንዳያስከፍሉ የሚል ውል ከአባ ዮሐንስ ጋር ተዋውለው ምለው ሲያበቁ ውኃው እንዲለቀቅልን ሲል ዓፄ ዳዊትን ሊቀ ጳጳሳቱን እንዲለምነው ገጸ በረከትንም እንዲልክላቸው አድርገህ ለምነው ሲል ለመነው።

ሊቀ ጳጳሳቱም ከታሠረበት መፈታቱን የቡራኬ ቃልም ካለበት ደብዳቤው ጋር ለኢትዮጵያ በረከትና የእምነቷ ምልክት ለዘለዓለም የሚሆንና የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል የተሰቀለበት ከ፬ቱ ሊቃነ ጳጳሳተ ሲከፈል ለእስክንድርያ መንበር በክፍሉ የደረሰውን ግማደ መስቀሉና ከለሜዳውን ሰፍነጉንና የኩርዓተ ርእሱ ሥዕል አድርጎ ላከላቸው።

የግብፅ ንጉም ብዙ ወርቅና ብር በያይነቱ ሽልማትንም አድርጎ የወዳጅነት ምልክት ለዓፄ ዳዊት ላከላቸው:: ዓፄ ዳዊትም ሊቀ ጳጳሳቱ የላከላቸውና ንጉሡ የላከላቸውን በማመስገን ተቀብለው ሲያበቁ ሊቀ ጳጳሱ የላከላቸውን ግማደ መስቀሉን ተቀብለው ንጉሡ የላከላቸው ወርቅና ብር ግን አመስግነው ‹‹ወርቅ ሞልቶኛል አያስፈልገኝም›› ብለው ለንጉሡ መለሱለት::

ግመደ መስቀሉንም ጌታ በራዕይ ሌሊት መጥቶ ‹‹አንብር መስቀልየ በዲበ መስቀል መስቀሌን በተመሳቀለ ቦታ አስቀምጥ›› ብሎ ተናገራቸው መሰረት በዚሁ ቦታ እንዲቀመጥ አደረጉ:: ይህም ቦታ በወሎ አውራጃ ግሼን በሚባለው ቦታ በከበሬታ ተቀምጦ ይገኛል::

ዓፄ ዳዊትም የዓባይን ውኃ እንደቀድሞው እንዲፈስ ለቀቁላቸውና ያንን ቦታ ውኃው ተቋርጦበት ስለ ነበረ ካርቱም ተባለ:: ካርቱም ማለትም ተቈረጠ ማለት ነው:: ከረቶ እንዲል ትግሬ ክሩት ማለት ነው:: በትግረኛ ቈረጠ ሲል ከረተ እንዲል:: የዓፄ ካሌብንና የዓፄ ገብረ መስቀልን ታሪክ ለመጻፍ ያስገደደኝ ኢትዮጵያ ሀገራችን ነገሥታቷ ከዕገሌ ሀገር ክረስቲያኖች ተጠቁ ሲባል ባሕሩን ተሻግረው፤ በረሃውን ጥሰው፤ ውኃውን መልሰው፤ ሠራዊታቸውንና ሰውነታቸውን መሥዋዕት



www.ethiopianorthodox.org



አድርገው፤ ስለ ሃይማኖታቸው ሲጥሩና ሲደክሙ በነበሩበት ጊዜ የሮማ ነገሥታት ክርስቲያንን በመግደልና ጣዖታትን በማክበር የአረማዊነትን ሥራ እየሠሩ እንደ ነበሩ ለማሳወቅ፤ ኢትዮጵያም ፊት በኦሪት ሕግ ከልደት በኋላም በአባ ሰላማ ከእስክንድርያ የተቀበለችው ከሐዋርያት ተያይዞ በቆየው በተዋህዶ ሃይማኖት ጸንታ መኖሯን፤ የነገሥታቷም ብርታትና ገናንነቷን ታሪክ ሲቃውንቷና ታላላቆችዋንም ቢያውቁት የኢትዮጵያ ወጣቶችም ብልሖች ከመሆናቸው በላይ ይህን የሃይማኖታቸውን ጽናት አውቀው በሃይማኖት የአባቶቻቸው ተከታዮች እንዲሆኑ ስል ነው::

ከዚህ ቀጥለን የግራኝንና የፖርቶጊዞችን አመጣጥ እንገልጣለን::

## ምዕራፍ ፲

ኢትዮጵያ ሀገራችን በተዋህዶ ሃይማኖት ጸንታ በኢትዮጵያውያን መምህራን እየተሰበከላት ስትኖር ቆይታ ከዓፄ ልብነ ድንግል መንግሥት ደረሰች:: የዓፄ ልብነድንግል ዘመንም ሰላማዊ ነበር:: ለ፳፱ ዓመታትም ጠላት ሳይነሳበት ስለ ቁየ የሕዝቡ ሀብት ስለበረከተ እርሻም በማስፋፋቱ የተነሳ ፺፻፻ (900-000) የሚሆነው ሠራዊታቸው እንደዛሬ የጦርነት ትምህርት ያልነበረው ነበርና ‹‹ የውጊያው ልምምድ ሊጠፋብን ነው ቦካን ጦር አውርድልን እያሉ›› ግፍ ሲያወሩ በፈረስ ጉግስም እርስ በርሳቸው ሲጫወቱ የገዛ ግምባቸውን በጦር እየወጉ ግንቡን እያፈረሱ ይውሉ ነበር:: ስለዚሁም ምክንያት ከተማው ቦካን ተባለ:: አፄ ልብነ ድንግልና ሕዝቡ እንደ አረሚ/አህዛብ ልማድ የፈረሳቸውን ግንባር የቦረንትቻ እየቀቡ፡ ትንባሆንም እያጤሱ ሲኖሩ ይህም አልበቃ ብሎ ለየአድባራቱ ትልቅ ትልቅ ጫን ዕጣን ልከው ‹‹አባቶቼ ይህን እያጠናችሁ ጦር አውርድልን ብላችሁ ወደ እግዚአብሔር ለምኑልኝ›› ብለው ወደ ቤተ ክህነት ላኩ::

በዚሁ ጊዜ የቤተ ክህንት ወገን የሆነ ሁሉ አዘነ:: ጳጳሱ አባ ስምዖን፡ ዕጨጌው አባ ዮሐንስ ድራግ ማሰሬ ዘመለኮት ዓቃቤ



www.ethiopianorthodox.org



ሰዓት ቃለ ዓዋዲ የተባሉ ሊቃውንት ወደዓፄ ልብነ ድንግል ሄደው ይህን ማድረግ አይገባምና አታድርጉት ሲሉ ቢነግሯቸው እንኳን ሊሰሙ ፊታቸውንም ነሥተዋቸው ተመለሱ::

ዓፄ ልብነ ድንግል መነኮሳቱና ቤተ ክህነቱ ‹‹የማይገባውን ነገር በመሥራትዎ እግዚአብሔር ይቆጣዎታል›› ብለው ቢመክሯቸው ኤልያስ አክአብንና ኤልዛቤልን ተው ብሎ ቢመክራቸው አንሰማም ብለው ፫ ዓመት ከመንፈቅ በረኃብ ሕዝቡን እንዳሳለቁት ዓፄ ለብነ ድንግልም አልሰማም በማለታቸው እግዚአብሔር አዝኖ **ግራኝ መሐመድን** አስነሳባቸው:: አብያተ ክርስቲያናት ተቃጠሉ:: መጻሕፍት ተቆነጻጽለው ጠፉ:: ምእመናን እንደ በግ ታረዱ:: ደማቸው እንደ ውኃ ፈሰሰ:: አጥንታቸው በየወደቀበት ተከሰከሰ::

ዓፄ ልብነ ድንግልም በሠሩት ጥፋት እግዚአብሔር ግራኝን እንደ አስነሳባቸው ስላወቁ እየተዋጉ ሲሸሹ ሱባኤ እየገቡ በሠራሁት ኃጢአት ይቅር በለኝ እያሉ አልቅሰው አዘኑ:: እግዚአብሔርንም ደጅ እየጠኑ እግዝእትነ ማርያምንም ከልጅሽ ከወዳጅሽ አማልጂኝ እያሉ ቢለምኗት ከዕለታት አንድ ቀን በራእይ ከመልአኩ ቅዱስ ራጉኤልን ከሰማዕታት ቅዱስ ጊዮርጊስን ከጻድቃን አቡነ ተክለ ሃይማኖትን አስከትላ ተገለጠችላቸው:: ‹‹እኔን ሳትወደኝ ለምን ስሜን ታነሳለህ

አሁንም ጸሎትህን አልሰማም ያባትህን የወዳጄ የናዖድን ትእዛዝ አፍርሰሃልና ልጄ በዳዊት አፍ አድሮ የኃጢተኛ ጸሎት አልቀበልም ያለውን አልሰማህም›› ብትላቸው መልሰው ‹‹የኔን ኃጢአት ሳታስቢ ያባቶቼ የዘርአያዕቆብንና የናዖድ ታማኝነት አስበሽ ከልጅሽ ከወዳጅሽ አማልጅኝ›› ሲሏት ምሕረት ለማዷ ነውና ‹‹እንግዲህ በንፍስህ ደስ ይልሃል በሥጋህ ግን ታዝናለህ በስደት ትሞታለህ አሁንም ንስሐ ግባ ልጄ ከናዖድ ከዘርአያዕቆብ መንግሥት እንደይጠፋ አድረጓልና፡፡
የልጅ ልጆችህም እንደነናዖድ የኔን ኪዳን ጠብቀው ቢኖሩ መንግሥታቸው ይጸናል፡፡ ባይጠብቁ ግን መንግሥታቸው ትጠፋለች፡፡ ሀገራቸውም ለአሕዛብ ትሰጣለች›› አለቻቸው፡፡
ከዚህም በኋላ ዓፄ ለብነ ድንግልን ግራኝ መሐመድ እያባረራቸው ባደረጉት ጥፋት ንስሐ ቢገቡ መልአኩ ራጉኤል በራዕይ መጥቶ ‹‹አንተ በስደት ትሞታለህ ከልጆችህም ገ ይነግሣል (ገላውዴዎስ) ፊ. ይመውት (ፊቅጦር) ሚ ይሠየጥ (ሚናስ) ይሸጣል ያ ይነብር (ያዕቆብ) ይኖራል፡፡›› እያለ ነገራቸው፡ እንዳለውም ዓፄ ልብነ ድንግል በስደት ሞቱ፡፡
ከዚህ በኋላ ግራኝ መሐመድ አብያተ ክርስቲያናትንና ምእመናንን ባጠፋ ጊዜ የኢትዮጵያን ሕዝበ ክርስቲያን ለመርዳት በዚያን ጊዜ በዓለም ላይ የታወቀ ኃይለኛ የነበረው





የፖርቶጊዝ መንግሥት ስለነበረ ዓፄ ልብነ ድንግል በላኩት መሠረት አነሣሥቶ ግዛቱ ከነበረው ህንድ ፬፻ 400 የፖርቶጊዝ ሠራዊት ከህንድ ተነሥተው ዶም ክርስቶፍ በተባለው (ካፒቴን) የጦር አዛዥነት እየተመሩ መጡ፡፡ በዚያን ጊዜ የፖርቶጊዝ ንጉሥ በነበረው በ፫ኛ ዮሐንስ ትእዛዝ በመርከብ ሁነው በህንድ ውቅያኖስ በባሕረ ኤርትራ አድርገው ምጥዋ ሲደርሱ በድኝኖ ወደብ ወጡ፡፡ በሐማሴን አድርገው ምጥዋ ሲደርሱ በድኝኖ ወደብ መጡ የሐማሴን ኤርትራ ሀገረ ገዥ ባሕር ነጋሽ ይስሐቅ የተባለ ባላባት ኢትዮጵያን ለመርዳት መምጣታቸውን ስላወቀ ወደ ምጥዋ በቅሎዎቻቸውን ግመሎቻቸውን ፈረሶቻቸውን ይዞ ሂዶ ከብዙ ሠራዊት ሁኖ ተቀብሎ፡ መድፎቻቸውንና መሣሪያቸውን ሁሉ በግመሎች ላይ ጭነው ባሕረ ነጋሽ እየመራቸው መጡና ወደ ድባርዋ ገቡ፡፡
በመጡ ጊዜ የተደረገላቸውን ከነሱ ጋር በመጣው ፖርቱጊዛዊ ሚጉኤል ካስታንሆዞ የተባለው የዚያን ጊዜ ከጻፈው ታሪክ ያገኘነውን የደረሱበትን በታዎችና ያገኙትን በየጊዜው የገጠማቸውን ደስታና ችግር ከዚህ በታች በጥቂቱ እንገልጻዋለን፡፡

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፲፩

## ፖርቶጊዞች አመጣጥ

፬፻ 400 የፖርቶጊዝ ወታደሮች በጦር አለቃቸው ዶም ክርስቶፍ ዳጋማ መሪነት ከህንድ አገር ተነሥተው ሲመጡ በፈረንጅ በዘጠነኛ ቀን በሉልዮ (ዮሊ) ሐምሌ ወር በ1541 ዓ.ም በኢትዮጵያ ሐምሌ ፳፲ ቀን ፲፭፻፴፫ ዓ.ም ቅዳሜ ከእኩለ ቀን በኋላ ምጥዋ ገብተው ጨው በሚገኝበት ቦታ አሁን ግራር በሚባለው ይመስላል አደሩ። የጉዞዋቸው ጸሐፊ የነበረው ዲ.ክስታንሆዞ በጽሑፉ እንዲህ ይላል። ‹‹በነጋታው ሐሩሩ ሙቀቱ ስለ በረታብን ከዚህ ዓርፈን ዋልን። እሁድ ማታውን ተነሥተን ጣፋጭ ውኃ ካለበት ቦታ ደረስን። ይህም ቦታ ማይ አጣል የሚባለው ይመስላል።

ከዚህም ተነሥተን ስንጓዝ ቦታው ሙቀታም በመሆኑና ውኂም ያነሰበት ቦታ ስለሆነ በቀን አርፈን እየዋልን ሌት እየተጓዝን ፯ ቀኖች ከተጓዝን በኋላ አንድ ትልቅ ተራራ ስለገጠመን ከጧት እስከ ማታ ስንሄድ ውለን ወጣነው።

ከተራራው በላይ በደረስን ጊዜ በጣም ጥሩ አየርና ቀዝቃዛ ውኃ ያለበት ለፊ ሜዳ የሆነውን ብርዳም ሀገር አገኘን። በዚሁ በግራኝ ትእዛዝ ዓረቦች ያፈረሱት በጣም ትልቅ ቤተ ክርስቲያን ስለ ነበረ ከእርሱ አጠገብ ፱ ቀን ዕረፍት



www.ethiopianorthodox.org



እንድናደርግ ዶም ክርስቶፍ አዘዘን። ሀገሩም በሞላው ጠፍቶ ነበር። ከዚያም ሁነን የምጥዋ ባሕርን ለማየት እንችል ነበር›› ይላል።

ይህም ዓርብ ረቡዕ የተባለውን ወጥቶ ስለ ሚገኝ በአኳኋኑ ከአሥመራ ውጭ ምጥዋ መንገድ የሚገኘው ቤት ጊዮርጊስ የሚባለው ሳይሆን አይቀርም ልንለው እንችላለን።

ካስታንሆዞ ቀጥሎም ‹‹ከ፱ ቀኖች ዕረፍት በኋላ ከዚሁ ተነሥተን ብርዳም በሆነው ሀገር ቀዝቃዛ ውኃም የሞላበትን ሀገር እየተሻገርን ፫ ቀን ተጉዘን ከአንድ ትልቅ ከተማ ባጠገቡ ትልቅ ወንዝ ጎርፍ የሚሄድበት ከፈሳሽ ውኃ ዓሣ ያለበት ደረስን።

ይህም ከተማ ከኛ ጋር የነበረው ያገር ገዢው የባሕረ ነጋሽ ከተማ ነበር። በዚሁም ወንዝ ዙርያ ብዙ ገጠሮች አሉ። በዙርያውም ብዙ መንጋ ከብት ይገኙባቸዋል።›› ሲል ጽፈቸዋል።

ይህም ከተማ ድርባዋ ወንዙም የመረብ ወንዝ ሊባል ይችላል። ድባርዋም የጥንት ከተማ መሆኑ በዚህ ይታወቃል። ካስታንሆዞ ቀጥሎም ከከተማው ስንደርስ ዶም ክርስቶፍን ለመቀበል ወደ ከተማው ብዙ መነኮሳት መስቀል ይዘው ባማረ ዑደት የእግዚአብሔርን ምሕረት በእግዚኦታ እየለመኑ ከዶም

ክርስቶፍ ጋር በተገናኙ ጊዜ እንደዚህ ባለ ጭንቅ ዘመን እግዚአብሔር ለእርዳታቸው ስለአመጣን አመሰገኑ:: የቅዱስ ሃይማኖታቸው ጠላት ግራኝ ፲፬ ዓመት ሙሉ ሀገሩንና አብያተ ክርስቲያኑን እንዴት አድረጎ እንዳጠፋው ነገሩት::

ዶም ክርስቶፍ ስለዚሁ ጉዳይ የሃይማኖታቸውንና የክርስቶስን ጠላትን ለማጥፋትና ክርስቲያኖችን ለመርዳት እንደመጡ ነገሯቸው:: እነሱም በዚሁ ደስ እያላቸው ጸሎት ለማድረግ ከሱ ተሰናብተው ወደ የገዳማቸው ሄዱ::

ዶም ክርስቶፍም ባሕረ ነጋሽ አዘጋጅቶላቸው በነበረው ቦታ ሔደው አብረውት ከመጡት የፖርቶጊዝ ወታደሮች ጋር ዕረፍት አደርገን ከሰፈርን በኋላም ባለ ሀገሮችም በባሕረ ነጋሽ ትእዛዝ የሚቻላቸውን ያህል አምጥተውልን በላን ሲል ጽፏል::

ይህ የመጡበት ጊዜም ክረምት ነበርና መካከላቸው የነበረውንም ቦታ ጠላት ይዞት ስለ ነበረ ሁለቱ ከንጉሡ ከዓፄ ገላውዴዎስ ጋር ለመገናኘት የማይቻል መሆኑን ተረዱት:: በኋላ ዶም ክርስቶፍ በ፫ኛው ቀን የዓፄ ልብነ ድንግል ምሽት ንግሥት ሰብለ ወንጌል ደብረ ዳሞ መኖራቸውን ሰምቶ ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ አንድ መቶ ወታደር ከነሱ ጋር ልኮ ንግሥቲቱን አጅበው ከደብረዳሞ እንዲያመጡ አዘዘ:: ንግሥቲቱ መጥተው



www.ethiopianorthodox.org



ድባርዋ ላይ ባንድነት ሲከርሙ ሳለ መነኮሳቱና ካህናቱ ንግሥቲቱ ባሉበት ሕዝቡን ሰብስበው ምህልላና ጸሎት ሲያደርጉ ፖርቶጊዞችም ቁመው ከነሱ ጋር ኑዛዜ እየተናዘዙ ሥጋውና ደሙ ይቀበሉ ነበር›› ይላል::

ካስታንሆግዞ ፖርቶጊዛዊ በጻፈው ታሪክ እንደምናገኘው ንግሥት ሰብለ ወንጌል ከደብረ ዳሞ በብዙ ክብርና ከፍ ባለ ጥበቃና ዓጀብ ሁነው ሐምሌ ፳፯ ቀን ፲፭፻፴፫ (1533) ዓ.ም ድባርዋ ላይ ገብተው እስከ ታኅሣሥ ፲፰ ቀን ፲፭፻ ፴፬ (1534) ዓ.ም ከሠራዊታቸው ጋር ከረሙ:: ባሕር ነጋሽ ይስሐቅም የንግሥቲቱ ሠራዊትንና ፖርቱጊዞቹን ቀለባቸው ለቀን ፲ ከብት ልክ የሌለው እንጀራ ጤፍና ዳጉሳ ከገባሩ እያስመጣ ይቀልባቸው ነበር::

## ምዕራፍ ፲፪

## የፖርቶጊዞች ሥራ

ከዚህ በኋላ ክረምቱን ሙሉ ፖርቶጊዞቹ መድፍና ጥይት የሚጭኑባቸውን ሠረገላዎች እየሠሩ ከርመው ክረምት ሲወጣ ታኅሣሥ ፲፱ ቀን ፲፭፻፴፬ (1534) ዓ.ም ንግሥቲትዋ ከሠራዊታቸው ጋር እንያ ፬፻ ፖርቶጊዞችም መድፎቻቸውና ጥይታቸውን ከነባሩዱም በሠረገሎች ላይ ጭነው ከድባርዋ ከተማ ተነሡ:: ይህም ዘመን በፈረንጅ ዲሴምበር 15 15 41 ዓ.ም ነበረ::

ሲሄዱ ሳሉም (ሚጉኤል) ካስታንሆዞ በጻፈው መጽሐፉ ‹‹ከከተማው ተነሥተን ስንጓዝ መንገዱ አስቸጋሪ ስለሆነ ፰ ቀን ተጉዘን በባሕር ነጋሽ ግዛት ከሚገኘው አምባ እግርጌ ላይ ደረስን:: ከዚህም ኢትዮጵያውያን ‹‹ገና›› የሚሉትን የልደት በዓል አክብረን ዋልን:: በዚሁም ቀን በዙርያው የሚገኙት ብዙ መነኮሳትና አብረው የሚጓዙ ቀሳውስት ሁነው በአንድ ላይ ተሰብስበው የልደት በዓልን በተቻላቸው በብዙ ደስታ አክበረው ዋሉ›› ይላል::

ይህንም እንዳሒሽ ተራራ ግርጌ ልንለው እንችላለን:: ቀጥሎም ስምንቱን ቀን ከዚህ ስንብተን ካሳለፍን በኋላ ከዚህ ተነሥተን መንገዱ ወጣ ገባ አባጣ ጎባጣ በመሆኑ ሠረገላዎቹን ለማስኬድ


www.ethiopianorthodox.org



አስቸጋሪ በሆነው መንገድ ሁለት ቀን ተጉዘን በጣም ከፍተኛ ከሆነ በርዝመቱም እላይ ከተያያዘ ተራራ ደረስን:: መንገዳችንንም ለመቀጠል ይህንኑ ለመውጣት ግድ ስለሆነብን ሠረገላዎቹን ለማለፍ የማይቻል መሆኑን ተረዳን:: ዶምክርስቶፍም መድፎቹንና ሠረገላዎቹን አወላልቀው እያንዳንዱ ቁራጭ ለየራሱ እንዲለያይና ሰው ሁሉ እያንዳንዱ (አዝሎ) በጫንቃው ተሸክሞ እንዲያልፍ ባለው መሠረት ጥይቱንና መድፉን በጀርባችን አዝለን በብዙ ድካም እያሳረፍን በ ፫ ቀን ተጉዘን አወጣነው::

ይህንንም ዳገት ወጥተን በነጭ ድንጋይ የተሠሩ ባለ ብዙ መስኮቶች ስታቴ ጣራ ያላቸው ቤቶች ያሉባት አንዲት ከተማ አገኘን:: ይህንንም በአከለጉዛይ የሚገኘው የእንዳሕሽ አምባ ወይም ተራራዎች መንገድ መሆኑን መገመት ይቻላል:: ይህንንም አልፈን አንድ ቀጥ ብሎ የቆመ አምባ መንገዱም ዘወርዋራ የሆነ ቦታ ደረስን:: ከዚያውም አድረን አምባ ራስጌ ወጥተን ብናይ ቁጥራቸው ከ፫፻ የሚበልጥ ከሞቱ ብዙ ዓመታት ያደረጉ ቆዳቸው ከሥጋቸውና ከአጥንታቸው ሳይለያይ ከዚያው ሳለ ደርቆ የሚኖሩ የሰው ሬሳዎች አየን›› ይላል::

ይህን አምባ መጠራ እንዳ ጻድቃን ወይም ባረክናሣ ነው ልንለው እንችላለን::

ካስታንሆዞ ቀጥሎም ‹‹ከዚህም ተነሥተን ሁለት ቀን ተጉዘን ዓጋሜ ከተባለው አውራጃ ደረስን፡፡ በዚህም ያገሩ ሰው በክተት እየገባልን ስምንት ቀን ቆየን፡፡ ከዚህ በኋላ የካቲት ፫ ቀን ፲፭፻፴፬ 1534) ዓ.ም በፈረንጅ (11 ቀን 1542) ድንኳናችንን በአምባው ላይ ተከልን›› ይላል፤ ይህም አምባ ሰነይቲ ልንለው እንችላለን፡፡

## ከግራኝ ጋር የተደረገ ጦርነት

ከዚህም በኋላ ከግራኝ ጋር የመጀመሪያ ጦርነት ገጥመው፡ ግራኝም ጭኑን በጥይት ተመቶ ፈረሱ ሞተ፡፡ እሱም ወደቀ፡፡ ድል አደረጉትና ከነሠራዊቱ አባርረው ቁስለኞቻቸውን አንሥተው አስቲድኑ ድረስ እየታከሙ አንድ ወር ተቀመጡ፡፡ እንደ ገናም ከዚያ ተነሥተው የንግሥቲቱ ሠራዊትና ፖርቱጊዞች ግራኝ ወደ ሸሸበት እየተከታተሉ ዞብል ከሚባል ቦታ እንዲደርሱበት ፈጥነው ወደ ፊታቸው ሁለት ቀን ተጓዙ፡፡ ሚያዝያ ፱ ቀን ፲፭፻፴፬ 1534) ዓ.ም ቀንም ከግራኝ ሠራዊት ጋር ሁለተኛ ውጊያ ገጠሙ፡፡ ግራኝም በመቁሰሉ ምክንያት በአልጋ ላይ ተሸክመውት በትከሻቸው ስለ ነበረ ፖርቱጊዞችና ኢትዮጵያኖች ፪ኛ ድል አደረጉ፡፡

በዚህ ጦርነት ጊዜ ከግራኝ ብዙ ሠራዊት አልቆበታልና ግራኝና ቱርኮች እየሸሹ ወደ ወፍላ ሐሸንጌ ሄዱ፡፡ ንግሥቲቱና ዶም



www.ethiopianorthodox.org



ክርስቶፍም ከነሱ የሞቱትን ቀብረው የቆሰሉትንም ከአንድ መኮንን ሹም ሀገረ ገዥ ጋር እቤቱ ትተዋቸው ግራኝን ለመከታተል ሠራዊቶቻቸውን ይዘው ወፍላ ሐሸንጌ ላይ ሂደው ምግብና ውኃ አግኝተው ከዚያው ከረሙ፡፡

የሞተ ቀን ማንም ሳይነቅላት ተነቅላ ወድቃ የነበረችውና ደርቃ መነኮሳቱ ለምግባቸው መሥሪያ ዕንጨት ከእርስዋ እየሰበሩ እሳት ሲያነዱ ኑረው እንደገና የተከላትና ያኑሣት ሳይኖር ወደ ነበረችበት ቦታ ቁማ ተተክላ ሥር ሰዳ ዕለቱን ለምልማ ቅጠል አውጥታ ተገኘች። መነኮሳቱም በዚሁ ተአምራታዊ ነገር ተደነቁ። ይህም ነገር በሁሉ ተሰማ።

እኛም ሀገራችን ለመሄድ በምጥዋ ስናልፍ እዚሁ ገዳም እሷን ለማየት ወጥተን ለምልማ እንደ ቀድሞ ቁማ አየናት።›› ሲል ማጉኤል ካስታንሆሆ የተባለው ፖርቱጊዛዊ ጽፎዋል። ይህች ገዳምም እንደ አነጋገሩና ምልክቱ ደብረ ቢዘን ናት ተብሎ ይገመታል። ይህች ዛፍም በእንዳ ዮዲት ወገን ያለች ዛፍ ሳትሆን አትቀርም።





## ምዕራፍ ፲፬

ንግባእኬ ኀበ ጥንተ ነገር ወደ ጀመርነው ከጥንት ነገራችን እንመለስ። ዓፄ ገላውዴዎስ ጠላታቸውን ግራኝን ድል አድርገው የድል አክሊል ተቀዳጅተው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ወደ ከተማቸው ተመልሰው ገብተው ዕረፍት አደረጉ። እነዚያም ኢትዮጵያን ለመርዳት ሲሉ ከሀገራቸው መጥተው ከፍ ያለው ድል ተካፋዮች የሆኑት፡ ቁርጥ በሆነው ሕሊና፡ በማይበገር ጀግንነት ሲዋጉ ከነበሩት ፖርቱጊዞች ግማሾቸው በጦር ዓውድማ ሲሞቱ ከ፬፻ (400) ፖርቱጊዞች አንድ መቶ ተረፉ። እነዚህ የመጡበትን ጉዳይ የድል አክሊል በማግኘት ፈጽመው ከንጉሥ ጋር በድኅና ሥራቸው የፈጸሙ ሁነው ተገኙ።

ከዚህ በኋላ ንጉሡ ዓፄ ገላውዴዎስ የፖርቶገጊዞች አለቃቸው ካፒተን ዶም ክርስቶፍ ዳጋማ በሞተበት ቀን በዓመቱ በመስከረም ፪ ቀን ፲፭፻፴፯ (1537) ዓ.ም ለሞቱት ፖርቱጊዞች ተዝካር አወጡላቸው። ብዙ የገዳማት መነኮሳትና ቤተ ክህነት ከየአውራጃው በኢትዮጵያ ያሉትን ጠርተው የፍትሐቱን ስነ ሥርዓት በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ፈጽመው አስፈትተው ስለ ተዝካራቸው በብዙ ደግ ሰው ሰውን ሁሉ መብሉንና መጠጡን አቅርበው አጠገቡት።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ በኋላ ንጉሡ ለጥቂት ዘመን ዕረፍት አድርገው ሕዝቡን በሰላማዊ ኑሮ ሲስተዳድሩ በነበረበት ጊዜ ፖርቹጊዞች በክብር ተይዘው በፈለጉት አኗኗር እያስደሰቱ ሲያኖሯቸው ቆዩ። ዘግይቶ ግን የተባለው ፖርጹጊዞቹን ከዓፄ ልብነ ድንግል ተልኮ ያመጣቸውና ከፖርቶጌዝ ንጉሥ ፫ኛ ዮሐንስ እርዳታ ለመጠየቅ አስቀድሞ ፖርቶጋል ሂዶ የነበረው ሰው በርሙዴዝ ኢትዮጵያን በካቶሊክ ሃይማኖት እንድታምንና ከእስክንድርያ ጳጳስ ማስመጣት ቀርቶ እርሱ በሮማ ሊቀ ጳጳሳት ስም የኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳስ ለመሆን ዓስቦ ንጉሡ ዓፄ ገላውዴዎስን ‹‹የኢትዮጵያ ሕዝብ ሁሉ በካቶሊክ ሃይማኖት እንዲያምን ዓዋጅ ያስነግሩ ዘንድ ለፖርቱጋል መንግሥትም ከኢትዮጵያ ሀገር ከፍሎ ሲሦ መንግሥት ግዛት ይሰጥ›› ብለው እንዲያውጁ ሲል በድፍረት ተናገራቸው።

ዓፄ ገላውዴዎስም ‹‹ኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖትዋን ለውጣ ወደ ካቶሊክ ሃይማኖትም የምትገባበት ከሀገርም ተቆርጦ ለፖርቶጌዝ መንግሥት ሲሦ ግዛት የምትሰጥበት አንዳችም ምክንያት የለም›› ሲሉ ቁርጥ ያለ መልስ ሰጡት።

ከዚህ በኋላ ቤርሙዴዝ በቁጣ ቃል ተነሣና እንዲህ ሲል ተናገራቸው ‹‹እንግዲያስ ከዚህ አንቀመጥም ወደ ሀገራችን



www.ethiopianorthodox.org



ለመሄድ አሰናብቱን›› ንጉሡም ከሞት የተረፉትን ፻፷፮ ፖርቹጊዛውያን ‹‹ጥቂት ጊዜ አርፋችሁ በክብር ኑሮ ቆዩና እኔም በመልካም አድርጌ አሰናብታችኋለሁ›› ቢሏቸው ‹‹አይሆንም›› ሲሉ የመጨረሻውን መልስ በሰጡ ጊዜ ቤርሙዴዝም ተቆጥቶ ዓፄ ገላውዴዎስ በሰጡት መልስ ስድብ እየጨመረ በኃይለ ቃል እየተናገረ ‹‹አሰናብቱኝ አገሬ እሄዳለሁ›› አለ።

ንጉሥም እሄዳለሁ ካለት ከ፮ ፖርቶጊዞች ጋር አሰናብተውት በድባርዋ አድርጎ ወደ ምፅዋ ወደብ በሆነው ሐርጊጎ ላይ በመርከብ ተሳፍሮ በህንድ ሀገር በኩል አድርጎ ወደ ሀገሩ ፖርቱጋል ተመለሰ።

ይህንን የፖርቴጊዞች ታሪክ የጻፈው ሚጉኤል ካስታንሆዞ የተባለው አብሮአቸው የነበረ ፖርቱጊዛዊ ነው።

ከዚህ በኋላም ከውጊያው ላይ በጥይት ቆስሎ የነበረው ቁስሉ አልሽር ስለአለውና ቁስሉን ለማዳን የሚችል ሰው ስለአጣ ንጉሥን አሰናብቱኝ ቢላቸው ንጉሡ ዓፄ ገላውዴዎስም በጣም እያዘኑ ሌሎችም ፱ ፖርቶጊዛውያን ተጨምረው ‹‹ሀገራችን ናፍቀን እንሄዳለን›› ስላሉ ብዙ ወርቅና ብር የወርቅና የብርም ሽልማትን ሰጥተው እስከ ምጥዋ የሚያደርሷቸው በቅሎና ፈረሶች፡ መንገድ የሚመራ መኮንን አድርገው ወደ ምጥዋ

በክብር ላኩዋቸው:: ከነሡ ጋርም ወደ ፖርቶጊዝ ንጉሥ ፫ኛ ዮሐንስ የምስጋና ቃል የሞላው መልእክት ጽፈው ሰጥተው በብዙ ምስጋና አሰናበቷቸው::

ንጉሥ ዓፄ ገላውዴዎስ ወደ ፖርቶጊዝ ንጉሥ የላኩት መልእክት ይህ ከታች ያለው ቃል ነበር:: ቃሉም በግዕዝ ቋንቋ ነውና እንዲህ የሚል ነበር::

በስመ ሥላሴ ዘኢይትፌለጥ አምላክ ዘይሬኢ እንተአፍአ ወዘየአምር ውሣጤ ሕሊና ዘያደክም ኃያላነ ወዘያነሥእ ውዱቃነ መልእክት ዘተፈነወ እምኀበ ንጉሥ ገላውዴዎስ ወልደ ዓፄ ወናግ ሰገድ ወልደ ዓፄ ናዖድ ወልደ ዓፄ እስክንድር ወልደ ዓፄ በእደ ማርያም ወልደ ዓፄ ዘርአ ያዕቆብ፣ ወልደ ዓፄ ዳዊት ንጉሠ እስራኤል፣ ወልደ ሰሎሞን ንጉሥ ሰላም ለከ ወሰላመ ይኩን ላእሌክሙ ይብጻሕ ኀበ መፍቀሬ እግዚአብሔር ወሃይማኖት ኀበ ኦርቶዶክሳዊ ወልዱ ለዘአማኑኤል ንጉሠ ፖርቶጋል ኀበ ዮሐንስ በጊዜ ፀብዕ ዘረዳእከነ ወፈኖከ ለነ ጀነራል ደም ክርስቶፍ ዳጋማሀ ዘመጽአ ኀቤነ ወዓሊከ በእንተ ክርስቶስ:: የሚልና ስለሚጉኤል ካስታንሆ፤ አገልግሎት የፈጸመውንና ስለ ቁስሉንለማዳን እንዲጥርለት እንዲደክምለት ለንጉሡ ጥብቅ አደራ ያለበት ደብዳቤ ሰጥተው አሰናበቷቸው:: ይህም የሆነው በየካቲት ወር ፲፭፻፴፪ ዓ.ም ነበረ::



www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፲፭

### ዓፄ ሱስንዮስ

ከዚህ በኋላ ከግራኝ ሞት እስከ ፹ (80) ዓመት የሚሆን የኢትዮጵያ በኦርቶዶክስ ሃይማኖት በቀድሞ ወልድ ዋህድ ፩ አካል ፩ ባሕርይ በሚል ከሐዋርያት ተያይዞ በቆየ በአቡነ ሰላማ በተሰበከላት ሃይማኖት ጸንታ ስትኖር በዓፄ ሱስንዮስ ዘመን፲፮፻ ፲፮ (1616) ዓ.ም እግዚብሔር ወልድ በለበሰው ሥጋ ፩ አካል ሁለት ባህርይ ነው የሚል የካቶሊክ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ይሰበክ ጀመር:: የዚሁም መሰበክ ምክንያት በዚህ ጊዜ የካፒታን ዶም ክርስቶፍን ዓፅም ከኢትዮጵያ ወደ ፖርቶጊዝ ሀገሩ ለመውሰድ የዶም ክርስቶፍ ወንድም ልጅ የፖርቶጊዝ ንጉሥ ወደ ጳጳሱ ልመና ማቅረቡ ነው:: ጳጳሱም አልፎንሱ ሜንዲዝ የተባለውን አንድ ካህን ወደ ኢትዮጵያ ልኮ የዶም ክረስቶፍ ዓፅሙን እንዲያስመጣለት ለመነውና ጳጳሱም ከኢየሱሳውያን ማኅበር አንድ ቄስ ጃሮኒ ሉቡሲኒ የሚባለውን ወደ ኢትዮጵያ ላከው::

እነዚህ ማኅበረ ኢየሱሳውያን የተባሉት ከአስጳንያና ከፖርቱጊዝ ሀገር ናቸው:: ከቄሱ ጋርም ሌሎች ጨምሮ ከላካቸው በኋላ ኢትዮጵያ ላይ መጥተው፡ ከዓፄ ሱስንዮስ ተገናኝተው፡ ስለ የካፒታኑ ዶም ክርስቶፍ ዳጋማ ዓፅም ለመውሰድ



www.ethiopianorthodox.org



መምጣታቸውን ነገሩት:: በኋላ ዓፄ ሱስንዮስ ለትግሬ ጠቅላይ ገዥ ተክለ ጊዮርጊስ የተባለው ካፒታን ዶም ክርስቶፍ ሲሞት የጦርነት ሜዳ ወደ ነበረው ቦታ ጠይቆ እንዲያሳያቸው ትእዛዝ አስተላለፈላቸው::

እሱም ጠይቆ አንድ ክርስቲያን አባቴ ነገረኝ የሚልና አንድ እስላም በዓይኑ ዶም ክርስቶፍ ሲቀበር ያየ ሰው አድርጎ መቃብሩን አሳያቸው:: በኋላምየተላከው ቄስ የካፒቴን ዶም ክርስቶፍ ዳጋማን አጥንት አውጥቶ ይዞ በህንድ ሀገር አድርጎ ወደ ሀገሩ ፖርቶጋል አደረሰው::

በዚህ ጊዜ ከግራኝ ሞት ከ፹ 80 ዓመት በኋላ የፖርቶጊዝ ንጉሥ መልእክተኛ የካፒታን ዶም ክርስቶፍ አጥንት የወሰደው ቄስ ጋር የመጡቱ ኢየሱሳውያን ማኅበር ልኡካን ከዚሁ ኢትዮጵያ ላይ ቀርተው የካቶሊክ ሃይማኖትን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ይሰብኩ ጀመር::

ዓፄ ሱንዮስም በዚህ ሐዲስ ካቶሊካዊ ሃይማኖት አምኖ የኢትዮጵያ ሕዝብንም በዚሁ ሐዲስ ሃይማኖት እንዲያምን አዋጅ አስነግሮ አስገደደው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ ግን ‹‹ያንን ከሐዋርያት ተያይዞ በእስክንድርያዊት ቤተ ክርስቲያን በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የመጣልን ወልድ ዋህድ አንድ አካል አንድ ባሕርይ የሚል ያባቶቻችንን ሃይማኖት ትተን በአንድ አካል

ወልድ ፩ ባሕርይ ነው የሚለውን ሃይማኖት እናምንም›› በማለት ጸንቶ ሰው ሁሉ ሽፍቶ በኢትዮጵያ ሁሉ ሁከት ተነሣ::

ንጉሥ ሱስንዮስም ባደረጉት ጦርነት ድል እየሆኑ ይመለሱ ነበር:: በየጊዜውም ጦርነት ያደረጉትንና ድል የሆኑበትን ከዚህ በታች ለማስረዳት ያህል እንገልጥ ዘንድ እንወዳለን::

፩ኛ ውቅሮ በተባለው ቦታ ከኢአማንያን ጋር ጦርነት ያደረጉበትንና ድል የሆኑበትን በነገሡ በ፬ኛው ዓመት ድል ሆኖ ከተመለሱ በኋላ ጎርጎራ ከተባለችው በጣና ባሕር ወደብ ከተማ አድርጎ ተቀምጦ የነበረበት ነው::

፪ኛ በነገሡበት በ፰ ዓመት እንደገና እቴፌር በተባለው ከተማው ሳለ አንድ አካል ፩ ባሕርይ በሚል ሃይማኖት እመኑ ሲል አዋጅ አስነገረና በሰሜን ሀገር ላይ ጌዴዎን የተባለ አንድ ሽፍታ ተነሥቶባቸው ከሱ ጋር ጦርነት አድርጎ ድል ሁኖ ተመለሰ::

፫ኛ በነገሡበት በ፲፩ ዓመቱ ደንቀዝ ላይ ከተማ አድርጎ ሳለ እንደገና ሰሜን ላይ ከጌዴዎን ጋር ሁለተኛ ጦርነት አደረገ:: በዚህ ጊዜ ግን ጌደዎን ሞተ:: በዚሁም ጊዜ ልጁ ሩሲልን በደጃዝማችነት ሰሜንን እንዲገዛ ሾመው:: ከዚህ በኋላ ፩ ባሕርይ ሃይማኖት አናምንም ያሉትን ቤተ ክህነትንና ምእመናን ብዙ መኳንንት ወንዶችንና ሴቶችን ታላላቆችንና

www.ethiopianorthodox.org





ወጣቶችን እየሰበሰቡ ወግዳ በተባለው አውራጃ ላይ እየሰየፉና እየሰቀሉ ሲፈጁ ‹‹አአምን በኢየሱስ ክርስቶስ ዘውእቱ ወልድ ዋህድ አሐዱ አካል ወአሐዱ ባሕርይ›› እያሉ ሁሉ በሰማዕትነት ተሠው::

## ምዕራፍ ፲፮

መንግሥት ከነገደ ይሁዳ ወደ ዛጉዌ በተዛወረበት ጊዜ በ፱፻፳ (920) ዓ.ም በዘመነ ጉዲት ድል ነዓድ ንጉሠ አክሱም በነበረበት በ፲ኛ ዘመነ መንግሥቱ በትግሬ ሀገር ጉዲት ባማራ ሀገር እሳቶ እየተባለች የምትጠራ የፈላሻ ወገን የሆነች ሴት ተነሳች ድልናዓድንም ድል አድርጋ ነገሥታቱ አብርሃና አጽብሐ የሠሩትን የአክሱም ቤተ ክርስቲያን በእሳት አቃጠለች ኢትዮጵያውያንንም በአይሁድ ሃይማኖት እመኑ እያለች በክርስቲያንነቱ የጸናውንም እየሰየፈች ሕዝቡን በብዙ ሥቃይና መከራ እያስጨነቀች ፵ (40) ዘመን ኢትዮጵያን ገዝታ ኑራ በክፉ ሥቃይ ሙታለች::

እንዲሁም ዓፄ ሱስንዮ ስመ መንግሥቱ ሥልጣን ሰገድ ከ፲፮፻፲፮ (1616) ዓ.ም ከነገሡበት ጀምሮ ፩ ባሕርይ በሚል ሃይማኖት ያላመኑትን ሰዎች ሲገድልና ሲያሳድድ በነበረበት ጊዜ ጽላተ ሙሴ የእግዚአብሔር ታቦተ ሕግ ከአክሱም ድግሳ ወደ ተባለው የአካለጉዛይ አውራጃ ተሰደደች:: እነዚያ የሀገሩ ሰዎች ደቂ ድግናም በክብር ተቀብለው የሱስንዮስ መንግሥት እስኪያልፍ ድረስ ድግሳ ተቀምጣ ቆየች::

‹‹ፋሲል ይንገሥ ሃይማኖት ይመለስ›› የሚል አዋጅ ተነግሮ ዓፄ ፋሲል ዓድያም ሰገድ ከነገሡ በኋላ ግን ታቦተ ጽዮን



www.ethiopianorthodox.org



ከድግሳ ፲፪ ዓመት ተቀምጣ ኑራ እንደገና ወደ አክሱም በሺህ ፲፮፻፳፭ (1625) ዓ.ም ከቦታዋ ተመልሳ ገባች:: ስትመለስም እነዚህ ደቂ ድግና በድግሳ ላይ በክብርና በብዙን ጥንቃቄ እንደ ጠበቋት አክብረው አጅበው አክሱም ድረስ ሸኝተው አደረሰዋት:: ስለዚህም ንጉሡና የአክሱም ሰዎች ደቂ ድግናን እንደ አክሱም ባለባቶች መብታቸውን እንዲያገኙ የሚል ሕግ ተወሰነላቸው:: የኢትዮጵያ ክብረ ነገሥትም ስለዚሁ ታሪክ ‹‹ፖርቶጋሎች ኢየሱሳውያን በመምጣታቸው ጊዜ ፩ ባሕርይ ሃይማኖትን ባመጡት አናምንም ስላሉ ብዙዎች በሰይፍ በጦር እሳት ተገደሉ:: በየያይነቱ የሆነ ቅጣት ሞትና ግርፋት ተቀበሉ:: መከራና ስደትም ጸናባቸው:: ጽዮን ታቦተ ሕግም ከአክሱም በምሥራቅ ወደ ምትገኘው በአንዲት ድግሳ በምትባል ሀገር ተሰዳ ተቀመጠች›› ይላል::

በ፲፮፻፲፩ ዓ.ም ከክርስቶስ ልደት በኋላ በስደት ከአክሱም የወጣችበት ቀንም ኅዳር ፮ ቀን ቅዳሜ ዕለት ነበረ:: የድግሳ ሕዝብም ከፍ ባለ ክብር ተቀብለው በብዙ ጥንቃቄና ጥበቃ፲፪ ዓመት ያህል አስቀመጧት:: ቀጥተኛይቱ የአባቶች ሃይማኖት ከተመለሰች በኋላ ጽላተ ሙሴ ተመልሳ ከፍ ባለ ክብረ ወደመንበርዋ ተመለሰች::

የገባችበትም ቀን ሐምሌ ፳፮ ቀን ፲፮፻፳፬ ዓ.ም እንድ የንጉሥ ፋሲል መጀመሪያ መንግሥት ዘመን ነበር። ይህም ፋሲለደስ ርቱዓ ሃይማኖት ነው። የድግሳ ሰዎችም ከርስዋ ጋር በክብር አጅበዋት እስከ አክሱም ድረስ መጡ። ስለዚህ በንጉሡ ትእዛዝና በሊቃውንቱ ፈቃድ ተጽፈው ተመዘገቡ። በደብተራው ፈቃድም ከአገልጋዮችዋ ጋር ተቆጠሩ። ትክክል ሆኑ ይላል።

ይህም የሆነበት ምክንያት የሚከተለው ነበር። አንደኛ ዓፄ ሱስንዮስ በ፷፬ኛ ዘመነ መንግሥቱ ጊዜ በላስታ ሀገር ብርቱ ጦር ተነሳባቸው። ከዚሁ ጦርነት ለማድረግ በተነሡበትም ጊዜ ልጁ ደጃዝማች ፋሲል አባቱን ዓፄ ሱስንዮስን ለመርዳት ሠራዊቱን አስከትቶ መጥቶ ነበር ይህ የሚሄዱበት ጦርነት ብርቱ በመሆኑንና ከዚህ ቀደም ካደረጉት ጦርነትም ድል እየሆኑ በመመለሳቸው። ዳግመኛ ይህ አዲሱ ሃይማኖት ስለታወጀ በሕዝብ ላይ ሁከት ገብቶ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሞላው የከዳ በመሆኑ ነው። በዚያም ጊዜ ዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ለንጉሥ ሱስንዮስ ሁል ጊዜ ድል የሚሆኑበት ምክንያት ሃይማኖት መለወጥ መሆኑን እያስረዱ እንግዲህ በዛሬው በምናደርገው ጦርነት እግዚአብሔር ድል የሰጠን እንደሆነ ልጅዎን ፋሲልን ሊያነግሡ ሃይማኖትም ሊመልሱ



www.ethiopianorthodox.org



ስእለት ይግቡ ብለዋቸው ንጉሡም እሺ እንዳላችሁኝ ስእለት ገብቼ አለሁ በማለታቸው ነበር።

ከዚህ በኋላም ሰኔ ፫ ቀን ፲፮፻፳፫ ዓ.ም ሰኞ ቀን 1623 ተነሥተው ሰኔ፳፬ ወይና ደጋ ከተባለው ቦታ ጦርነት ገጠሙ። በጦርነቱም ድል አድርገው ከፍ ያለ ዕድል ያለው አሸናፊነት በማግኘታቸው በብዙ ደስታ ከተመለሱ በኋላ እንደ ተሳሉት ‹‹ፊተኛው አዋጅ ይፍረስ ፋሲል ይንገሥ ሃይማኖት ይመለስ›› ሲሉ አዋጅ አድርገው ፋሲል ልጃቸውን በሕይወት ሳሉ ከዙፋናቸው አስቀምጠው አነገሡት። ክብረ ነገሥት ተከለ ጻድቅ መኩሪያ ከገጽ ፱ እስከ ፺፯ ተመልከት። ከዚህ በኋላ ሕዝቡ በተዋህዶ ሃይማኖት ወልድ ዋህድ ፩ አካል ፩ ባሕርይ ነው። በሚል እንደ ቀድመው በእምነቱ ጸንቶ በሰላም ይኖር ጀመር።

## ምዕራፍ ፲፯

## ዓፄ ፋሲል

ዓፄ ሱስንዮስ በዓዋጅ ‹‹ፋሲል ይንገሥ ሃይማኖት ይመለስ›› ብለው ልጃቸው ፋሲለደስ ስመ መንግሥታቸውን ዓለም ሰገድ አሰኝተው ከሞቱ በኋላ ንጉሡ ፋሲል ከተማቸውን ጎንደር ላይ ቆርቁረው ተቀመጡ:: በዚያም ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተዋህዶ ሃይማኖት ተቆርቋሪ መሆናቸውን ያውቅ ነበርና መንግሥታቸውን በደስታ ተቀብሎ፡ በዱር በገደል የነበረው ሽፍታ ሀገሩ ገብቶ፡ በሰላም ለንጉሠ ነገሥቱ ተገዝቶ ሲኖር ሳለ:: የቤተ ክህነቱ ሊቃውንት በዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስ መሪነት ተሰብስበው ከንጉሡ ዘንድ ሒደው ‹‹ከዚህ ቀደም እነዚህ ሚስዮናውያ ባመጡት፪ ባሕርይ ሃይማኖት ጠንቅ የብዙ ምእመናን ደም በከንቱ ፈሰዋልና ከሚስዮናውያን ጳጳስ ከሜንዴዝ አልፎንሱ ጋር ስለ ሃይማኖቱ ክርክር ለማድግ ለጉባዔው ዓዋጅ ይነገርልን›› ሲሉ ለዓፄ ፋሲል አመለከቱ:: ዓፄ ፋሲልም ዓዋጅ አስነግረው ከያገሩ ሊቃውንት ተሰብስበው ጎንደር ላይ ጉባዔው ተደረገ::

በዚህ ጊዜ ዕጨጌ በትረ ጊዮርጊስ የተማሩ ሊቅ ነበሩና ለሊቃውንቱ አፈ ጉባዔ ሆነው ሲቆሙ ሜንዴዝ አልፎንሱም ወገኖቹን እነ ፔኤዝን ይዞ ቆመ:: በመጀመሪያ አልፎንሱ እጨጌ



www.ethiopianorthodox.org



በትረ ጊዮርጊስ ‹‹የእግዚአብሔር አብ የባሕርይ ልጁ ታሞ ተሰቅሎ ሙቶ ዓለምን አዳነ የሚል መጽሐፍ ከብሉይ ከሐዲስ ማስረጃ ስጡኝ›› ብሎ ጠየቃቸው:: ዕጨጌም ጳውሎስ ‹‹ለሮሜ ሰዎች የጻፈላቸው መልእክት ክርስቶስ ስለኛ እንዲሞት ብሎ በዕነ ቀጠሮው መጣ ይላል ፭፥፰ቁ ዳግመኛም ዝቅ ብሎ ለእግዚአብሔር እኛ ጠላቶቹ ስንሆን በልጁ ሞት አዳነን›› ይላል ፭ ም፥፲ቁ ቢሉት መልስ አጥቶ ዝም አለ:: ቀጥሎም በዚሁ ቢሸነፍ ማሸነፊያ ያገኘሁት መስሎት ‹‹የእግዚአብሔር ፊት ወዴት ነው›› ሲል ጠየቃቸውና ዕጨጌም ወዲያው ጥዋፍ አብርተው በጉባዔው ፊት ‹‹የዚሁ መብራት ፊት ወዴት ነው›› ብለው መልስ ቢጠይቁት እንደገና መልስ አጣ:: ዕጨጌም ‹‹የዚሁ መብራት ፊቱ ወዴት መሆኑን ወደ ዚህ ብለህ እንደማይለይ የእግዚአብሔርንም ፊት እንዲሁ በሁሉ ዘንድ ነው›› ሲሉ መልስ በሰጡት ጊዜ አልፎንሱ ተረትቶ ሄደ::

ከዚሁ አያይዞ ስለዚሁ አንድ ሊቅ ‹‹ወረከብናሁ ለበትር ዘያደክማ ለሮሜ ጽሩብ በንባብ ወቅሩጸ በትርጓሜ››፤ ብሎ ተቀኘና ሊቃውንቱ ‹‹ንሴብሖ ለእግዚአብሔር ስቡሐ ዘተሰብሀ›› እያሉ በአደባባይ አሸበሸቡ ሲል ታሪክ ነገሥቱ ይገልጻል::

ክቡር አንባቢ ይህንን ሁሉ መልስ የመለሱት ኢትዮጵያዊ ሊቅ የእስክንድርያ ጳጳስ መሆናቸው ሊባል ነውን? አይደለም

ከጥንት ከአባቶቻቸው የኢትዮጵያ ሊቃውንት ተምረው የወረሱት ሊቅነት መሆኑን በግልጽ ያስረዳናል። መጽአ የሚለውን ባሕርየ መለኮቱን ነው እንጂ ባሕርየ ሥጋውስ ከዚህ ምድራዊ ስለሆነ በጽኑ ቀጠሮው መጣ አያሰኘውም ነበረ። ስለዚህ ኢትዮጵያ ሀገራችን ባለፈው አንቀጽ እንደተናገርነውና እንደ ተገለጸው የ፪ ባሕርይ በህል ሃይማኖት ከተሰበከላት በኋላ ምንም ፋሲል ይንገሥ ሃይማኖት ይመለስ በሚል አዋጅ ታውጆ በጥንታዊ ሃይማኖት ጸንታ ብትኖርና ያለች ብትሆን ዓፄ ፋሲል እኒህ ሚስዮናውያን እነ ሜንደዝ አልፎንሱ እነ ፖኤዝ በሃይማኖት ምክንያት ገብተው ጠላት የውጭ መንግሥት ለማስመጣት ሳያስቡ እንደማይቀሩ አስበው ሚስዮኖቹን ከሀገር ወጥተው በምጥዋ በኩል ወደ ሀገራቸው እንዲሄዱ የሐማሴን ባሕር ነጋሽን አዝዘው አባረዋቸዋል። ሲል የሚስዮኖቹን መሄድ የኩልቦ የጵሩሾን የሳቤላ መጻሕፍቶች ታሪክ ይተርካሉ።

የሀገራችን ታሪክ ነገሥት ግን አሳቡን ከነዚሁ ሳይለይ ባጭር መንገድ እንደዚህ ይላል። ‹‹ዓፄ ፋሲል (ዓለም ሰገድ) ሜንደዝ አልፎንሶን በምጥዋ በኩል እንድሄድ ከተላከ ሐማሴን ሲደርስ አመመኝ ብሎ ቀርቶ የቅባቶችንና የጸጋዎችን ሃይማኖት ከርሱ



www.ethiopianorthodox.org



ሃይማኖት አመሳስሎ ‹‹ክርስቶስ በቅብዓተ መንፈስ ቅዱስ ከአብ አንደኛ የጸጋ ልጅ ሆነ›› ብሎ በግልጽ አስተማረ።

አስተምሮም በመጨረሻ ጊዜ ‹‹ለኢትዮጵያ ሁለት እሾኽ ተክየባት ሄድኩ››፤ ብሎ ፈክሮ በምጥዋ በኩል ወደ ሀገሩ ተመለሰ ይላል።

ጸጋ ልጅና ቅብአት ሃይማኖት ነው። በዚሁ አልፎንሱ የተከላቸው እሾኾች ቅባትና የጸጋ ልጅ ሃይማኖት ትምህርት በኢትዮጵያ አንድ ጊዜ ሲቀዘቅዝ አንድ ጊዜ ሲነሳ ቢኖርም በዚሁ ሃይማኖት የሚገኙ ሰዎች በአንድ ሚልዮን ከሁለት ሦስት የሚበልጥ አልነበረም። ስለዚህም በየጊዜው በሊቃውንቱ በኩል የሃይማኖት ክርክር ቢነሳበትም ሕዝቡ ጉልህ ሁኖ የሚያውቀውና የሚያምነው ያ ጥንታዊ በአባ ሰላማ ከሣቴ ብርሃን የተሰበከላትን የተዋህዶ ሃይማኖትን ትምህርት ስለሆነ በዚሁ በተዋህዶ ሃይማኖት ሕዝቡና መንግሥቱ እስከ ዛሬ ጸንቶ ያለና የሚኖር ሆንዋል። በዚያን ጊዜም ይህንን የሃይማኖት ትምህርት ሲነቅፍ አንድ ሊቅ እንዲህ ሲል ተቀኘ።

## ሥላሴ ቅኔ በግዕዝ

ቃለ እምነ ሥጋ በአፍአ ፈለጡ ውሉደ ሮሜ ዘንተኒ
ልማደ ዘአፍአ ከመኢንግበር ልማደ
ዋህድና ክልኤቱ በታቦር ተግህደ፤

በሰገደሂ ለቃል እንዘ ይሬሲ እሐደ፤
በሥጋ ሰገደ ኀበ ሰገደ፤
ወልደ አብ እስመ ኢወለደ።
ወድንግል ኢወለደት ባዕደ።

ይህም በአማርኛ ትርጓሜው የሮሜ ልጆች ቃልን ከሥጋ ለዩ። ይህንን በመለየት ልማድ እንዳናደርግ ግን የቃልና የሥጋ መዋሐድ ሊያስረዳ አብ ይህ ልጄ ነው ባለው ምስክርነት በታቦር ተገለጠ። ቃልን ከሥጋ ጋር አንድ አድርጎ ለቃል የሰገደ በሥጋ ሰገደ። አብም ድንግል የወለደችውን እንጂ ሌላን አልወለደም። ድንግልም አብ የወለደውን እንጂ ሌላ አልወለደችምና። ያንኑ አብ ልጄ ያለው አንድ አካል ነው ማለቱ ነው።





## ምዕራፍ ፲፰

እንዲህ ሲሆንም ከዚህ በፊት እስከ ዓፄ ልብነ ድንግል በነበሩ ዘመኖች የውጭ ሀገር መንግሥታት የእጅ ሥራ የንግድ ጉዳይ ከመነጋገር በቀር ለሃይማኖት እንደ አሁን ጊዜ ከሊቀ ጳጳሱ በመተባበር አይጣጣሩም ነበር። ከዓፄ ልብነ ድግል ወዲህ ግን በግራኝ እርዳታ ምክንያት ከፖርቶጋልና ከእስጳኛ ነገሥታት በኢትዮጵያ ላይ በቤተ ክህነቱ ገብተው መንግሥታቸውን ለማስፋፋት ሲሉ ከሮማ ሊቀ ጳጳሳት ተስማምተው ኢትዮጵያን በ፪ ባሕርይ ሃይማኖት ለማሳመን የዚሁን ሃይማኖት ለውጥ በየክፍላቸው የሀገር ግዛት ድርሻ ለመካፈል ተስማምተው ነበር።

ይህንንም ለመፈጸም መጀመሪያ በዓፄ ዘድንግል ፪ኛም በዓፄ ሱስንዮ ዘመነ መንግሥት በበለጠ ፈንታ አግኝቶ ፩ሺ ፮፻ ዓ.ም ጸንቶ የነበረውን የተዋህዶ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ገልብጠ ዓፄ ሱስንዮስም በ፪ ባሕርይ አምኖ ሕዝቡን እመኑ እያለ ዓዋጅ ቢያስነግር የተቃወመውንም ቢያስቀጣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በማይንቀሳቀስ መንፈስ ተመርቶ የቆየውን ኦርቶዶክሳዊ ሃይማኖቱን አልለውጥም በማለት እንቢ ብሎ የመጣውን አዲስ ነገር ካገሬ አላገባም ሲል መከተ። ስለዚህ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን የጀመረችው ዓላማ ወደ ግቡ ሳይደርስ ቀረና በቆየው

www.ethiopianorthodox.org

ሃይማኖቱ ጸንቶ ረጋ፡፡ በዚሁ ኢዲስ የ፪ ባሕርይ ሃይማኖት ብዙ የክርስቲያን ደም ስለ ፈሰሰ ግን ያሳዝናል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ በሃይማኖቱ ጸንቶ ረጋ ሲባልም በላይ አልፎንስ ሁለት እሾኽ በኢትዮጵያ ላይ ተክየባት ሄድኩ እንዳለው ይህ የቅብአትና የጸጋ ልጅ ሃይማኖት ያን ጊዜ ምንም ቢሰበክ ባዕዳን በጻፉት ታሪክ ተመርዘው ከአባ አየለ በተጻፈው መጽሐፍ የሸዋ ሃይማኖት ጸጋ ልጅ የጎጃም የቅብዓት ሃይማኖት ትግሬም የካራ ሃይማኖት ነው ሲሉ የጻፉት ሕዝቡን ለመለያየት የውጭ ሀገር ሰዎች የጻፉትን ታሪክ ብቻ ተምሮ ያገሩን ታሪክ ባለመማርና ባለማወቅ ስለሆነ የነጮች ደጋፊ በመሆን ሀገሩን ሲያዋርድና ያገሩን ህዝብ ሲለያይ ይገኛል፡፡

ሁኖም ይህ አዲሱ ሃይማኖት በኢትዮጵያ ከተሰበከ በኋላ እነ አልፎንሱና እነ ፖኤዝ በቅዱሳት መጻሕፍት የኢትዮጵያ ሊቃውንት ከረቷቸው በኋላ ዓፄ ፋሲል ከሀገሬ ውጡልኝ ብለው ቢያባርሯቸው ከነሱ ሰዎች በትግሬ ጠቅላይ ግዛት ፍሬምና በተባለው መንደር ተደብቀው ስለ ቀሩ ያንን የሕዝብ መንፈስ ለመለያየትና የውጭ ሀገር መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር የታቀደው እንዳይቀር ይጥሩ ስለ ነበር ኢትዮጵያ ዕረፍት አላገኘችም፡፡

በዚህም የኢትዮጵያ መዝግያ መፍቻ አገኙና የውጭ ሀገሮች የሃይማኖት ሰባክያን ነን እያሉ በርዋን ከፍተው በየጊዜው እየገቡ ስለ ሰበኩ ከዚያ ወዲህ ኢትዮጵያ ኃይሏ እየደከመ የሕዝቧ መንፈስ እየተለያየ ይሄድ እንደ ጀመረ ታሪክ ነገሥት በተክለ ጻድቅ መኩሪያ የተጻፈውን ከገጽ ፻፯ እስከ ፻፱ ገጽ ተመልከት፡፡

ከዚያ በፊት ዓረቦች ቱርኮች የእስላም ሃይማኖትን በመስበክ የአንዲት ኢትዮጵያ ሕዝብ አንድ ሲሆን በሃይማኖት ምክንያት ለያይተው የእርስ በእርስ ክርክር ጠብ በማንሣት፡ እርስ በእርሱ ደም በማፋሰስ፡ ቂምና በቀልን አብቅለውባት አልፈዋል፡፡ ቱርክና ምስርም በየጊዜው እየገቡ ለመውረር ተመችቶዋቸው ጠረፎችን ይዘው፡ መውጫና መግቢያን በመንሣት ሲያስጨንቋት ነበር፡፡ እንዲሁም ይህ የውጭ ሀገር ሃይማኖት ከተሰበከ ወዲህ የሃይማኖትን ባህል ተመርኩዘው የአውሮጳውያን ነገሥታት በየጊዜያቸው ብቅ ብቅ እያሉ ስለነበር ኢትዮጵያ ሰላምን ለማግኘት አልተቻላትም፡፡

## አባ ርዝቅላና አባ ጴሰፔ

ከነዚህም በኋላ በዓፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት አባ ርዝቅላ (ኢርዛቅና) የተባለ ነጭ ተደብቆ ለማታለል መጥቶ ‹‹እኔ ከእስክንድርያ ሊቀ ጳጳሳ የተላክሁ ጳጳስ ነኝ›› ብሎ ታቦቶቹን



www.ethiopianorthodox.org

እየባረከ፡ ክህነትና ዲቁና እየሰጠ ሲኖር ከጥቂት ቀን በኋላ ካቶሊካዊ ሮማዊ መሆኑ ታውቆ ከተመረመረ በኋላ ሐሰተኛ ጳጳስ ሲሉ አባርረው ወደ ሀገሩ አሻገሩት፡፡ ወዲያው እንደ ተለመደው ከእስክንድርያ አባ ማርቆስ የተባለውን ጳጳስ ኦርቶዶክሳዊ በ፲፮፻፳፯ ዓ.ም አስመጥተው ዓፄ ፋሲል ወደ ጎንደር ከተማቸው ሲገቡም በክብር ተቀብለው በክብር አስቀመጡት፡፡

ከ፳ ዓመት በኋላም አባ ማርቆስ ቢሞቱ አባ ጆቫኒ የተባለ ከእስክንድርያ የተላክሁ ነኝ ሲል በደንከል በኩል አባ ሚካኤል የተባሉም በስናር በሱዳን ሀገር በ፲፮፻፴፱ ዓ.ም መጡና ዓፄ ፋሲል በደንከል የመጣውን ጳጳስ ሐሰተኛ መሆኑን መርምረው የባእዳዊ ሃይማኖት በመሆኑ ለማታለል መምጣቱን አውቀው ሰርካ ከተባለ አምባ እንደ እስረኛ አድርገው አስቀመጡት፡፡ በሱዳን (ስናር) ሀገር የመጣውን አባ ሚካኤል የተባለውን ግን በእስክንደርያ ሊቀ ጳጳሳት ፈቃድ የመጣ ኦርቶዶክሳዊ ጳጳስ መሆኑን ስለ ተረዱት በክብር ተቀብለው አስቀመጡት፡፡

ከዚህ በኋላ በ፲፮፻፴፯ ዓ.ም ከነገሡ በ፴፰ኛ ዓመት ዓፄ ፋሲል ‹‹የሐዲስ ሃይማኖት ስብከት ያለበት መጻሕፍት ሁሉ የፈረንጅ ስብከት የማታለል ነውና እሳት አቃጥሉት›› ሲሉ ትእዛዝ ሰጥተው አቃጠሉት፡፡



www.ethiopianorthodox.org



ከዚህ በላይ እንደ ተባለው ወንጌል እንስብካለን እያሉ በሃይማኖት ምክንያት ነጮች በየጊዜው እየመጡ ለአንዱ ደጀዝማች ጠበንጃ፡ ለአንዱ ራስ መድፍና ጥይትን በየዓይነቱ ከመንግሥታችን እናስመጣልህ እያሉ የኢትዮጵያ መኳንንትን ከነገሥታቶቻቸው ጋር እያጣሉና እርስ በእርሱ ደም በማፋሰሳቸው ልብ ለልብ መለያየት ስለ በዛ የኢትዮጵያ ነገሥታት ክብራቸው እያነሰ፡ ግዛታቸውንም እየተቀነሰ የሕዝባቸው ደም ስለ ባዕድ እየፈሰሰ፡ የሀገራችን ክብር እየተገሠሠ ሔደ፡፡

ኢትዮጵያ በዘመነ ብሉይ በሕገ ኦሪት፡ በዘመነ ሐዲስ በሕገ ወንጌል ሐዋርያት ከሁለት አካል አንድ አካል ከሁለት ባኅርይ አንድ ባሕርይ ሆነ ብለው ያስተማሩትን ሃይማኖት በማመን ጸንታ የኖረችና የውጭ ሰዎች የሃይማኖት ስብከት ሳይገባባት ነገሥታቷና ሕዝቧ አንድ ልብ በመሆናቸው ምክንያት በዘመነ ብሉይ የነበሩ ነገሥታት እስከ ዓረብ ምድር እስከ የመን ድረስ ግዛታቸውን አስፋፍተው ይገዙ ነበር፡፡ በዘመነ ሐዲስም እስከ ዓፄ ካሌብና እስከ ዓፄ ገብረ መስቀል ከዚያ በኋላም የነበሩ የኢትዮጵያ ነገሥታት እስከ ረዥም ዘመናት ባሕርን ተሻግረው እየገዙ ግዛታቸውን አስፋፍተው እንደ ነበር በኢትዮጵያ ታሪክ

ነገሥት ላይ አውጣጥተን ከዚህ በፊት ባለፉት ምዕራፎች ገልጸነዋልና ከዚህ መድገም አያስፈልግም።



www.ethiopianorthodox.org



## ምዕራፍ ፲፱

የሮማ ባዕድ ሃይማኖት ቤተ ክርስቲያን ልዑካን የሆኑት ሰዎች በቅርብ ጊዜ የሠሩትን ተንኮል እኒህ ፫ቱ መጀመሪያ ከሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ሊሰብኩ ተልከው ወደ ኢትዮጵያ ሀገራችን መጥተው ያደረሱትን ጉዳት ከዚህ በታች በየጊዜው የምንገልጸው ነውና አንባቢ ተመልክተህ አስተውል። የሠሩትም በጊዜያችን ስለ ተፈጸመ ስብከታቸው የተንኮል ሥራ መሆኑ ግልጽ ሁኖ ይገኛል። እነዚህም እኩያን ፩ኛ አባ ጂስቴ ፪ኛ **አባ ያዕቆብ** (ጁስኮቦ) ፫ኛ አባ ማስያስ የተባሉት ካቶሊካውያ ናቸው።

አባ ጁስፐ ሳፔቶ ወንጌልን አስተምራለሁ እያለ በዓሰብ ወደብ ያለውን ፯ ኪሎ ሜትር ቦታ ኢብራሂም ከተባለው የደንከል ባላባት ሀገረ ገዥ ሱልጣን ለኢጣልያ ወታደርና ለጦር መሣርያ የሚያከማቹበት ቦታ በ፰ሺ ከአንድ ፻ (8100) ብር ሰጥቶ ለኢጣልያ መቆናጠጫ ይሆናት ዘንድ ገዛ።

ይህም ውሸት እንዳይባል አባ ጁስፔና ሱልጣን ኢብራሂም ገንዘቡን ተሰጣጥተው በተፈራረሙበት ቀን በማግስቱ ፳፩ ጊዜ መድፍ በኢጣልያ ሮማ ላይ በመተኮሱና የኢጣልያ ሰንደቅ ዓላማ ዓሰብ ወደብ ላይ መተከሉ ምስክር ይሆናል። በዚሁ

ጠንቅ አባ ጄስፔ ማኅበሩን አቋቁሞ ዓሰብን ለ፲፫ ዓመት በማኅበሩ እጅ ካቆየ በኋላ የኢጣልያ መንግሥት ለማኅበሩ ፬ሺ(4000) ሊሬ ሰጥቶ ከማኅበሩ እጅ ወስዶ ወታደሮቹንና የጦር መሣሪያውን አስቀምጦበት በዙሪያው የሚገኙት ደሴቶችና ወረዳዎች ይዞ ግዛቱ አደረገው:: በሺ፰፻፹፩ (1881) ዓ.ም እንደገና በምፅዋ ገብቶ ኤርትራን ግዛቱ አድርጎ ኢትዮጵያን ለመውረር በ፲፰፻፹፰(1888)ዓ.ም በየካቲት፳፫ቀን በዘመነዓድዋ መላዋን ኢትዮጵያ ለመውረር ሞከረ:: ይህም የሆነው ዓሰብን መቆናጠጫ አድርጎ ስለ ያዘ ነው::

ስለዚህ የኢጣልያ መንግሥት አባ ጄስፔን ይህንን ስለ አደረገለት ቅዱስ አባ ጄስፔ ሳፔቶ እያሉ የሮማ ቤተ ክርስቲያንም ጭምር እስከ ዛሬ የአባ ጄስፔን ሥዕል በፎቶግራፍ እያነሣች ከመጻሕፍትና ከቤተ ክርስቲያኗ መድረክም እያስጌጠች ቅዱስ ብለው ስለ እርሱ ክብር መጻሕፍትን እያጻፉ ካቶሊካውያን ሁሉ ይሰግዱለታል::

፪ኛ በምፅዋ ወደብ ወጥቶ እስከ ጎንደር ድረስ ሊሰብክ የተላከው አባ (ጄስኮቦ) ያዕቆብም ደግሞ የተላከበትን የወንጌል ቃል በመስበክ ፈንታ ጎንደር ላይ የ፪ት ባሕርይ ባዕድ ሃይማኖት ባህልን እየሰበከ በሕዝቡ ላይ ሁከትና ግርግር አስነሥቶ ነበር:: በሕዝቡም ዘንድ ክርክር ስለ አበዛ አርቆ ተመልካችና አስተዋዩ





ዓፄ ቴዎድሮስ የኢትዮጵያ ሕዝብ የአንድነት መንፈሱ እንዳይለያይ እና ኢትዮጵያ የውጭ ሰዎች ወረራ ግዳይ እንዳትሆን በማለት አባ ያዕቆብን በ፲፰፻፵፯(1847) ዓ.ም ‹‹በተዋህዶ ሃይማኖት የምታስተምር እንደሆንክ ተቀመጥ፤ በተረፈ ሰዎችህን ይዘህ ከሰዎችህ ጋር ሀገሬን ለቀህ ውጣ›› አሉት:: እርሱ ግን ከተባረረም በኋላ በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ተገኘ አሰሩት:: እንዲህ ማድረጋቸው ነጮች በሃይማኖት ስብከት እያስመሰሉ ገብተው ብዙዎች ሀገሮችን ግዛታቸው አድርገው መኖራቸውን ስለ አወቁ ነው:: ኋላ ግን አባ ያዕቆብን ከታሰረበት ፈትተው በምፅዋ በኩል ወደ ሀገሩ እንዲሄድ አባረሩት:: አባ ያዕቆብ ግን ኤርትራ ሲደርስ ተደብቆ በአካለ ጉዛይ አውራጃ ላይ በሐላይ በሌሎችም መንደሮች እየተዛወረ ይሰብክ ነበር::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፳

አባ ያዕቆብ ከሃይማኖት ስብከት ይልቅ የተላከበት ዋና ሥራው ለሀገር ወራሪ ለፖለቲክ ስለ ነበር ከፈረንሳዊ ንጉሥ ናፖልዮን ፫ኛ እየተላላከ ስለ ሀገሩ ልማትና ስለ መንግስቱ ስፋት የሚሰራው ዋና ጉዳይ ነበረው።

## ዓፄ ቴዎድሮስና ደጃች ንጉሤ

ይህ ሰው ሲሠራው ከነበረውም አንድ ታሪክ ከዚህ በታች እንገልጻለን፤ አባ ያዕቆብ የወንጌል መልእክተኛ ተመስሎ የነጮችን መንግስታት መልእክተኛ ስለሆነ መንግስቱን ወደ ኢትዮጵያ ለማስገባት የነበረውን ሐሳብ ለመፈጸም ትግሬ ላይ ከአጋሜ አውራጃ ውስጥ እየተመላለሰ ከሀገረ ገዥ ከደጃዝማች ንጉሤ ጋር የለበጣ ፍቅርን መስርቶ ነበር። በዚህ ተንኰሉም ደጃዝማች ንጉሤን አባብሎ ከዓፄ ቴዎድሮስ አቀያየመ። ቅያሜ የፈጠረውም ጉዳይ የሚከተለው ነበር። ደጃዝማች ንጉሤ ሀገሩ ሰዓስዕ ይባላል። የኢሮብ ባላባት ነው። አባ ያዕቆብ ደጃዝማች ንጉሤ ዓፄ ቴዎድሮስን የሚወጋበት የጦር መሣሪያ ጠበንጃና መድፍ ከነወታደሩ ከፈረንሳይ ንጉሥ እንድትልክላቸው ሲል ወደ ናፓልዮን የፈረንሳይ ንጉሥ ላከ መልዕክቱንም የላከው



www.ethiopianorthodox.org



በዚያን ጊዜ በነዚያ በባዕድ ሃይማኖት ባመኑት የሀገራችን ሰዎች አድርጎ ነበር።

የመልእክቱን ደብዳቤ በኛ ሰዎች የላከበት ምክንያትም ንጉሡ ናፖልዮን የኢትጵያ ሕዝብ ሃይማኖቱን መቀበሉን እንዲረዳለት በማለት ነበር። መልእክተኞቹም ፩ኛ አባ እምነቱ ፪ኛ ልጅ ጸጋይ ጋብር ናቸው። አባ ያዕቆብ ፈረንጁ እነዚህ ፪ቱን ሳፔር የተባለውን አንድ የፈረንሳይ ሰው የነሱ መሪ አድርጎ ሲልካቸው ለፈረንሳይ ንጉሥ ለናፖልዮንና ለሮማው ሊቀ ጳጳሳት ፱ኛ ፒዮስ የሚሰጥ ደጃዝማች ንጉሤ የላኩት ደብዳቤንና የብር ሽልማት የበቅሎና አንበሳ ቆዳና ጎፈር ሌላም እሱን የመሳሰለ ገጸ በረከቱን አስይዞ ነበር። መልእክተኞቹም በኅዳር ወር ፲፰፻፶፩(1851) ዓ.ም ማሳጀር ኢምፐሪያል በተባለችው መርከብ ተሳፍረው ከምፅዋ ተነስተው በጥር ወር ፲፰፻፶፩ (1851) ዓ.ም ሮማ ደረሱ። በዚያም ከሊቀ ጳጳሳቱ ተገናኝተው ለሊቀ ጳጳሳቱ ደጃዝማች ንጉሤ የላከውን ደብዳቤና ገጸ በረከት አድርሰው ከሮማም ፓሪስ ከተማ ደርሰው ለናፖልዮን ደብዳቤውን አቀረቡ።

ደብዳቤውም እንዲህ የሚል ነበር። ‹‹የተላከ ከደጃዝማች ንጉሤ ይድረስ ከግርማዊ የፈንሳይ ንጉሥ ናፖልዮን ፫ኛ ሰላም ለእርስዎ ይሁን። ኢትዮጵያ ከብዙ ጊዜ ጀምራ ወድቃ አሁን

ግን ለመነሳት የራስዋ ኃይል ስለማይበቃት ከፈረንሳይ መንግስት እርዳታ ትፈልጋለች። እኔም በሀገሬ ውስጥ ባለን ዓቅም የፈረንሳዊን ጥቅም ለመጠበቅ የተዘጋጀሁ መሆኔን አንድ ሰው ልከው ሊያስመረምሩ ይችላሉ።

አሁንም በፊቴ ያለውን የካቶሊኮች ጠላት የሆነውን ቴዎድሮስን የምወጋበት መሣሪያና የሚረዱኝም ወታደር እንዲልኩልኝ እለምናለሁ። ደግሞ ለማናቸውም የሆነውን ነገር ይነግሮት ዘንድ አባ ያዕቆብ ይጠይቁ›› የሚል ነበር።

አባ ያዕቆብ ለፈረንሳይ ንጉሥ ለናፖልዮን የላከው ደብዳቤም እንዲህ የሚል ነበር ‹‹ግርማዊ ሆይ ከቴዎድሮስ ይልቅ ደጃዝማች ንጉሤን የመላዋ ኢትዮጵያ ንጉሥ መሆኑን ብታውቁለትና በማናቸውም ብትረዱት ለፈራንሳይ መንግሥት ጥቅም ያለው ነው።›› የሚል ነበር።

ይህንን ሁሉ ያደረገው አባ ያዕቆብም የፈረንሳይን መንግሥት ኢትዮጵያ ላይ በማስገባት ምክንያት ሊሆን የሚችልበትን የሠራው መሆኑን በዚህ ደብዳቤው መረዳት ይቻላል። በኋላም ናፖልዮን ብዙ የጦር መሣሪያ በያይነቱ ገጸ በረከትና የጦር ሠራዊት ኮንቲ ሩሴል የተባለውን የጦር አዛዥ ያገር ተወላጆች ሰዎችም አድርጎ ሸለቆ ለሸለቆ በሆነው ቦታ በወታደሮች እየተመሩ ወደ ምፅዋ ወደብ አድርሶ በመጡበት ወደ ሀገራቸው



www.ethiopianorthodox.org



እንዲመለሱ አደረገ። ይህንን ታሪክ በስፊው ለመረዳት ለሚፈልገው የኢትዮጵያ ታሪክ ፲፰ እስከ ፲፱ ስለ ዓፄ ቴዎድሮስ የተጻፈውን መጽሐፍ ይመልከት።

## ምዕራፍ ፳፩

### አባ ማስያስና ዓፄ ሚኒልክ

፫ኛአባ ማስያስ የተባለው በሸዋ ሆኖ ሲሰራው የነበረውን ደግሞ ባጭሩ ከዚህ በታች የምንገልጸውን ተመልከት:: አባ ማስያስ ለኢጣልያ ንጉሥ ፪ኛ አማኑኤል አበ ንስሐ የነበረና ኢጣልያ ኢትዮጵያን ለመውረር የሚሆን ምክንያት ከንጉሡ ጋር ተመካክሮ የሮማዊት ባህል የሃይማኖት ስብከትን መሣሪ አድርጎ ወደ ሐረር እናርያ ከተባለው አውራጃ የገባ ሰው ነበር:: በዚያም አገር ሲሰብክ ቆይቶ በሸዋ አውራጃም አስተምራለሁ እያለ ፪ ባሕርይን ሃይማኖት በመስበክ እየተዛዋወረ ከመኖሩ ባሻገር ከዓፄ ምኒልክ ጋር ተዋወቀና ለዓፄ ምኒልክ አንድ አንድ ምክር እየሰጠ ሲያካፍላቸው የቆየ ነው::

የሚያካፍላቸው ዋናው ምክሩም ዓፄ ምኒልክን ከዓፄ ዮሐንስ ጋር ማቀያየምን ያለመ ነበር:: ለዚህ ይረዳውም ዘንድ አስቀድሞ ከኢጣልያ መንግስት ጋር ወዳጅ አለቃ የነበረ ከ፲ መርከቦች ጋር አድርጎ ለደጃዝማች ንጉሤ ረዳት የላከለት ነበረ:: ይህንንም ሁሉ በቶሎ ለደጃዝማች ንጉሤ እንዲደርስለት አደረገ::

ከዚህ በኋላ አባ ያዕቆብ ለላከቸው ሰዎች የሮማ ሊቀ ጳጳሳት ቡራኬ ሰጥቶዋቸዋል:: ናፓልዮንም ለአባ እምነቱ ወርቅ መስቀል በዕንቁ ባሕርይና በ፲፫ ሉል ያጌጠ የወርቅ መስቀል:: ለልጅ ጸጋ ጋብርም የብር ሰገባ ጫማ ጎራዴና ማለፍያ የሆነ ጠበንጃ ሸልሞ ወደ አገራቸው ላካቸው:: አባ ያቆብም ምፅዋ ሲገቡ ተቀብሎ አኖራቸው::

ደጃዝማች ንጉሤ ካሉበት ሐውዜን ገብተው መልእክተኞቹን አባ እምነቱንና ልጅ ጸጋን ከደጃዝማች ንጉሤ ጋር አገናኝቶ እነሱም ናፖልዮን የላከውን ደብዳቤ በነሐሴ ወር ፲፰፻፹፩ ዓ.ም ለደጃዝማች ንጉሤ አስረከቡ:: ዓፄ ቴዎድሮስም ደጃዝማች ንጉሤን ከወንድማቸው ጋር ማርከው ገደሏቸው::

እነዚያ የመጡት የፈረንሳይ ወታደሮችንም ዓፄ ቴዎድሮስ የጦር ሰራዊታቸውን ልከው ካሉበት ቦታ አስከበቧቸው:: አባ ያዕቆብ ግን በካቶሊክ ሃይማኖታቸው ባሳመናቸው እምነት እንዲያደርጉና የኢጣልያ መንግሥት ለዓፄ ምኒልክ ብረትና በያይነቱ የጦር መሣሪ ሌላም አስፈላጊ የሆነውን ሁሉ እንዲሰጣቸው ያለውን ተስፋ እያረጋገጠ ስለ አስገነዘባቸው ከንጉሥ ምኒልክ ደብዳቤ ተቀብሎ ወደ ኢጣልያ መንግስት እየተላላከ ሲኖር ቆየ:: ዓፄ ምኒልክ በዚሁ ሚስዮናዊ አባ ማስያስ አማካይነት ከኢጣልያ መንግስት ጋር በደብዳቤ ግንኙነት ካደረጉ በኋላ በታህሳስ በ፲፰፻፹፫ ኣ.ም የኢጣልያ መንግስት ማርኬዝ አንቶኖሪ የተባለውን መልእክተኛ

www.ethiopianorthodox.org

ከተከታዮቹ ኢጣልያውያን ጋር ከንጉሥ ምኒልክ ዘንድ ሳከ:: ወደ ኢትዮጵያ ገብተውም ከሸዋ አውራጃ ሐር እምባ ከተባለው ቦታ ሲደርሱ ዓፄ ምኒልክ ገና ከርሳቸው ጋር ሳይገናኙ መምጣታቸውን ስለ ሰሙ አባ ማትያስን ‹‹እኒህ ሰዎች ሀገሬን ለመሰለል የመጡ ናቸውና ተመለሱ በላቸው›› ቢሉት እሱም እነዚህ ‹‹ኢትዮጵያን የሚጎዱ አይደሉም›› እያለ በብዙ ምሳሌ እያስረዳ በተናገራቸው ጊዜ ንጉሥ ምኒልክ ተቀብለው አነጋገሯቸው::

አባ ማቲያስም ይህን ግንኙነት ማድረጉ የጦር መሣርያ ለዓፄ ምኒልክ ሰጥቶ ዓፄ ዮሐንስን እንዲወጉለት ሲል ነውና የኢጣልያ መንግሥት የላካቸውን ደብዳቤና ገጸ በረከትን መልእክተኞቹ ለንጉሥ ምኒልክ አበረከቱ::

ይህን ሁሉ ያደረገውም የሮማዊት ቤተ ክርስቲያን ሐዋርያዊ ሰባኪ ተብሎ ኢትዮጵያን ለመውረር ምክንያት የሚሆነውን በመሥራቱ ማውረሲዮኒ ሳዘሮ የተባለውን በቅዱሳኖቻቸው ስም የተሰራ ኒሻን ከንጉሥ ምኒልክ ፊት መልእክተኞቹ ለአባ ማቲያስ ሸልመውታል::

## ዓፄ ዮሐንስ

ነገር ግን ዓፄ ዮሐንስ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ ከኢትዮጵያ ከመሬቷ ስንዝር ከአፈሯ እፍኝ ያህል አልሰጥላትም እያሉ



www.ethiopianorthodox.org



ኢትዮጵያን የውጭ ሰው ጠላት እንዳይገባባት በማለት ቀኝና ግራ እየሮጡ ሲጠብቁዋት ኖረዋል:: ከእግዚአብሔር አደራ የተቀበሏትን ሀገር በጥንቃቄ ሲጠብቋት ስለ ነበሩ እኒዚያ የወንጌላዊት ሃይማኖት ወንጌል እናስተምር እያሉ ከውጭ ከሲዊድን አገር የመጡትን ሚስዮናውያንና እነ አባ ማስያስ እነ አባ ያዕቆብንም ሳይቀር ጠርተው ሰብስበው ‹‹ከኢትዮጵያ ምን ልትሠሩ መጣችሁ?›› ቢሏቸው እነሱም ሳያፍሩ ‹‹ወንጌል ለመስበክ ነው›› አሏቸው::

ዓፄ ዮሐንስም ‹‹ወንጌል አንዲት ናት እግዚአብሔርም አንድ ነው:: ሕዝቤንም የሚያስተምሩ በቂ የሆኑ መምህራን ካህናትና ሊቃውንት ጳጳሳትም አሉኝ ማንን ልትሰብኩና ልታስተምሩ ነው የመጣችሁ›› ቢሏቸው እነሱም ከዚህ ሀገር ላሉት አይሁድ (ፍላሻ) እና እስላም ሲሉ መለሱላቸው:: ዓፄ ዮሐንስም ‹‹ከዚህ ሳትመጡ አስቀድማችሁ ያገኛችኋቸው በኢየሩሳሌም ያሉ አይሁድና እስላም ነበሩ እነሱን ሳታስተምሩና ሳታሳምኑ እንዴት ብላችሁ ከዚህ መጣችሁ›› ቢሏቸው ‹‹አሜሃ ይብህም አፍ ወልሳን ዘይነብብ ዓመፃ›› እንዳለው ያዕቆብ ዘስሩግ መልስ መስጠት አቅቶአቸው ከንጉሡ ፊት ቁመው እየተያዩ ቁልጭ ቁልጭ ሆነና ዝም አሉ::

ንጉሡ ግን ‹‹በሉ ስለወንጌል ቃል ስል ለሰውነታችሁ ምሕረት አድርጊላችኋለሁ አሁንም ላገሬ ሕዝብና ለመንግሥቱ የሚያስፈልገኝ የእጅ ጥበብን የሚስተምሩ መምህራን የምንጣፍ የሕንፃና የንግድ የብረታ ብረት ቀጥቃጭነት የሚያስተምሩት እንጅ ኢትዮጵያ ለወንጌል ትምህርት የራሷ መምህራን ስለሚበቋት እናንተንና እናንተን የመሳሰሉ አያስፈልጋትምና ሀገሬን ልቀቁልኝ›› ብለው እከላቸውን በምፅዋ እከላቸውን በመተማ አባረሯቸው::

ይህንንም ለጊዜው እንጅ ጥቂት ቀን ቆይተውስ በምጥዋ የሄደው ኤርትራን በመተማ የሄደው ድርቡሽን አሥነስቶ የንጉሡን ሕይወት አስይዘው ኤርትራ ኢትዮጵያን በኢጣልያ ለማስወረር ሞክረዋልና በባዕዳን ሃይማኖት መልእክተኞች ያመጡትን ተንኮል ሳይፈጽሙ አልቀሩም:: የነዚህ ሰባክያን ሥራ ባጭሩ ይህ ነው::

በዚህ አዲስ ሃይማኖት እናስተምራለን ብለው መጥተው ዓሰብን የባህር ወደብ ይዘው በነበሩት ሰዎች ምክንያት የ፪ ባሕርይ ሃይማኖት ሰባኪው አባ ጁስቴ የሮማ መንግስት ኢጣልያንን አውርሶ የገዛውን ርስት ለኢጣልያ መንግሥት ሠራዊትና መሣሪያ መደበር እንዲሆነው በሰጠው መሰረት ከዚያ ሠራዊቱን ሰብስቦ ቆይቶ ምጥዋን ለመያዝ በቃ:: ከምጥዋም አሥመራ





ከተማውን አድርጎ ሞላው ኤርትራን ለመግዛት ቻለ:: በዚሁም አባ ጁስቴ ሳፔቶ ቅዱስ ተብሎ በሥዕሉም ቅዱስ እያሉ በኢጣልያ ሀገር ይሰግዱለታል::

በኤርትራም አባ ያዕቆብ ጂያስኮቦ የተባለው ሰው በአከለ ጉዛይ አውራጃ ተደብቆ ሲኖር የኢጣልያ ሠራዊት ኤርትራ በገባ ጊዜ የ፪ ባሕርይን ሃይማኖት እያስተማረና የሮማን ታሪክ በሚያስደስት ትምህርት እየሰበከ እያሌ ሰዎች አሳምኖ ነበር:: የኢጣልያ መንግሥትም ኤርትራን በመግዛቱ ተደስቶ ሲኖር አባ ያዕቆብ በሰበከላቸው በአዲሱ ሃይማኖት አምነው ያጸድቀኛል በማለት እጅግ ብዙ የአባቶቻችን ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ትተው አምነውበት የነበረውን አዲሱን ሃይማኖት ለአገር መውረርያና የባዕዳን መንግስት መስፋፋት ምክንያት እንዲሆን አደረጉት:: ኢጣልያ ኤርትራን ይዛ ስታበቃ ባንዲራው አሥመራ ላይ የተከለበት ቀን ሐምሌ፲፮ ቀን ፲፰፻፹፩ (161881) ዓ.ም ሲሆን ከ፯ ዓመት በኋላ ኢትዮጵያን በመላዋ ለመውረር ጦራቸውን ማዘጋጀት ጀምረው ነበር::

በዚህ ጊዜም ክቡር ጀግናው **ደጅአዝማች ባህታ ሐጎስ** ይህን አዲሱን ሃይማኖት የሰማዩን መንግሥት የማያወርስ አገኘን ብለው በአባ ያዕቆብ የተሰበከላቸውን አዲሱን ሃይማኖት አምነው ብዙ ሰውንም በዚህ አዲሱ ሃይማኖት እመኑ እያሉ

www.ethiopianorthodox.org

ሲያሳምኑ የነበሩት ወደ መንግሥት ስማይ የሚያገባ የጴጥሮስ ሊቀ ሐዋርያት ሃይማኖት አገኘን በማለት አምነውበት ነበር፡፡ ኂላ ግን እላይ በተጠቀሰው ዓመት ያንን ሃይማኖት ተመርኩዞ በእነ አባ ጄዘገ ሳፔቶ በእነ አባ ያዕቆብ ስብከት ገብቶ ኤርትራን በገዥነት የያዘ የኢጣሊያን መንግሥት ኢትዮጵያን ለመውረር ጦር ሠራዊቱን አዘጋጅቶ በተነሣ ጊዜ እኒህ ጀግናው ስመ ጥሩ የሆኑት ክቡር ደጃዝማጅ ባህታ ሐጎስ በሃይማኖት ስብከት በማታለል ገብቶ ሀገርን ለመውረርና መንግሥቱን ለማስፋፋት መሆኑን ተረድተውና የተንኮሉን ሥራ ተመልክተው ከተጸጸቱ በኂላ ኢትዮጵያን ለመርዳት ሲሉ ሀገሬን አሳልፌ አልሰጥም፡፡ በማለት ከራስ መንገሻ ዓፄ ዮሐንስ ጋር ተላልከው ስገነይቲ የነበረው ጣልያንን አስረው ሲያበቁ ከኢጣሊያ ሸፍተው ወደ ራስ መንገሻ ዘንድ ወደ ትግሬ ሀገር ሄዱ፡፡ ሐ.ደውም በመተባበር ጣልያንን ወግተን ከሀገራችን እናስወጣዋለን በማለት ከሰገነይቲ ተነስተው ልዑል ራስ መንገሻን ለመገናኘት ወጡ፡፡ ወታደሮቻቸውን አስከትተውም ትግሬን ለመሻገር ሲጉዋዙ ሐላይ ከተባለው መንደር ሲደርሱ ታኅሣሥ ፳፯ ቀን በ፲፰፻፹፯ (1887) ዓ.ም የኢጣሊያ የጦር ሠራዊት ደርሶባቸው የኢጣሊያ ጦር ሠራዊት ጋር በጀግንነት ተዋግተው በጦር ሜዳ ላይ ሞቱ፡፡



www.ethiopianorthodox.org



ይህም የሆነው **ከልዑል ራስ መንገሻ** ተላልከው ልዑል ራስ መንገሻም ከትግሬ የጦር ሠራዊታቸውን አስከትተው ተነስተው ከደጃዝማች ባህታ ለመተባበር በመንገድ ላይ ሳሉ ራስ መንገሻም መምጣታቸውን ኢጣሊያ አውቆ ሳይደርሱላቸው ጦርነቱ ስለ ገጠማቸው ነው እንጂ ራስ መንገሻ ደርሰውላቸው ተባብረው ጦርነቱ ተደርጎ ቢሆን ኖሮ ሳያሸንፉ አይቀሩም ነበር፡፡

## ምዕራፍ ፳፪

ከዚህ በኋላ የእኅታቸው ባለቤት የሆኑት ፊተውራሪ ተስፋ ብእምናይ የተባሉ የኩዓቲት ባላባት ‹‹ባሕታን ያህል ሙቶ ይቀራል›› በማለት ትግሬ ተሻግረው ሒደው ደጃዝማች ባሕታ ተዋግተው መሞታቸውን ለልዑል ራስ መንገሻ ነገሯቸው:: ልዑል ራስ መንገሻም ከእንደርታ አውራጃ ዓይባ ከተባለው ሀገር ሠራዊታቸውን አስከትተው ከትግሬ ወደ ኤርትራ ተሻግረው እስከ ኩዓቲት ድረስ በፊተውራሪ ተስፋ እምናይ እየተመሩ መጥተው በኩዓቲት ላይ በየካቲት ወር ሽ፰፻፸፯ (በኢት) 1985 (በፈ.) ከፍ ባለ ጀግንነት ከኢጣልያን ጋር ተዋግተው ድል ሆኑ፤

በዚሁ ጠንቅ ጣልያኖች ኢትዮጵያን ለመውረር የመጡበት ምክንያት የዓድዋ ጦርነትን አስከተለ::

በዚህም ጊዜ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን አሳልፎ ስለልሰጣት ግርማዊ ዓፄ ምኒልክ ጣልያንን ድል አድርገው ኢትዮጵያንም ከወራሪ ቢያድንዋት ከመረብ አንስቶ እስከ ምዕዋ ያለው ሀገር ዋንና ድንበርዋን ኢጣልያ ስትጠባበቅ ፵፯ ዓመት ሲሆናት ሕዝንም በጭቆና አገዛዝ ቆየች::

ይህም አሁን ኤርትራ ተብሎ የሚጠራው ሀገራችን ከጥንት ጀምሮ ትግራይ ትግሪኝ ተብሎ ጠቅላይ ግዛቱ ሲጠራ በክፍል



www.ethiopianorthodox.org



ከመረብ ወዲህ ሐማሴን ከመረብ ወዲያ ትግራይ ተብሎ ይጠራ የነበረው ነው::

ኢጣልያ ከገዛ በኋላ ግን ለፖለቲክ እንዲመቸው ሲል የኢጣልያ መንግሥት ከእንግሊዝ መንግሥትና ከፈረንሳይ መንግሥት የኮሎንያን ግዛት የወሰን ክልል ውል በተፈራረሙበት ጊዜ በሱዳን በኩል ከእንግሊዝ ጋር የከሰላ ግዛት ብላታ ገብሩ የተባሉት የዓፄ ዮሐንስ ሹም ሲገዙት የነበረውን የመታሕት አውራጃ ክፍል የሆነ ለገንዘብ ዕዳ ምትክ ይሆን ዘንድ ኢጣልያ ከእንግሊዝ መንግሥት ብድር ስለ ነበረባት ስለ ገንዘቡ ፋንታ የከሰላ ግዛትን ለእንግሊዝ መንግሥት አሳልፎ የሰጠበት ጊዜ በሽህ ፰፻፺፬ (በፈ.) 1902) ዓ.ም ነው::

ከዚያ በፊት ያለው በዓፄ ዮሐንስ ጊዜ ልዑል ራስ አሉላ ሲገዙት የነረበውን ሀገር ከመረብ ምላሽ እስከ ምፅዋ ያለውንም በዚያን በ1902 (በፈ.) ፲፰፻፺፬ ዓ.ም በወሰን ክልል በተዋዋሉበት ውል ከተፈራረሙ በኋላ በዚሁ ዓመት **ሐማሴን** ስትባል የነበረችው መረብ ምላሽ በባሕርዋ ስም **ኤርትራ** ተባለች::

ይህም የሆነው ከላይ በተጠቀሰው ዓመተ ምሕረት በጀነራል ማርቲኖ ነው::

እንዲህ አድርጎ በእነ አባ ጁዜፔ ሳፔቶ በእነ አባ ያዕቆብ የሃይማኖት ሰባክያን ምክንያት መንገድ ተጠርጎለት የገባው የኢጣሊያ መንግሥት ሕዝቡ የዕውቀትና የሥልጣኔ ትምህርት እንዳይማር በማለት ወደ አዲሱ እምነት አምነው ለሚኖሩ ልጆች በያሉበት የጣልያን ትምህርትን የሚማሩበት ትምህርት ቤት (እስኮላ) ሲሠራ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ልጆች የሚማሩበት ግን መንደፈራ ላይ አስኮላ ሳን ጊዮርጆ የተባለው ብቻ ነበር። ከዚህም የመኳንንት ልጆች በስተቀር የተራ ሕዝብ ልጆች ትምህርት ለመማር ለመግባት ክልክል ነበር።

ይህም የዕውቀት ትምህርት ለሐበሻ ወይም ለኤርትራ ልጆች ከሦስተኛ ክፍል በላይ ለመማር ክልክል ሆኖ ነበር። ኋላ ጀነራል ጋስፓሪኒ የተባለው ኢጣሊያዊ ሀገረ ገዥ የኤርትራን ሕዝብ የሃይማኖት ሹሞች እስላምና ክርስቲያን የኦርቶዶክስ የካቶሊክና የወንጌላዊት ኋላፊዎች የሆኑትን ቤተ ክህነት አስፈርሞ የተፈረመውን ዕቡነ መሠረት ጥሎ አስቀምጦ፡ በ1925 (በፈ) ፲፱፻፳፭ (በኢ.ት) ክርስያንና እስላም የሆነውን ወገን ሁሉ የተራ ሕዝብና መኳንንት ልጆች በኅብረት ጣልያንኛ ቋንቋ የሚማሩበት እስኮላ ከፈተ። ይህም ቪቶሪዮ ተብሎ አሁን መንግሥታችን ከመጣልን ልዑል መኮንን ት/ቤት አሥመራ ላይ የሚገኘውን ት/ቤት አሠርቶ አስመርቆ በደምብ



www.ethiopianorthodox.org



የሐበሻ ልጆች አንድነት ሁነው እስከ ፫ኛ ክፍል የሚማሩበትን ተከለ። ከዚያም ወዲህ እየተማሩ ሲኖሩ ሳለ ጎቨርናቶረ ጋስፓሪኒ ወደ ኢጣሊያ ተዛውሮ ከሄደ በኋላ። ሌላ ፋሺስታዊ ጎቨርናቶረ ዳውዲያቺ የተባለው ሰው በስተኋላው ተሾሞ ወደ ኤርትራ ሲመጣ የሐበሻ ልጆች በቂ ትምህርት ካገኙ የባርነትን ነገር ተረድተው ኢትዮጵያ እያሉ ሊሸፍቱብን አይደለም? በማለት ከአራተኛ ክፍል በላይ **እንዳይማሩ ክልክል እንዲሆን አገደው።**

እሱ ወደ ኢጣሊያ ተዛውሮ ሌላ ጀ አስቱቶ የተባለ በስተኋላው የመጣው ጎቨርናቶረ ደግሞ የሐበሻ ልጆች ከሦስተኛ ክፍል በላይ የእውቀት ትምህርት እንዳይማሩ ክልክል አድርጎት ነበር።

## ምዕራፍ ፳፫

## ስለኢጣልያ መንግሥት የግፍ ሥራ

ከዚህ በኋላ ኢጣልያ በ፲፱፻፴፭ በፈ. 1935 ዓ.ም በኢትዮጵያ ላይ ወረራ ፈጽማ ያደረሰችው ሥቃይ ውርደት መከራ እስራትና ግርፋት እንዲሁም ሞት በኤርትራና በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የፈጸሙት ግፍ ሁሉ በዓለም ተደርጎ ታይቶ የማይታወቅ ነበር። ፋሺስት ኢጣልያ ከፈጸመችው የግፍ ሥራ ከብዙው ጥቂቶቹን እዚህ እንጠቅሳለን። በኢትዮጵያ ላይ የሕዝቡ የግፍ እልቂት ወሰን የሌለው እልቂትና አብያተ ክርስቲያናትን ማቃጠል የተፈጸመባት ሲሆን በኤርትራ ሕዝብ ላይም የተፈጸመው ከብዙ አንድ አንድ የምንጠቅሰው የሃይማኖት ተጽእኖና የሕዝቡን ውርደት ነው።

ፋሺስት ኢጣልያ አላይ በተባለው ቦታ ኢትዮጵያን በወረራ በያዘች ጊዜ የኤርትራ ልጆች የቋንቋቸውን የሐበሻ ትምህርት እንዳይማሩ ተከለከሉ። የኢጣልያ ቋንቋ ብቻ ካልሆነ በቀር በሁሉ ትምህርት ቤት ክልክል እንዲሆን የወንጌላዊት ትምህርት ቤትና ማተሚያ ቤትን ዝግ እንዲሆን አደረገ። በኋላ ሰኔ ከ፲፱፻፲፱ በፈ..1927 ዓ.ም ጀምሮ በኢትዮጵያ ቋንቋ ግዕዝ አማርኛና ትግርኛን በማመስተማር ላይ ለነበርኩት ለርእሰ ደብር ዕቁበ እንድርያስም በኢጣልያ መንግሥት በጎቨርናቶሬ ጋስፓሪኒ

www.ethiopianorthodox.org





ለወር 90 ዘጠና ፍራንክ ተቀጥሬ የማስተምርበትን ፫ ክፍል ቤትና መኝታ ቤት ማዕድ ቤት ከነግቢው መብራትና ውኃ መንግሥት የሚከፍለው ያለበት ግቢ ተሰጥቶኝ እያስተማርሁ ስኖር እንዳልነበር ኢትዮጵያ በ፲፱፻፳፰ ዓ.ም በኢጣሊያ ፋሺስት ከተያዘች በኋላ ሐምሌ ፳፩ ፲፱፻፳፱ በፈ.1937 ዓ.ም የኔን ደሞዝ ነሥተውኝ የሰጡኝንም ትምህርት ቤትና መኝታ ቤት አስለቀቁኝ።

እኔም ሄጄ ወደ ኮሚሳርዮ ሎቤሎ ብጮኽ እሱም እኔ አላውቅም። አፋሪ ፖለቲኪ ነው የሚያውቅ ብሎኝ ወደ አፋሪ ፖለቲኪ ጠቅላይ ግዛት ለመጮህ ሔድኩ። ዶቶር ቢቫ በሚባለው ሰግሬቴር ከቢሮው ጽሕፈት ቤቱ ነገሬን ለመስማት ግባ ብሎኝ ስገባም ያ የአፋሪ ፖለቲኪ (ጠቅላይ ግዛት) ሹም ኮመንዳቶሬ ሳንማርኮ በድንገት መጥቶ እኔን ዓይቶ፤ ከሰግሪቴሩም (እንደራሴ) ጽሕፈት ቤት ገባና ወንበሩን ሳብ አድርጎ ተቀመጠ። ይህ ሰው ምንድን ነው የሚለው? ሲልም በብርቱ ቁጣ ቃል ሰክረቴሩን ጠየቀው። እኔንም በዓይነ መዓት እያየ ተናገረው። ሰክረቴሩም እኔ አሁን ነው ግባ ያልኩት ነገሩን ገና አልሰማሁትም አለው።

ኮማንዳቶሩም በገዛ እጁ እኔን ሲጠይቀኝ (አነጋጋሪ አስተርጓሚ) ክቡር ደጅአዝማጅ ተድላ ተክላይን ጠርቶ አምጥቶ ምንድን

ነው የሚለው አለው፡፡ እኔም ጌታዬ የኢጣሊያ መንግሥት በሐበሻ ትምህርት አስተምር ብሎ ትምሕርት ቤትንና ለኔም በደመወዝ ቀጥሮ ካስቀመጠኝ ጊዜ ጀምሮ 10 አስር ዓመት ያህል እያስተማርሁ ስኖር ቆይቼ ነበር አሁን ግን ትምህርት ቤቱን ዘጋው ትምህርቱንም አታስተምር ደሞዝም ከሐምሌ ፳፩ ቀን ፲፱፻፳፱ ዓ.ም ጀምሮ የለህም ብሎሃል መንግሥት አሉኝ፡፡ ስለዚህ ትምህርት ቤቱ የተዘጋው በኔ በደል እንደሆነ በደሌን እንድትገልጹልኝ ወይም በሥራ ያጠፋሁት እንዳለ ልትገልጹልኝ ስል አቤቱታዬን ለመንግሥት ለማመልከት ነው የመጣሁት አልሁት፡፡

ኮማንዳቶሪውም ትምህርት ቤቱን እንዲዘጋ ያደረግነው ባንተ በደልና ጥፋት አይደለም፡፡ መንግሥት ተማሮቹ የሐበሻ ትምህርት እንዳይማሩ ስለ ከለከለ ነው፡፡ ተማሮቹ እንማራለን ካሉም የኢጣሊያ ትምህርት ወደ እስኮላ ቪቶርዮ ሄደው ይማሩ ሲል መልስ ሰጠኝ፡፡

ከዚህ በኋላ እኔም በልቤ ኢትዮጵያ ጠፍታ ኢጣልያ የኢትዮጵያ ባለባቶቿንና ቋንቋዋን አጥፍተው የኢትዮጵያውያንን ርስት ይዘው ኢጣልያውያን ርስታቸውንና ቋንቋቸውን አስፋፍተው ለመኖር ያላቸውን ምኞት መፈጸማቸውንና ቋንቋዋን ለማጥፋት ያቀዱት ሐሳብ ከልቤ ተደቀነና ‹‹ምነው እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ያችን ለም ሀገር አሳልፎ ሰጥቷችሁ ትምህርትን በማስፋፋት ፈንታ በዚህ ክፉ አሳባችሁ ሕዝብዋንና ቋንቋዋን ለማጥፋት ተነሳችሁ? ብዬ ከልቤ ንዴት የተነሣ ኮማንዳቶሪው እንዲገድለኝ ስል ጠረጴዛውን በእጄ እየመታሁ ስማ ብዬ ‹‹ኢትዮጵያን ልታጠፉ አሰባችሁ? ኢትዮጵያ አትጠፋም እናንተና አሁን ግፍ የምትሠራ ያለች የኢጣልያ መንግሥት ግን በአጭር ዓመታት ትጠፋለች የሠራችሁትና ያሰባችሁት ግፍ ያን ጊዜ በናንተ ይደርሳል›› ብዬ በግልጽ እንዲገድለኝ ስል በቁጣ ተናገርሁት፡፡

ኮማንዶቶረ ሳንማርኮንም ተናደደና ከወንበሩ ተነሥቶ ምንድር ነው ያለው ሲል አነጋጋሪውን(አስተርጓሚውን) ክቡር ደጃዝማች ተድላ ተክላይን ጠየቃቸው፤ ክቡር ደጃዝማች ተድላም እኔን እንዳይገድለኝ ሲሉ ‹‹አታስተምር ብላችሁ ትምህርት ቤቱና ደሞዜን ከነሣችሁኝ ለኔም እግዚአብሔር ያውቅልኛል›› ነው ያለ አሉት፡፡

ኮማንዶቶረውም (ኖን ፓርላንቶኩዚ) እንደዚህ አይደለም የተናገረው አለ፡፡ እኔም ልሞት ስለ ቈረጥሁ ‹‹በግለጥ ንገሩት ከመግደል አልፎ ምን የሚያደርገኝ ነው? ኢትዮጵያ ጠፍታ ከማየት መሞት ይበልጠኛል›› ንገሩት አልኳቸው፡፡

www.ethiopianorthodox.org

እርሳቸውም ከአሁን አሁን ሊገድለው ነው በማለት እየተንቀጠቀጡ እንደ ተናገርሁት ‹‹እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ያህል ሰም ሀገር አሳልፎ ሰጥቷችሁ ሲያበቃ እናንተ ጣልያኖች በጎ ነገር በመሥራት ፈንታ መንግሥቷን አጥፍታችሁ ቋንቋዋንም እናጥፋው እያላችሁ አይደለምን? አሁን የሐበሻ ትምህርትን ልጆችዋ እንይማሩ መንግሥት ከልክሏል የምትለኝ እንግድያስ ኢትዮጵያ አትጠፋም። እናንተና ኢጣልያ ግን በቅርብ ዓመታት ትጠፋላችሁ›› ብሎ ነው የተናገረው ሲሉ የተናገርሁትን ገልጠው ተናገሩት።

ኮማንዳቶሬ ሳንማርኮም ነገሩን በሰማ ጊዜ እኔ አሁን ይገድለኛል ብዬ ሞቴን ሳስብ እሱ እህ ብሎ ደንግጦ ወደ ጠረጴዛው ተደፍቶ ብዕሩን አንስቶ ጠረጴዛውን እያንኳኳ በብዕሩ ላይ ተደፍቶ ሳየው በምን ልግደለው እያለ ነው የሚያስብ ብዬ አንገቴን ወደርሱ አቅንቼ ለመሞት ስዘጋጅ እርሱም ሩብ ሰዓት ልክ ዝም ብሎ ብዕሩን ሲያንኳኳ ቆይቶ ያ ሁሉ ለማየት ብቻ እንኳ የሚያስፈራ ቁጣው በርዶ እንዲህ ሲል ተናገረኝ።

‹‹ይህ መንግሥት ሕፃናቱ የሐበሻ ትምህት እንዳይማሩ አንድ ጊዜ ወስኗል። በመንግሥት ውስጥ ልታስተምር አይቻልም። ነገር ግን በፈቃድህ አስተምራለሁ ያልህ እንደሆነ እኔ



www.ethiopianorthodox.org



እንደፈቃድህ ልታስተምር ፈቃድ ልስጥህ መንግሥት ግን አይረዳህም›› ሲል መልስ ሰጠኝ።

እኔም ‹‹አታስተምር አትበሉኝ እንጂ የመንግሥት እርዳታ አንድ ነገር አልፈልግም›› ስል መልስ ሰጠሁት። እሱም እንግዲያስ እንደፈቃድህ አስተምር ሲል የፈቃድ ወረቀት ሰጥቶኝ የማስተማር ሥራዬን በራሴ አከናወንኩና ዕዳጋ ዓርብ ላይ ትንሽ እንደ ዳስ መሰል ሠርቼ የማስተማር ሥራዬን ቀጠልሁ።

የኢጣልያኖች ግፍ መቼም ተወርቶ አያልቅም። ኃሳባቸው የነበረው ሀገራችንን መሬታችንን ተረስተው የራሳቸው ሀገር አድርገው የኢጣልያ ሕዝብ መጥቶ በኢትዮጵያ ርስት እንዲመሠረት የኛ ኤርትራና ኢትዮጵያ ሕዝብም ወደ ስሃራ በምድረ በዳ በአይሮፕላን ወስደው እየጣሉ እንዲያጠፋት እንደነበር በኢጣልያ ቋንቋ ተጽፈው የሚገኙ መጻሕፍት ምስክር መሆናቸውን እየገለጽሁ በኔም በግፍ ሥራቸው የደረሰብኝና ያጋጠመኝን ጭንቅ ለመጪው ትውልድ አሳስባለሁ ።

ከሚባለው ከተማ ሰብስበው ወንድ የሆነው ባንድ ወገን ሸክፈው ከሜዳ ማይ ጓይላ ከሚባለው ወንዝ ከመስኩ ላይ ፎቶ የምታነሳው መኪና አቁመው፡ በሌላ ቦታ እንዳደረጉት ሕዝቡን ከ፪ ከፍለው ፪፻ የሚሆኑ ፈረሰኞች ጦርና ጋሻ ጉራዴና ሰይፍ አስይዘው፡ ባንድ ወገንም እንደዚህ ፈረሰኞች የቀረው በእግር ያለው ሰው ሁሉ እኩል ጦርና ጋሻ እኩል ድንጋይና ሽመል የያዘ ባንድ ወገን አሰልፈው አንድ ሰው መልእክተኛ ቡስጣ ወረቀት የያዘ አድርገው።

ባንድ ክፍል ዓፄ ዮሐንስ ባንድ ክፍል ዓፄ ምኒልክ ብለው ስያሜ እየሰጡ ፪ የኢጣልያ ክልስ ሰዎችን አድርገው ዓፄ ዮሐንስ በተባለው የኢጣልያ ክልስ (ሲልቢስትሪ) መልእክተኛነት ወስዶ ሲሰጠው እርሱም ወረቀቱን አንብቦ ሲያበቃ ‹‹ንጉሡ ምኒልክ እምቢ አለ እንግዲህ ክተት ሠራዊት ምታ ነጋሪት ብለህ አዋጅ አስነግር አሉና አንድ ኢጣልያዊ ሰው አስነሥቶ ኩናት ኩናት እያልህ ጩህ ብሎት እርሱም ኩናት ኩናት እያ ፈረሰኞቹም ፋሺሽቱ እንዳዘዛቸው በዓል ሐመር በዓል ሐመር በዓል ሐመር እያሉ ድንፋታና ሁካታ ሆነ ያን ጊዜም እኒያ አንድ ክፍል ወደ አንዱ ክፍል ገቡባቸውና እነዚያ ፈረሰኞቹም ድብልቅልቅ ማለት ሆነ። በዚህ ያላችሁ ተሸረናል በሉ ሲላቸው ተሻርን ተሻርን ይሉ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org



በዚህ ላይ ከቃላቸው ወይም ከቲያትር ሥራው አንድ ነገር ቢዛባ እንደ ገና መልስ እየተባለ ሲገደድ ሰነበተ። ሰውዬው ደክሞት አርፋለሁ ብሎ ቢቀመጥ ወይም ለማረፍ ገለል ቢል የመንግሥት ዘበኞች አሉና ተነሥ እያሉ የተቀመጠውን ሰው በኮርማጅ (ባለንጋ) እየመቱ ያስነሱት ነበር። እንዲህ ሲደረግም ሴቶች ዋይ ዋይ እያላችሁ ጉንጫችሁን ምቱ እያሉ በዘበኞች ጉንጫቸውን እያስመቱ በእንዲህ ያለ በሌላም ክፉ ነገር ሕዝቡን እየተዘባበቱበት ሰነበቱ። እንደገናም ሴቶችን ሰብስበ ዕራቁታችሁን ሁናችሁ ታዩ አላቸው። ከመስኩ ላይ ይህ ሁሉ ሲሆንም ፊልሙን የምታነሳ መኪና ከዚያ አለችና የተደረገውን ሁሉ መፎቶግራፍ ታነሳ ነበር።

ሴቶቹ ግን ምንም ቢሆን ዕራቁታችንን አንወጣም አሉ። ይህን ጊዜ ሰው ሁሉ በኃዘን አዘቅት ተክዘና የዓይኑ ልቡናውን እንባ ወደ ሰማይ ረጨ። ይህን ቃል ከፋሽስት የሰማ ፊተውራሪ ገብረእግዚእ (አሁን ደጃዝማች) የተባለው የተክለ ዓገባ ወረዳ ምስሌኔ ሀገረ ገዥ ግን እነዚህ ሴቶች ፊት እኔን ግደለኝና በኋላ እነሱን ዕራቁታቸውን ታቆማቸዋለህ እንጂ እኔ ሳልሞት ምንም ቢሆን እራቁታቸው አይቆሙም ሲሉ ተናገሩት። እንኪያስ እንዳሉ ከባሕሩ አፋፍ ሴቶችን አቅርበ ካፋፉ አቆማቸውና

ከባሕሩ ውስጥ የተጣለውን ጥላቸውን የዕርቃንታቸው ሃፍረትን በፎቶግራፍ አነሳ።

ይህንንና ሌላውን የግፍ ሥራ በማድረግ በተሰበሰቡት ሕዝብ ሲጫወቱባቸው ስንብተው አሥመራ ያለውን ሕዝብ ደግሞ እንዲሁ ለማድረግ ወደ አሥመራ ተዛወሩ።





## ምዕራፍ ፳፭

ፋሽስት ኢጣልያኖች አሥመራ መጥተው በሕዝብ ላይ ካደረሱት የግፍ ሥራ አንዱ በቤተ ክህነት ቅድስት ማርያምና አካባቢ የአገር ቤትን ሰው በዓለም ሕዝቦች ፊት መዛበቻ ለማድረግ የሥረዓተ ክህነትን ሕግ በልግጫ ለማሳየት የተሞከረው ሙከራ አንዱ ነው። በመላው ሐማሴን አብያተ ክርስቲያናትን አልባሳት ንዋያተ ቅዱሳትና ጽንሐ የአሥመራ አከባቢም ካህናት የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያ አልባሳት ንዋየ ቅድሳትና ጽንሐ ካህናትና መዘምራንን ያለ ውድ በግድ ሰብስበው ያሾፉ ነበር። ከሰኔ ፳፱ ቀን እስከ ሐምሌ ፲፱ ፲፱፻፴፩ በፈ. 1939 ዓ.ምም ገጀረት አጠገብ ባለው በሳንፍራንቸስኮ ቤተ ክርስቲያን የኢጣልያ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በነበረው ሕንፃ ሰብስቦ ካህናቱ ልብሰ ተክህኖዋቸውን ለብሰው መዘምራኑ የወርቅ በዓውደ ዓመት የሚለብሱት ልብስ ለብሰው ኢጣልያ እንደ አዘዘ በግድ ያለ ውድ ሲሆኑ ይውሉ ነበር። ከላይ ከተባለው ቀን ጀምሮ፤ በየቀኑ ከቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን አሥመራ ከጥዋቱ በፈ. በ፰ሰዓት በኢትዮጵያ በ፪ሰዓት በመኪና አሳፍሮ ወደ ሳንፍራን ቸስኮ ቤተ ክርስቲያን እየወሰደም ከውስጥ አግብቶ በየወንበሩ እያስተቀመጠ እያስነሳ የፌዝ ነበር።



www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ክርስቲያኑም በኤለትሪክ ደምቆ ብርሃኑ ልክ የቀን ፀሐይ ይመስል ነበር፡፡ ከየአብያተ ክርስቲያኑም የተሰበሰቡት ከሺ (1000) በላይ የሚሆኑ ጽንሐሆች በቤተ ክርስቲያን በጣራው ተሰቅሎ ነበር፡፡

ድምፅ የምታነሣው ፎቶግራፍ የምታነሣ ቴሌቪዢን መኪናዎችም በየተመደበላቸው ቦታ ከቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ ተቋቁመው ሥራቸውን በመሥራት ላይ ነበሩ፡፡

ከዚህ በኋላ የኢትዮጵያ ጳጳሳት የመዓርገ ክህነትና ዲቁና እንደምን አድርገው እንደሚሰጡ መዓርገ ክህነትና ዲቁናን የሚቀበሉትም ለጳጳሱ ምን ገንዘብ ሰጥተው መዓርገ ክህነትና ዲቁናን እንደሚቀበሉ በፊልሙና በቴሌቪዥን በማንሳትና ለዓለም መላገጫ ለማሳየት ሲሉ ኢጣልያኖች ሴልቨቢስትሪ የተባለውን የፖሊስ አስፔቶሪ የኢጣልያ ክልስ (ሐንፊፀ) የጳጳስ ቆብና ልብሰ ጵጵስናን አልብሰው ስሙንም አባ ማስያስ የሚል ስም ሰይመው፡ ከወንበሩ አስቀመጡት፡፡ አሞሌ ጨው የሚመስል ዕንጨት ጠርበው ከአዳራሹ አምጥተው አስቀመጡትና ከኛ አንድ ቄስ ዘርአ እግዚእ ተስፋ ዮሐንስ የተባሉትን አቡነ ቀሲስ ብለው አስነሡ፡፡

ከዚህ በኋላ ወጣቶችን ተማሮች በየአንድ አንድ እያስነሡ ያንን አሞሌ ጨው አስይዘው ተጎንብሶ ወደ ጳጳሱ ይሄድና



www.ethiopianorthodox.org



አሞሌውን አበርክቶ ጳጳስ የተባለው በመስቀሉ ባርኮ ቱ ጥሬቲ አንተ ቀስሃል ማለት ነው፤ ቱ ፕሬቲ እያለ ሲያሰናብታቸው ይውላል፡፡ ከዚህም ማኽል መዘምራኑን ወረብ ወርቡ ይለናል፡፡ እኛም መዘምራኑም ንጉሥኪ ጽዮን ኢይትመዋዕ ለፀር ወኢየኃ ድጋ ለሀገር ብለን እንዘምር ነበር፡፡

ወረቡን ስንዘምር የፊልሙ አንሺ ዋና አዛዥ ይደሰት ነበር፡፡ ይህም በግዕዝ ቋንቋ በመሆኑ ምሥጢሩን ባለማወቁ ድምፁን ብቻ የዜማውን ጣዕም ብቻ በመስማቱ ነው እንጂ ምሥጢሩን አውቆት ቢሆን ኑሮ በቦምብ ወይም በጥይት ጨርሶ ያጠፋን ነበር፡፡

ምክንያቱም እኛ የባዕድ መንግሥት ግፍ ስለ አስቀቀንና የባዕድ መንግሥት አገዛዝን ስለ ጠላን በግዕዝ ቋንቋ የኢትዮጵያ መንግሥት ንጉሥ ከጥንት ጀምሮ የተሰየመው ንጉሠ ጽዮን የሚል ስለ ሆነ እኛም በዚሁ ስም ንጉሥሽ ጽዮን በጠላት አይሸነፍም (አይጠፋም) ሀገሪቱንም አይተዋትም በሚል ምሥጢራዊ ጸሎት እግዚአአብሔርን በመለመን በያሬድ ዜማ ወረባችንን እየመላለስን እንዘምር ስለነበር ነው፡፡ኢጣልያዊውም በጣዕመ ዜማው ተደስቶ በትግርኛ እየመላለሰ ዝፈኑ ይለን ነበር፡፡

ከሰኔ ፳፱ እስከ ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ከእሁድ ቀን በስተቀር እንደዚሁ በማለት በየቀኑ ከጥዋቱ በኢትዮጵያ ከ፪ ሰዓት እስከ ፰ ሰዓት የማታ፤ በፈ. ከጥዋቱ፰ ሰዓት እስከ ፰ ሰዓት የማታ ስንውል ጥዋት በመኪና ወስደው ማታ በመኪና እያመላለሱን ስንሠራ ስንብተን ሐምሌ ፲፰ ቀን ፲፱፴፩ ዓ.ም ፊልሙን የምታነሣውን መኪና አዘጋጅተው የኢጣሊያዊው አለቃ ያን ጳጳስ ተብዬ አባ ማስያስ ሲለው የነበረውን ሰው ልብሰ ምንግሥትን አልብሶ ዘውዱን በራሱ ላይ ደፍቶ፡ እኛንም ለያንዳንዳችን ወንበር ሰጥቶ አስቀምጦ ዛሬ ተቀምጣችሁ ነው ስትሠሩ የምትውሉ አለን::

ንጉሥ ግን ሲመጡ ናቸውና አዋጅ ነጋሪው ንጉሥ መጡ እያለ ፫ ጊዜ ሲናገር በ፫ኛው ጊዜ እናንተ ተነሥታችሁ ተቀበሉ ብሎ ነገረን:: አዋጅ ነጋሪ የተባሉትም አዝማች ገብረእግዚአብሔር ነበሩ:: ንጉሡም የሚመጣው በአዳራሹ ቤተ ክርስቲያን በስተጓዳው ነበር::

ከዚህ በኋላ አዋጅ ነጋሪ የተባሉት አዝማች ገብረ እግዚአብሔር በስተጓደው ደጃፍ ሁነው ፫ ጊዜ ንጉሥ መጡ ንጉሥ መጡ ሲሉን በ፫ኛው እኛም ከወንበራችን ተነሥተን እየሰገድን ስንቀበል ንጉሥ ተብየውም ዘውዱንና ልብሰ መንግሥቱን ተጎናጽፎ መጥቶ በፊታችን በነበረው የወርቅ ዙፋን ሲቀመጥ

www.ethiopianorthodox.org





ዋለ:: እንደ ገናም አላማረም በመባል እየተመላለሰ በዚሁ የቲያትር ሥራ ልምምድ ከጥዋቱ እስከ ማታ ተዋለ:: አዋጅ ነገሪውም ንጉሥ መጡ፤ ንጉሥ መጡ፤ ንጉሥ መጡ እያሉ ሲጮሁ በጣም እንደሰት ነበር:: እንዲያውም ቄስ ተስፋ እግዚእ የተባሉ ተላላኪ መጀመርያ በትግርኛ አዋጅ ነጋሪው ንጉሥ መጺኦም ንጉሥ መጺኦም(ንጉሡ መጡ ንጉሡ መጡ) ሲል ቄስ ተስፋ እግዚእ ደሞ ድርግም ይበሉ (ገደል ይግቡ ገደል ይግቡ)እያሉ ያስቁን ነበር::

እንዲህ እየተባለ ቀኑን ሙሉ ውለን ስናበቃ ኢጣሊያዊው እንግዲህ አብቅታችኊልና ከነገ ጀምሮ በየቤታችሁ ተቀመጡ ብሎ የድካማችን ገንዘብ ሳይሰጠን አሰናበተን::

ከዚህ በኋላ በነገታው ሐምሌ ፲፱ ቀን ፲፱፻፴፩ ዓ.ም እኒህ ትያትር ሲያሠሩን የሰነበቱ ኢጣልያኖች ወደ አሥመራ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲን መጥተው ኤጺስ ቆጶስ አቡነ ቄርሎስንና የቤተ ክርስቲን ገበዝ ቄስ ሀብተ ሚካኤል የተባሉትን ከነ ካህናቶቹ ጠርተው አምጥተው በሥርዓተ ቅዳሴያችሁ ጊዜ ሥጋው ደሙ ስታቁርቡ የድርጊቱ ሥነ ስርዓት ከመቅደሱ ወጥታችሁ ቁማችሁ እንደም አድርጋችሁ እንደምታቁርቡት አሳዩን ስላሉዋቸው እንዳይገድሏቸው ሲሉ መቅደሱን በቁልፉ ሊከፍቱ ቢሉ መዝጊያው አልከፈት ብሎ እምቢ አለ::

ጣልያኖቹም በገዛ እጃቸው ሊከፍቱ ቢሞክሩ እምቢ አላቸውና እንግዲስ እንስበረው መዝጊያውንም ሌላ ሐዲስ መዝጊያ እናደርግበታለን ብለው ሊሰብሩት ሲሉ ክቡር ቄስ ገበዝ ሀብተ ሚካኤል ‹‹የለም በሀገራችን መቅደሱ እንደዚህ አልከፈት ሲለን መዝጊያውን ሰብረን እመቀደሱ ብንገባ እግዚአብሔር መዓቱን ያወርድብናልና መዝጊውን ሰብረን ልንገባ አንችልም›› ሲሉ ተናገሯቸውና ልበሰ ተክህኖዋቸውን የለበሱ ካህናቱን ከመቅደሱ ደጃፍ አቁመው በፎቶግራፋቸው አንሥተው ሔዱ:: የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የወርቅ አልበሳትንም መርጠው መርጠው ከዚህም ማኸከል ልዑል ራስ ደስታ ዳምጠው ለቤተ ክርስቲን የሰጡት የብር ለምድና ልዑል ራስ ሥዩም መንገሻ የሰጡትን የቤተ ክርስቲያኑን የወርቅ ካባ:: ወደ ሀገራቸው ወሰዱት:: ይህንንም ግፍ በኛ በኢትዮጵያና በኤርትራ ሕዝብ ላይ የሠሩት ኢጣልያ የባዕድ መንግሥት ስለሆኑ ነው::





## ምዕራፍ ፳፮

የባዕድ መንግሥት ባዕድ የሚለየው በተፈጥሮ በኀብር እኛን በአለመምሰሉና በትውልድ ከኛ ባለመዋሃዱ ሲሆን እኛንም መጉዳቱ የማይቀር መሆኑን የሚያስረዳ ታሪክ ከዚህ ቀጥሎ እናያለን:: ይህንንም በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም በእንግሊዝ መንግሥት ረዳትነት ግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጋምቤላ በኩል የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማቸውን አቁመው (ሰቅለው) ፋሽስት ኢጣልያንን በማሸነፍ በድል አድራጊነት ተመልሰው አዲስ አበባ ከተማ ገብተው ዳግመኛ በመንበረ መንግሥታቸው ዙፋን በተገኙበት ጊዜ አይተነዋል::

በዚያ ጊዜ **የእንግሊዝ መንግሥት** የግርማዊነታቸው ረዳት የመሰለው የጦር ሠራዊቱን የፋሺሽት ኢጣልያ መንግሥትን በማባረር በድል አድራጊነት በሱዳን ሀገር መጥቶ ከሰላን ይዞ ፋሺታዊ የኢጣልያ ምንግሥትን አስለቅቆ ኤርትራን በያዘ ጊዜና ኤርትራን በማስተዳደር ኤርትራን ለዘለዓለም ስገዛ እኖራለሁ በሚል ተስፋ ነው:: የኤርትራ ሕዝብ ግን በኢጣሊያ ነጭ ባዕድ መንግሥት አገዛዝ ያን ያህል በአባቶቻች ሥቃይና መከራን አሳልፈን አሁን ደግሞ በነጭ ባዕድ መንግሥት ስንገዛ ልንኖር? እኛስ እግዚአብሔር በትውልድ የሥጋ ዘመዳችንና የኢትዮጵያ ሀገራችን ንጉሥን በድል አድራጊነት ከመለሰልን

www.ethiopianorthodox.org

በሀገራችንና ንጉሠ ነገሥታችን በሆነው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ብንገዛ ነው የሚሻለን አሉ ::

ሁሉምም ‹‹ኢትዮጵያ ሀገራችን ኃይለ ሥላሴ ንጉሣችን ሊገዛን ነው የምንፈልገው›› የሚል እንቅስቃሴ በሕዝቡ መንፈስ ሠርፆ ኢትዮጵያ ወይም ሞት በማለት የሀገር ፍቅር ማኅበር አቋቋሙ:: የእንግሊዝ መንግሥት ‹‹ማን ሊገዛችሁ ትፈልጋላችሁ›› ሲል ለኤርትራ ሕዝብ ባቀረበለት ጥያቄ መሠረት ሕዝቡ ኢትዮጵያዊ ስለሆነ ኢትዮጵያ ሀገራችንን ኃይለ ሥላሴ ንጉሣችንን ነው የምንፈልገው ሲል መልስ በመስጠቱ ይታወቃል:: የእንግሊዝ መንግሥት ምንም የንጉሠ ነገሥታችን ረዳት በመሆን ቢመጣ ባዕድ መንግሥት የነጭ ተፈጥሮ ያለበት በመሆኑና መንግሥቱን ለማስፋፋት ሐሳብ ስለነበረው ፊት ሲገባም ከኢጣልያ ጋር በጦርነቱ ጊዜ ንጉሣችሁ ኃይለ ሥላሴን ይዠላችሁ መጣሁ የሚል ጽሑፍ በየጊዜው በአውሮፕላን በመንዛት የነበረው ትቶ ለራሱ መንግሥቱን ለማስፋት ኤርትራን ለመግዛት ያለውን ሐሳብ ለመፈጸም ነበር:: የኤትርትራ ሕዝብ ግን ያልጠበቁትን መልስ ስለሰጣቸው ኤርትራን ለመግዛት ያቀደው ሐሳብ ሳይሆንለት መቅረቱን ተገንዝቦ በ፲፱፻፴፰ ዓ.ም ነሐሴ ፳፪ ቀን ከቀኑ በኢ.ት. ፲፩ በፈ. በ፰ ሰዓት ተኩል ከቀትር በኋላ ሲሆን የእንግሊዝ ባለ





ሥልጣኖች የሱዳን ወታደሮቻቸውን በመላክ አሥመራ ከተማን በሞላው ምንም ሳይሰማና ሳያውቅ በየቤቱና በየሥራው ሳለ ሰላማዊው ሕዝብ የሆነውን ሰው እመንገድ የሚሄደውን እቤት የቌየውን እቤት እየገቡ ወንዱንና ሴቱን ሕፃናቱን ሽማግሌውን በጥይትና በመትርየስ እየተኰሱ ጨረሱት:: ታዛዦቹ የሱዳን ወታደሮችም ከተጠቀሰው ሰዓት ጀምረው ሌሊቱ እስቲነጋ ድረስ ያገኙትን እስላምና ክርስቲያን ሳይለዩ በጥይትና በመትረየስ ገደሉት::

ያን ቀን እንግሊዝ የፈጃቸው ያልታወቁ ብዙዎቹ ሲሆኑ ከታወቁት ብቻ ከክርስቲያን የሞቱት ፷ (60) የቆሰሉት ፬፻(400) ነበሩ:: ከእስላሙም እንደዚያ ያታወቁት በየገደሉ በየመንገዱ የቀያቸውን ሰው ገድለው ወድያው በመኪና እያጓዙ በዱርና በገደል በወንዝና በበረሃ የጣልዋቸው ቁጥራቸው ሊታወቅ አልተቻለም::

ከእነዚያ ከሞቱት ሬሳቸው የተገኙ ክርስቲያን የተዋህዶ ሃይማኖትና የወንጌላዊት የሆኑ በአሥመራ ቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን የምዕመናን መቃብር በስተ ደቡብ በሚገኝ በዘባ ሳባ ትይዩ በሆነው መቃብራቸው በልዩ ሁኔታ ታጥሮ ይገኛል:: በካቶሊካዊት ክርስቲያን ወገን የሞቱትንም በየመቃብራቸው ተቀብረው ይገኛሉ::

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፳፮

ይህንን የጻፍኩት የባእዳን መንግሥታት በኛ ላይ በየጊዜው የግፍ ሥራና የባዕድ መንግሥት የሌላውን ሀገር ለመግዛትና መንግሥቱን ለማስፋፋት ያለውን ሐሳብ ለማስረዳት፡ መጪውም ትውልድ እንዲያውቀው ለማለት ነው እንጂ የሌላ ሃይማኖትን ለመንቀፍና የእንግሊዝ መንግሥት ለኢትዮጵያ ያደረገላትን እርዳታ ለግርማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥታችን ያደረገላቸውን ክብርና ረዳትነትን ለማቃለል አይደለም፡፡ስለዚህ ባእድ ባእድ ነው ዘመድ ዘመድ ነው ጥቂት ሥጋ እንደ መርፌ ትወጋ እንደ ተባለው የትውልዳችንና የሥርወ ምንግሥታችን ዘር መንግሥት ሲሆን ጥቅማችንን እንጂ ጉዳታችንን ክብራችንን እንጂ ውርደታችንን ስለማያስብ ይኸውና ያን ሁሉ የተሠራብንን የባዕድ መንግሥት የግፍ ሥራ የጭቆና አገዛዝ አሳልፈን አሁን በንጉሣችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አግኝተነው ያለውን ክብር ማሰብና አክብረን መያዝ አለብን፡፡

እሊህም ፳ንሆይ **ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ** ንጉሠ ነገሥታችን የሥርወ መንግሥታችንና የትውልዳችን የሥጋችንና የዓፅማችን ዘር መሆናቸውን ንጉሣችን በባዕድ መንግሥታት እኛ ኢትዮጵያውያን ከሦስተኛ ክፍል በላይ እዳንማር ክልክል የነበረውን ዛሬ እስከ ዩኒቨርስቲ መዓርግ

www.ethiopianorthodox.org





እንድንማር በማድረጋቸው፡፡ በሞኅው ተዘግቶብን የነበረውን የሥነ ጥበብ ትምህርት እስከ አይሮፕላን መንዳትና መሥራት መላው የአየርና የምድርን ጥበባት እንድንማር ሁኔታዎችን በማመቻቸታቸው ልንረዳ እንችላለን፡፡ የእግዚአብሔር ቸርነት ያልተለያቸው ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥታችን የተዘጋብንን ከፍተው ድንቁርናችንን አጥፍተው መዓርጋችንን ከዓለም ከከፍተኞች መንግሥታት ጋር አስተካክለው ሀገራችን እንድትከበር ባንዲራችን ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ የሆነው ወገናችን ስለሆኑ ነውና የኛ ልጆችና ወጣቶች መጪው ትውልዶችም ይህን አግኝተ ነው ያለነውን የብርሃን ኑሮ እያጣጣምን ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥታችን ረዥም ዕድሜና ጤና እንዲሰጥልን እግዚአብሔርን ከመለመን እንዳናቋርጥ አደራችንን ወደ እናንተ ልጆቻችን እንጥላለን አሜን፡፡

አዘጋጂው

ርእሰ ደብር ዕቁበ እንድርያስ ዓስቡ

አንባቢ ሆይ አስተውል!

እዚህ ጥንተ አሚን በተባለው ጽሑፌ ላይ አብዛኛው ታሪክ የቀድሞ የኢትዮጵያ ነገሥታት የሠሩትንና ያገኙትን ድል ባጭሩ የገለጥሁበት ምክንያት ኤርትራ ከጥንት ኢትዮጵያዊት መሆኗንና የኢትዮጵያ ሀገር ጥንታዊነትና መሠረት በመሆንዋ ነገሥታትዋም በየጊዜው በኤርትራ ላይ የሠሩትንና ድል ያደረጉበትን አንብበው በመረዳት መጪዎቹ ትውልዶች ኢትዮጵያዊነታቸውን እንዲገነዘቡ በማለት ነው።

ለሁሉም እግዚአብሔር ይርዳን አሜን።





## የአርእስት ማውጫ


ምዕራፍ ገጽ

፩. ስለ ስነ ፍጥረት

፪. ስለ አግአዝያን

፫. ስለ ትውልደ አብርሃም

፬. ስለ ንግሥተ ሳበ

፭. ስለ ሰሎሞናዊ መንግሥት ዘኢትዮጵያ

፮. ስለ ቀዳማዊ ምንሊክ

፯. ስለ ፍሬ ምናጦስ

፰. ስለ አብርሃ

፱. አጽብሐ

፲. ስለ ጻድቃነ ንኑም

፲፩. ስለ አባ ሊባኖስና አባ ዮሐኒ ስለ … ቅዱሳን

፲፪. ስለ ዓፄ ካሌብ

፲፫. ስለ ሀገረ ናግራን

፲፬.ስለ ዘእስራኤልና ዓፄ ገብረ መስቀል

የአፍ ታሪክ

፲፭. ስለ ዓፄ ዓምደጽዮን

፲፮. ስለ ዓፄ ዳዊት ቀዳማዊ ዘኢትዮጵያ ንጉሥ

፲፯. ስለ ግራኝ ንጉሥና ዓፄ ልብነ ድንግል

፲፰. ስለ ፖርቶጌዝ አመጣጥ


www.ethiopianorthodox.org

፲፱. ስለ ፖርቶጊዞች ሥራ

፳. ስለ ከግራኝ ጋራ ጦርነት

፳፩. ስለ ግራኝ ሞት

፳፪. ስለ ዓፄ ሱንዮስ

፳፫. ስለ ዓፄ ፋሲል

፳፬. ስለ አባ ርዝላና አባ ጱስፐ

፳፭. ስለ አባ ያዕቆብ ፈረንሣዊ

፳፮. ስለ ዓፄ ቴዎድሮስና ደጃች ንጉሤ

፳፯. ስለ አባ ማስያስና ደጅአዝማች ንጉሤ

፳፰. ስለ አባ ማስያስና ዓፄ ሚኒልክ

፳፱. ስለ ዓፄ ዮሐንስ

፴. ስለ ደጅአዝማች ባሕታ

፴፩. ስለ ልዑል ራስ መንገሻ ዮሐንስ

፴፪. ስለ ሐማሴን መባል ቀርቶ ኤርትራ የተባለችበት

፴፫. ስለ ኢጣልያ መንግሥት ትምህርት ቅነሳ

፴፬. ስለ ኢጣልያ መንግሥት የግፍ ሥራ

፴፭. ስለ እንግሊዝ መንግሥት

፴፭. ስለ ግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ



www.ethiopianorthodox.org